


እንኳን ለብርሃነ ልደቱ እና ጥምቀቱ አደረሰን

ዋጋ ብር 3

# ፈለገ ጥበብ

ጥር - መጋቢት ቁጥር ፫ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም



- ✞ የዑም ተወልደ መድኅኔ ዓለም
- ✞ መስዋዕተ ወንጌል
- ✞ ጸዮንን የሚጠሉ ይፈሩ
- ✞ ዳግና አቡነ ገብረ ክርስቶስ

www.ethiopianorthodox.org

# ዜና አህጉረ ስብከት

## ሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት

የሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ፈለገ ጥበብን ለምእመናኖቻቸው ለማዳረስ ጥረት ካደረጉት አህጉረ ስብከቶች አንዱ ነው። የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ለመጽሔቱ ያለውን አድናቆት ከመግለጹም በላይ የሀገረ ስብከቱን የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከት ዘገባ ልኮልናል፤ የዘገባው ጭማቂ እነሆ።

- ሀገረ ስብከት ራሱን ችሎ በሀገረ ስብከት ደረጃ የተቋቋመው በቅርብ ጊዜ በመሆኑ የራሱ የሆነ ጽ/ቤት አልነበረውም። ስለሆነም በቅርቡ ባለአምስት ክፍል አዲስ ቢሮ አሠርቷል። ወደ ጽ/ቤቱ የሚያስገባ ውም መንገድ አሠርቷል።
- በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ቅጽረ ግቢ በሚገኘው ሰፊ ቦታ ከ፯ ሺህ በላይ ባሕር ዛፍ በመትከል አጥጋቢ ውጤት አስመዝግቧል።
- በፍቼ ከተማ ዜሮ፩ እና ዜሮ፯ ቀበሌዎች ሁለት አፀደ ሕፃናትን በማቋቋም የከተማውን ሕፃናት ከነጣቂ ተኩላዎች በመከላከል ላይ ይገኛል።
- ለሰንበት ት/ቤቶችና ለካህናት የተለያዩ ሥልጠናዎችና ሰሚናሮችን ሰጥቷል።
- አህጉረ ስብከቱ በተለያዩ ቦታዎች ፲ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነጽ ላይ ይገኛል። የብዙዎች ግንባታም በመጠናቀቅ ላይ ነው።

ታሪካውያን ቅዱሳት መካናትንና በውስጣቸው የሚገኙ ንዋየ ቅድሳትን በመንከባከብ አስፈላጊውን ሁሉ እያደረገ ይገኛል።

## ምሥራቅ ሐረርጌ

የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ቀደም ሲል በሰንበት ት/ቤት ሠርገው ገብተው የነበሩትን መናፍቃን ለመግታት የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰዱንና ሰንበት ት/ቤቱን በአዲስና በተጠናከረ መልኩ በማደራጀት ላይ መሆኑን በብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ፊርማ ከተላከልን የሀገረ ስብከቱ ደብዳቤ ለማወቅ ችለናል።

ብፁዕነታቸው በዚህ ደብዳቤአቸው እንደገለጹት የመናፍቃንን እንቅስቃሴ ለመግታት ሲባል በጠቅላይ ቤተ ክህነትና በሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ዕውቅና ከነሐሴ ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ጀምሮ ሁኔታው እስኪስተካከል ድረስ በሀገረ ስብከቱ የነበሩ የሰንበት ት/ቤቶች በሙሉ ተዘግተው እንዲቆዩ ተደርገው እንደ ነበር አስታውሰው ከመስከረም ፲፱ ቀን ፲፱፻፺ ጀምሮ ግን የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በነበሩት በብፁዕ አቡነ ይስሐቅ አመራር ሰጪነት የተዘጉት የሰንበት ት/ቤቶች እንዲከፈቱ ሆነዋል።

በአሁኑ ሰዓት ሰንበት ት/ቤቶች ሥራቸው በተጠናከረ ሁኔታ እያከናወኑ ያለ መሆኑና በቅርቡም በአዲስ መልክ ተደራጅተው ሥራ የጀመሩበትን ፪ኛ ዓመት በዓላቸውን በርእሰ ከተማው በሐረር በሚገኙ ስድስቱ አድባራት በድምቀት ማክበራቸውን ከዘገበው ለመረዳት ተችሏል።

## ጅቡቲ

በጅቡቲ የሚገኘው የምሥራቀ ፀሐይ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በከተማው ያሉ ኢትዮጵያውያንን በተለይ ደግሞ ወጣቱን ከመናፍቃን ለመከላከልና ባለበት የስደት ኑሮ እምነቱን ጠብቆ በሃይማኖቱ ጸንቶ እንዲኖር በቀየሰው ስልት መሠረት፤

፩ኛ. ከታኅሣሥ ፩–ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም (ለሁለት ወራት)

፪ኛ. ከመጋቢት ፩–ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ለሦስት ወራት መደበኛ ኮርስ በማዘጋጀት ፶፫ ወጣቶችን ማስመረቁን ከጅቡቲ ከደረሰን የጽሑፍ ዜና ለማወቅ ችለናል። ሪፖርቱ በጅቡቲ እንደ ሀገር ውስጥ ሁሉ መናፍቃን በንግድና በተለያየ ሽፋን ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ በስደት የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን በወጥመዳቸው ውስጥ ለማስገባት ከፍተኛ መፍጨርጨር በማድረግ ላይ መሆናቸውን ጠቅሶ ይሁንና ቤተክርስቲያኑ ይህንን የመናፍቃንን እንቅስቃሴ ለመግታት አመቺ ስልት በመዘርጋት መንጋዎቹን በመጠበቅና በመከላከል እንደሚገኝ ገልጿል።

## ኢሊባቦር ሀገረ ስብከት

የኢሊባቦር ሀገረ ስብከት የ፲፱፻፺፩ ዓ.ም የሥራ ክንውን በመገምገም ለ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የሥራ ዕቅድ በማውጣት ለሥራው ሂደት መከናወን የሚረዳው መርሃ ግብር ነድፎ አጽድቋል።

ሀገረ ስብከቱ በተለይ ለፈለገ ጥበብ መጽሔት ዝግጅት ክፍል በላከው ደብዳቤ እንደ ገለጸው ይህ መርሐ ግብር የተነደፈው መስከረም ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የሀገረ ስብከቱ የ፲፪ ወረዳዎች ሊቃነ ካህናት፤ የመቱ ከተማ አራቱ አድባራት አስተዳዳሪዎችና የሀገረ ስብከቱ የክፍል ኃላፊዎች በተገኙበትና በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ ርእሰ መንበርነት በተመራው ጉባኤ ነው።

በአዲሱ ቃለ አዋዲ አፈጻጸም፣ በስብከተ ወንጌልና የሰንበት ት/ቤቶች እንቅስቃሴ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ የተወያየው ይህ ጉባኤ ያለፉትን ጠንካራና ደካማ አሠራሮችን በመገምገም ለወደፊቱ መሠራት ባለባቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን አስተላልፏል። በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም የሥራ ዘመን መልካም ውጤት ላስመዘገቡ አብያተ ክርስቲያናትም ሽልማት ተሰጥቷል። ❖

## መልእክት ለአንባብያን

የፈለገ ጥበብ መጽሔት ቋሚ ደንበኛ ለመሆን ለምትፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የሚከተለውን የክፍያ መጠን በመፈጸም መጽሔቱን በየ፫ወሩ ማግኘት የምትችሉ መሆናችሁን እየገለጽን፤

ደንበኞች ክፍያውን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ለሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሂሳብ ቁጥር 1955 ገቢ በማድረግ ሙሉ ስማቸው ከነ አድራሻቸው በፖስታ ቤት በኩል መላክ የሚችሉ መሆናቸውን የምናረጋግጠው በደስታ ነው።

| ቦታ | ሁለት እትም/ግማሽ ዓመት | አራት እትም/የዓመት |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ | ፯.፳፭ | ፲፪.፶ |
| ክፍለ ሀገር | ፯ | ፲፬.፴ |
| ውጭ ሀገር | ፬ ዶላር | ፰ ዶላር |

# ፈለገ ጥበብ

፪ ዓመት ቍጥር ፫

ጥር ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

በየ፫ ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት

## ከአዘጋጁ ብዕር

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ።

ክብር ምስጋና ለእግዚአብሔር ይድረሰውና እነሆ ፈለገ ጥበብ መጽሔት ለሦስተኛ ጊዜ ከእናንተ ጋር ለመገናኘት በቃች። ከእናንተ የሚደርሱንን ጥቆማ ዎች፤ አስተያየቶች፤ መነሻ በማድረግ ዝግጅታችንን ለማሻሻል ጥረት አድርገናል። ይኸው ጥረታችን ለወደፊቱም ይቀጥላል።

ፈለገ ጥበብ በወጣቱ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በመላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ ተወዳጅነትንና ተቀባይነት እንዳገኘች ከሚደርሱን በርካታ የደብዳቤ፤ የስልክና የቃል መልእክቶች ለማወቅ ችለናል። በአንፃሩ በመጽሔቷ መውጣት የተደናገጡ መናፍቃንና እኛን መስለው የእምነት ጠላቶቻችንን ዓላማ የሚያራምዱ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተሰገሰጉ የቀበሮ ባሕታውያን መጽሔቷ በሕዝብ እጅ እንዳትገባ የተቻላቸውን ያህል ሲጥሩ ይስተዋላሉ።

በበኩላችን ይህን እንደሚያጋጥመን አስቀድመንም ገምተናልና በዚህ ቀላል ፈተና አልተደነቅንም አልተደናገጥንም። ነገና ተነገ ወዲያ የሚገጥሙን መሰል ፈተናዎችም በእናንተ ጸሎትና በእግዚአብሔር ኃይል እንደምናሸንፍ አንጠራጠርም። የእኛ መስተ ዋቶች እናንተ አንባቢዎች ናችሁና አሁንም ተሳትፎ አችሁንና አስተያየታችሁን እንሻለን።

«እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን»

ማውጫ


❖ ለጸሎትና ለንስሐ እንትጋ . . . ፫
❖ የልጆች እድገት በምን በምን? . ፭
❖ ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም
ዮም ተወልደ ከሣቴ ብርሃን . . ፯
❖ መግረሬ ፀር . . . . . . . ፰
❖ ትምህርተ ሃይማኖት
ጥንተ ትምህርተ ዘሃይማኖት . . ፲
❖ ሕግን ሁሉ ይፈጽም ዘንድ በዮርዳኖስ ተጠመቀ . . . . . . . . . ፲፫
❖ እኔም ወጣት ነበርኩ
ብላታ ልሳኑ ሃብተወልድ . . ፲፮
❖ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
መሥዋዕተ ወንጌል (ሥጋወደሙ) . . . ፲፱
❖ ጽዮንን የሚጠሉ ይፈሩ . . . ፳፩
❖ የመላእክት ተራዳኢነት . . . ፳፮
❖ ከወጣቱ ለወጣቱ
በቡሩሹ የሚሰብከው ወጣት . . ፳፱
❖ እስትጉቡእ
ዳግና አቡነ ገብረክርስቶስ . . ፴፪



ስልክ 11 23 69/12 34 25
ፖ.ሣ.ቁ. 81286
አዲስ አበባ



ዋና አዘጋጅ:- ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር
ም/ዋና አዘጋጅ:- መልአከ ሰላም ኃይለየሱስ ከበደ
ኤዲተሮች:- ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ
ቀሲስ በላይ ተገኝ
መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ


የፊት ለፊት ሽፋን በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከሰቆቃወ ድንግል

www.ethiopianorthodox.org

# እኛና እናንተ

ለውድ ለተከበራችሁ ለፈለገ ጥበብ መጽሔት አዘጋጆች ለጤናችሁ እንደምን አላችሁ? በአንደኛና በሁለተኛ እትማችሁ ጥሩ የሆኑ ጽሑፎችን አቅርባችኋል። በተለይ በሁለተኛው ዕትማችሁ ከሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ ጋር ያደረጋችሁት ትምህርት አዘል ውይይት ለወጣቱ አርአያ የሚሆንና ትምህርት የሚሰጥ በመሆኑ ለወደፊቱም ሌሎች ሰዎችን እያነጋገራችሁ ትምህርት እንድትሰጡ አስተያየቴን እሰጣለሁ። በሌላ ደብዳቤ እስከ ምንገናኝ ደህና ሁኑ።

ከቅዱስ ማርቆስ ቤ/ክ ሰንበት ት/ቤት
ዘካርያስ ነገደ

የፈለገ ጥበብ አዘጋጆች እንደምን ሰነበታችሁ ይህንን ደብዳቤ ልጽፍላችሁ ያነሣሣኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፪ መስከረም ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ያታተመችውን ፈለገ ጥበብን ሳነብ አንዳንድ ቅሬታዎች ስላደሩብኝ ነው። በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ መንፈሳዊ ጽሑፎች ሕይወትን ለማነጽ ታልመው ይመስለኛል። ነገር ግን «እኔም ወጣት ነበርኩ» በሚል ዓምድ ከአቶ ዓለመ ሥላሴ ጋር የተደረገው ቃለመጠይቅ በብዛት መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የሚዳስስ ባለመሆኑ ያገኙሁት መንፈሳዊ ትምህርት ትንሽ ነው። ጴናንትም ቃለ መጠይቁን ስታቀርቡ እንደ ዓለማውያን ጋዜጠኞች ነው፤ የአቶ ዓለመ ሥላሴ መልስም እንደዛው ነው።

ሌላው ደግሞ አቶ ዓለመ ሥላሴ የተቀኙትን ቅኔ በግዕዝ አቅርባችሁ በአማርኛ አልተረጐማችሁትም ይህ ደግሞ ሊታለፍ የሚገባው ጉዳይ አይደለም።

በተረፈ ሌላው ዝግጅታችሁ እንከን አይወጣውም ኪዳነምሕረት ጽናትን ትስጣችሁ እላለሁ።

እክሊለ ጊዮርጊስ
ከአርባ ምንጭ ዓለመ ብርሃን ሰንበት ት/ቤት

ፈለገ ጥበብ መጽሔት በትምህርት ሰጪነትዋ ደስ ብላኛለች። ለወደፊቱ ስለ ሥርዓተ ጥምቀት፣ ሥርዓተ ሜሮን፣ ሥርዓተ ቁርባን፣ ሥርዓተ ንስሐ፣ ሥርዓተ ክህነት፣ ሥርዓተ ተክሊል፣ ሥርዓተ ቀንዲል ይዛ ብትወጣ ደስ ይለኛል። ወጣቱ ወደመ ናፍቃን የሚሄድበት አንዱ ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ስለማያውቅ ነውና።

ባደግ ተስፋዬ
ከዲላ ደብረ ገነት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት

ሁለቱንም የፈለገ ጥበብ እትሞችን አንብቤአቸዋለሁ። ብዙ ቁም ነገሮችንም አግኝቼባቸዋለሁ። በተለይ ወጣቱና ቤተክርስቲያን የተሰኘው አምድ ብዙ አስተምሮኛል። ነገር ግን ከሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ ጋር ባደረጋችሁት ቃለ መጠይቅ አንድ ቅር ያለኝ ነገር አለ። ‹ሻለቃ ኃይሌ የሥራ ጠባይህ በጾምና በጸሎት ላይ ያሳደረው ተጽእኖ ይኖራል?› ለሚለው ጥያቄ የሰጠው መልስ አርአያነት ያለው አልመሰለኝምና ቢታሰብበት።

ኃይለ ሥላሴ (ተ.መ) – ከሀገረ ማርያም (ቡልጋ)

«የጐደለውን ለመሙላት የጠበበውን ለማስፋት አሁንም የእናንተን ተሳትፎ እንጠብቃለን።» በተባልነው መሠረት አስተያየቴን ጽፌላችኋለሁ።

• መጽሔቷ የምትዘጋጀው በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ እንደ መሆኑ ሰንበት ት/ቤቶችን የሚመለከት የተለየ ዓምድ ቢኖራትና ከአንባብያን የሚላኩ ጥያቄዎች የሚያስተናግዱበት የተለየ ዓምድ ቢከፈት።

• በመጽሔታችሁ የቤተክርስቲያናችንን ቁጥሮች መጠቀማችሁ መልካም ቢሆንም አንዳንድ የቁጥር ግድፈቶች አሉ ለምሳሌ የዘመን አቆጣጠር በሚል ርእስ ሥር «ዓመተ አዳም ወዮኅ» ጽሑፍ መሐል ፻፶ ቀናት መባል ሲገባው የ፶ ቀን እየተባለ ተጽፏል። ፻፶ ቀናት ማለት ሲገባው ፻፶ ቀን ተብሏል።

• በመጨረሻም በቤተክርስቲያናችን ዶግማ ቀኖናና ትውፊት መሠረት የሚወጡትን ትክክለኛ የኀትመት ውጤቶችና ካሴቶች እየተከታተላችሁ ዝርዝራቸውን በመጽሔቷ እንድትገልጹልን አደራ እላለሁ።

ሀብታሙ አምባቸው – ሰሜን ወሎ ቆቦ

አዘጋጅ፡- ለአስተያየትዎ ምስጋናችን የላቀ ነው። በመጨረሻ ላቀረብዋቸው ጥያቄዎች ለወደፊቱ ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት እንሞክራለን።

## ማረሚያ

በፈለገ ጥበብ ቁጥር ፪ መጽሔት የዘመን አቆጣጠር «ዓመተ አዳም ወዮኅ» በሚለው ርእስ ስር በአንቀጽ ፪ ፲፩ኛና ፲፫ኛ መስመር፣ በአንቀጽ ሦስት ፮ኛ መስመር፣ በ፫ኛ አንቀጽ ፫ኛና ፬ኛ መስመር ላይ የ፶ ተብሎ የተጻፈው በስህተት ስለሆነ ፻፶ (መቶ ሃምሳ) ተብሎ እንዲነበብ በታላቅ ትሕትና እንጠይቃለን።

# ለጸሎትና ለንስሐ እንትጋ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኤኮኖሚክ ኮሚሽን የስብሰባ አዳራሽ ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም በተከፈተው የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ኤድስ ጉባኤ በእንግሊዝኛ ካስተላለፉት አባታዊ መልእክት ትርጉም የተወሰደ፤



እስካሁን ከተከሰቱት በሽታዎች ሁሉ ኤድስ እጅግ ቀሳፊ እየሆነ መጥቷል። በመላው ዓለም ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ነው። በሽታው ተተኪ በሌላት የሰው ሕይወት ላይ ከሚያስከትለው ጥፋት በተጨማሪ የሚያደርሰው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በጣም ሠፊና ሥር የሰደደ ነው።

በየቀኑ በኤድስ ሳቢያ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች እንደሚሞቱ ስንሰማ ልባችን በኀዘን ይነካል። ወላጆቻቸውን በኤድስ የተነጠቁ ቁጥራቸው በ፲ ሺህዎች የሚገመት ዕጓለ ማውታ መኖራቸው በጣም የሚያሰቅቅ ነው። በተለይ «በኤድስ ምክንያት በመላው ዓለም ወላጅ አልባ ከሆኑት ሕፃናት መካከል ቢያንስ ፺፫% ያህሉ አፍሪካውያን መሆናቸውን» ስንሰማ በጣም እናዝናለን። እነዚህ የወላጆቻቸውን ፍቅር፣ እንክብካቤና ምቾት ያጡ ሕፃናት፣ ያላቸው ዕድል በማኅበረ ሰቡ እጅ መውደቅ ብቻ ነው። የነርሱ ዕጣ ፈንታ እጅግ መራር ነው። በእውነቱ እነዚህ ሕፃናት ባላጠፉት ጥፋት ከባድ ቅጣት የተጣለባቸው መሆኑ አሳዛኝ ነው።

ሞትን በፍርሀትና በቀቢፀ ተስፋ እየተሸማቀቁ የሚጠባበቁ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሕዋሱ ተሸካሚዎች መኖራቸውን ስንሰማ በእጅጉ እናዝናለን። በኤድስ መያዝ አስፈሪ ከሆነው ሞት ጋር የተያዘ ቀኑ ያልታወቀ ቀጠሮ ነው። በሰቀቀንና በፍርሀት የተወጠረ ቀጠሮ ነው።

ኤድስ የሚያስከትለው ማኅበራዊ ጉዳት እጅግ ሰፊ ነው። ኤድስ ቅስምን የሚሰብርና የመገለል ስሜትን የሚፈጥር ነው። የኤድስ ሕሙም ማኅበረሰቡ ገለልተኛ አድርጎኛል በማለት ዘወትር ጭንቀት ይሰማዋል። ከዚህም የተነሳ እርሱም ሆነ እርስዋ በሥነ ልቡናዊ ችግር ይዋጣሉ። ማኅበረሰቡ አግልሎኛል የሚል ስሜት ስለሚያድልባቸው በራስ የመተማመን ስሜትና ሰብአዊ ክብራቸው ይሟጠጣል። ሥራና የጤና እንክብካቤ ስለማያገኙ ሰብአዊ መብታቸው ይጣሳል።

ባለሙያዎች በተለይ በአፍሪካ ኤድስ በአስደንጋጭ ሁኔታ የሰው ኃይል እጥረትን፣ የወጣቶች ሕይወት መቀጠፍን፣ የአምራች ኃይል ቁጥር መመናመንንና የምርት መቀነስን እንዳስከተለ ይናገራሉ። የአሜሪካን የርዳታ ድርጅት ባካሔደው ጥናት «ኤድስ የአፍሪካ ሀገሮችን አጠቃላይ ዓመታዊ ምርት ከዜሮ.፫ እስከ ፩.፬% በዓመት እንደሚቀንስ» ገልጿል።

የቴክኖሎጂ ፈጣን ግስጋሴ አዳዲስ ሳይንሳዊ ውጤቶችን እያስገኘ መሆኑን እንሰማለን። ከቶውንም መፍትሔ የላቸውም ተብለው የነበሩ አንዳንድ ችግሮች አሁን እየተፈቱ ነው። ጥበብ በጣም ረቋል። የዓለምም ሀብት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው። ይሁን እንጂ ለኤድስ ፍቱን መድኃኒት ገና አልተገኘለትም። ተመራማሪ ሊቃውንት ለኤድስ ዘላቂ ፈውስ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም እንዳችም አስተማማኝ መፍትሔ አልተገኘም። በአኳያው በሽታው መስፋፋቱንና መዛመቱን አላቆመም። የሰውም ሕይወት በየቀኑ ይቀጠፋል። ይህን የኤድስ ወረርሽኝ ለመቋቋም እንግዲያስ ምን መደረግ አለበት? በኛ

www.ethiopianorthodox.org

በኩል ብቸኛውና አስትማማኙ የድኅነት ጎዳና የእግዚአብሔር መን ገድ እንደሆነ እናምናለን።

እግዚአብሔር አምላክ የምድርን በረከት ሰጥቶናል፤ ልንከተለው የሚገባውን ሕግጋትም ደንግጓል። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚነግሩን የእግዚአብሔርን ሕግ መጣስ በራስ ላይ ቁጣን መጋበዝ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንዲህ ሲል ያስጠነ ቅቀናል «ማንም ሲፈተን በእግዚ አብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እርሱ ራሱ ማንንም አይፈትንም። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች» ያዕ.፩፥፲፫–፲፭።

ስለዚህ በአማንያን አመለካከት የኤድስን መስፋፋት ለመግታት የእግዚአብሔርን ሕግጋት እናከብር ዘንድ ግድ ነው። አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሚለው የቅዱስ ጋብቻ ሕግ ሊከበር ይገባዋል። ራስን በሚገባ የመምራት ችሎታና የኃላፊነት ስሜት መገንባት ይኖርበታል። ሕይወትን በሥርዓት አለመምራት ራስን በግድየለሽነት ለማጥፋት እንደ መወሰን ይቆጠራል። ራስንና ቤተሰብን በመንከባከብ ቤተሰቡን በኃላፊነት ስሜት መምራት የተግባር መመሪያ መሆን አለበት። እግዚ አብሔር ከፍጥረታት ሁሉ አልቆ የፈጠረው የሰው ልጅ ራሱን አዋርዶ በደመነፍስ የሚመራ መሆን አይገባውም። ይልቁንም በቅዱስ እግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ ሁሌ ሊታሰበው ይገባል። ስለሆነም በእግዚአብሔር አምሳልና መልክ የተፈጠረው ሰው ኃላፊነት ተሰምቶት ሕይወቱን በሥርዓት ሊመራ ይገባል።

በዚህ መልካም አጋጣሚ የረዥም ዘመናት ዕድሜ ስላለው ክርስቲያናዊ የኢትዮጵያውያን የቤተሰብ አስተ ዳደግ ጥቂት ለመናገር እወዳለሁ። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቅንጅት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርና የቤተ ሰብ ፍቅር የሰፈነበትና ለአዛውንት ወይም ለዕድሜ ባለጸጎች ከበሬታ የሚሰጥ የተቀደሰና የተሳሰረ ድርጅት ነበር። በተለይ ወላጆች የልጆቻቸው የጋብቻ ሕይወት የተሳካና የሰመረ እንዲሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር። በጋብቻ ወቅት የወላጆች ምክር፤ ይሁንታና ምርቃት ትዳሩን ያፀናዋል ተብሎ ይታመን ነበር። ከዚህም በቀር ጋብቻ እስኪፈጸም ድረስ ድንግልናን ጠብቆ በንጽሕና መገኘት በወላጆችም ሆነ በተጋቢዎች ዘንድ ያኮራ ነበር። ይህ አድራጎት ሥነ ሥርዓት አክባሪነትንና ታማኝነትን ከመግለፁም በላይ የቅዱስ ጋብቻን ሥርዓትና ሕግጋት ማክበርን የሚገልፅ ነው። ዳሩ ግን የሥነ ምግባር ልልነት ይልቁንም እኒህን መልካም ባህላዊ እሴቶች ችላ ማለት ልቅ ግንኙነትንና ግዴለሽነትን አስከትሏል። ይህ ኢትዮጵያዊ መልካም የአስተዳደግ ባህል ያንሠራራ ዘንድ ሁሉም ሊተጋ ይገባዋል።

ኤድስን ለመከላከል ሌላው ሁነኛ ዘዴ፤ ኤድስ ስለሚያስከትለው አደጋ በሥርዓት የተዘጋጀ ጥልቀትና ተከታታይነት ያለው መንፈሳዊና ሙያዊ ትምህርት ለኅብረተሰቡ መስጠት ነው። በዚህ መሠረት፤ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የጋብቻን ክቡርነት ጠንቅቀው እንዲገነዘቡና ራሳቸውን ከአደጋ እንዲጠብቁ በስፋት እያስተማረች ነው።

ቀደም ሲል እንደ ጠቀስኩት ኤድስን ለመቋቋም ብቸኛው አስተ ማማኝ መፍትሔ ሊገኝ የሚችለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ነው። ከልብ ተጸጽተን ንስሐ በመግባትና ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ምሕረት እንዲያደርግልን፤ ፈውስ እንዲሰጠን ልንማጸነው ይገባል። ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ስለ ንስሐ የማዳን ኃይል በአፅንዖት ሲናገር እንዲህ ይላል:- «ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነፃለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች» (ኢሳ.፩፥፲፰)

የሰው ልጅ በንጹሕ ልቦና በተሰበረ መንፈስና በቅን ሕሊና በንስሐ ወደ ፈጣሪው ሊቀርብ ወይም ሊመለስ ይገባል። ልባችንና አእምሮ ዋችንን ወደ እግዚአብሔር መልሰን ሕጉን ብንጠብቅ እግዚአብሔር አምላክ ይህን ቀሳፊ በሽታ ከገጸ ምድር ሊያጠፋው ይችላል። በሙሉ ልብ ተጸጽተን ንስሐ ብንገባ ዘላለማዊ የርኅራኄ ምንጭ፤ ቅንና ቸር የሆነው ፈጣሪ አምላክ ይፈውሰናል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር «...ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋ ላችሁ። ...እንዲሁ ንስሐ ከማያስ ፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል» (ሉቃ.፲፫፥፫፤ ፲፭፥፯) ብሏል። ከኤድ ስም ሆነ ከማንኛውም ሕመም ለመዳን፤ ለጸሎትና ለንስሐ እንትጋ።

«እግዚአብሔር ሁሉንም በምሕረቱ ይባርክ» ✣

# የልጆች እድገት በምን በምን?



ለሰው ልጅ በአካል፤ በአዕምሮ፤ በሃይማኖት (በመንፈስ) እንዲያድግ ከሚያስፈልጉት በርካታ ነገሮች ውስጥ ቀዳሚውና መሠረታዊ ነገር፤ ምግብ፤ ልብስና፤ መጠለያ ነው። ለዚሁም ሕፃንን በሞግዚትነት ተንከ ባክቦ መያዝና ማሳደግ ያስፈልጋል። ሕፃናት ፍላጎታቸውን የሚገልፁት በማልቀስ ነው። እናት ልጁ የሚያ ለቅሰው ርቦት፤ ኀርብቶት፤ አሞት በአጠቃላይ በምን ምክንያት እንደሆነ ታውቃለችና በመልካም ሞግዚትነት ታፅናናዋለች።

ቅዱስ ጳውሎስ ልጆቻችሁን በመልካም አስተዳደግ አሳድጓቸው ኤፌ.፮፥፩ እንደሚለው ሁሉ፤ ልጆች እንዳይርባቸው፤ እንዳይጠማቸው፤ እንዳይታረዙ፤ እንዳይከፋቸው በመ ጀመሪያ የአካል እንክብካቤ ሊያደር ጉላቸው ይገባል፤ ይኸውም:-

አንደኛ በአእምሮ:-

ሕፃናት ለትምህርት ሲደርሱ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ ማድረግ ከአራትና ከአምስት ዓመት ጀምረው ፊደል እንዲቆጥሩ፤ ከዚ ያም በመቀጠል ፊደሎችን በሚገባ ለይተው እንዲያውቁ፤ አቡጊዳ እየተባለ የሚጠራውን ፊደሎችን ለያይቶ የሚያስቀምጠውን ክፍል እንዲማሩ ማድረግ፤ ይህን ክፍል ካጠኑ በኋላ ገበታ ሐዋርያት የሚባለውን የቅዱስ ዮሐንስን መልዕክታት ማስተማር ወይም መማር ነው። የሚጀምረውም መልእክተ ዮሐንስ ሐዋርያ ወልደ ዘብዴዮስ የሚለው ነው። ይህን ክፍል በቍጥር፤ በግዕዝ፤ በንባብ ከተማሩ በኋላ በተገኘው መጽሐፍ አጠቃላይ ንባብን ይማራሉ፤ የንባቡን ክፍል አጠናቅ ቀው ከአጠኑና ከአወቁ በኋላ ዳዊት የተባለውን መጽሐፍ ይማራሉ፤ ይህን መጽሐፍ አጥንተው ሲጨርሱ ዳዊት ደገመ ዳዊት ደገመች የምሥራች ይባላሉ፤ በቤተሰብና በአሳዳጊዎች ዘንድ ሽልማት ያገኛሉ። ተማሪዎችም ደስ ይላቸዋል፤ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር እንደፈቀደላቸውና ወላጆች እንዳሰማሯቸው ይሆናሉ። ማለት ለክህነትና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ትምህርቱን በመቀጠል ዜማውን፤ ቅኔውን፤ ቅዳሴውን፤ አቋቋሙንና ዝማሬ መዋሥዕቱን፤ ያለላቸው በመቀጠል ብሉያቱንና ሐዲሳቱን መጽሐፈ ሊቃውንቱን የቁጥር መጽሐፉን ወይም አውሻክሩን ይማራሉ። ይህ ዕድል ወይም እውቀትና ትምህርት ከክህነታዊ አገልግሎት በቀር ልዩነት አያደር ግም፤ ለምሳሌ ያህልም እነማሆይ ገላነሽን፤ እነማሆይ ቤተልሔምን የመሳሰሉት የቅኔ መምህራን ከናቶች ወገን ናቸው። ይህ ሁሉ ሊደረግና ሊፈፀም የሚችለው በልጅነት ከአባትና እናት አሳዳጊ ቤተሰብ በሚደረገው ቁጥጥርና እንክብካቤ የተነሣ ነው። ዛሬ ግን ይህ ሁሉ ዕውቀትና ፍልስፍና ቀረና ኢትዮጵያ ውያን ሁነው የኢትዮጵያ ቋንቋ የኢትዮጵያን ሥርዓትና ባህል የማያውቁ ልጆች እያየን ነው፤ አማርኛም የማይናገሩ አሉ።

ሁለተኛ ደረጃ በአጠቃላይ በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ቋንቋና ፍልስፍና የሚሰጠውን ትምህርትና ዕውቀት እንዲማሩ ማድረግ ነው። አንዳንዶች ዘመናዊ ትምህርት መማርና ማጥናት፤ ማወቅ ከእምነትና ከባህል ሥርዓት ውጭ የሆነ መስሏቸው ልጆቻቸውን ከዕውቀት ማዕድ ለይተዋቸው ነበር፤ ቁም ነገር ያለው መሆኑን ውለው አድረው ሲያጤኑት ግን የእግር እሳት ሆኖባቸዋል።

ቢሆንም ባንድ በኩል እውነታ አላቸው፤ የትምህርቱ እለፍ ተቀደም መጠናት አለበት። «ቅድመ መሀር ዎሙ ሉውሉድክሙ መዝሙረ ዳዊት ወሰሎሞን ወመጽሐፈ ሲራክ» ማለት ለልጆቻችሁ አስቀድማችሁ መዝሙረ ዳዊትን፤ ሰሎሞንን፤ መጽሐፈ ሲራክን አስተምሯቸው ማለት ነው።

መዝሙረ ዳዊት ስለ ልጆች ሲናገር እንዲህ ይላል። የእግዚአ ብሔር ምስክር የታመነ ነው ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል። መዝ.፲፰፥፯ መጽሐፈ ሰሎሞንም እንዲህ ይላል። ሰነፍን የሚወልድ ኃዘን ይሆንበታል የሰነፍ ልጅ አባት ደስ አይለውም። የልጆች ክብር አባቶቻቸው ናቸው የአባቶችም ክብር ልጆች ናቸው ብሏል። መጽሐፈ ሲራክም ስለ ልጆች ዕውቀትና መማር ወላጆች በልጆች መማር ደስ እንደሚላቸው ሲናገር እንዲህ ይላል።

ልጁን የሚወድ ሰው ደስ ይለው ዘንድ ልጁን መቅጣት መቆጣጠር ቸል አይልም፤ ልጁን ያስተማረ ሰው በልጁ መማር ያመሰግኑታል ልጁን ያስትማረ ጠላቱን ያስቀናል አባቱም ቢሞት እንዳልሞተ ይሆናል መልካም ልጅ ወልዶ በመልካም ሁኔታ አስትምሮ አሳድጓልና።

ያልተገራ ፈረስ ገርጋሪ ይሆናል፤ ያልተማረ ልጅም አውታታ ሆኖ ያድጋል። በሱ ጥፋት አንተ እንዳታፍር ልጅህን አስትምረው ያገለግልህ ዘንድ። መጽሐፈ ሲራክ ምዕራፍ ፴። መጻሕፍቱ እንዲህ ያለ ምክርና ዕዝናት ስለሚሰጡ ነው ልጆችን መጀመሪያ መዝሙረ ዳዊት፤ ሰሎሞንና መጽሐፈ ሲራክን አስተ ምሯቸው ያለው። ልጆች ባሁኑ ጊዜ የት ይማሩ? በቤት ወይስ በጎረቤት ወይስ በትምህርት ቤት፤ ወይስ በቤተ ክርስቲያን? ልጆቹን ቤተሰቦቹን መክሮ አስትምሮ ተቆጣጥሮ የሚያሳ ድግ፤ የሚያስተምር መልካም ቤተ

www.ethiopianorthodox.org

ሰብ አለ? መልካም ጎረቤት አለ? በፍቅር በሰላም በማኅበራዊ ኑሮ ተባብሮ የሚኖር ወይስ የቀንጣፋና የቁልቋል ጉርብትና ኑሮ ነው የሚኖረው? በነገር ሲደማ ሲቆስል እንዲህ ያለ ጉርብትና ተሆነ ልጆች የት ይደጉ የት ይማሩ ከማን ይማሩ?

ከቤት መልካም አስተዳደር ከሌለ መልካም ጎረቤት ከሌለ፣ በትምህርት ቤት ለተማሪዎች መልካም አርአያ የሚሆን መምህር ከአልተገኘ፣ በቤተ ክርስቲያን መንጋውን የሚጠብቅ የንስሐ ልጆቹን ከነልጆቻቸው የሚያስተምር ካህን ካልተገኘ የት ይማሩ?

## በሦስተኛ ደረጃ

የልጆች ዕድገት በመንፈስ የተባለው፣ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት የላቀና የከበረ ስለሆነ የመንፈስ ዕድገት ያስፈልገዋልና። ይህም ማለት፣ ከየት እንደመጣ፣ ወደየት እንደሚሄድ፣ በማን እንደሚኖር፣ ማን እንደፈጠረው፣ ማን እንደሚመግበው፣ ማን እንደሚያድነው ማወቅና መረዳት ስላለበት ነው።

ለዚሁም የመጀመሪያም አስተማሮች እናት አባት ናቸው፣ በመቀጠልም ቤተ ክርስቲያን ናት፣ የሚማሩትን ትምህርት ዓለምንና በዓለሙ የሚኖሩ ፍጥረታትን የፈጠረ እግዚአብሔር መሆኑን ማሳወቅ ነው። ስለዚህ ቀጥሎ ያሉትን የእግዚአብሔር ሕጎችንና ትእዛዞችን ማስተማር ነው።

፩ኛ. ከኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ

፪ኛ. የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ

፫ኛ. ሰንበትን አክብር

፬ኛ. እናትና አባትህን አክብር

፭ኛ. አትግደል

፮ኛ. አታመንዝር

፯ኛ. አትስረቅ

፰ኛ. በሐሰት አትመስክር

፱ኛ. አትመኝ (ዘጸ.፳፥፫–፲፯)

፲ኛ. ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ (ዘሌ.፲፱፥፲፰)

ይህ ትምህርትና ጥናት የሰው ልጅ ሁሉ ሊማረውና ሊያጠናው ይገባል፤ የኑሮ ሕይወት ነውና። ሰርቶ ገድሎ መኖር አይችልም ቢኖርም በግልጥ አይኖርም።

በመቀጠል፣ የእግዚአብሔር ቸርነትም ጥበብም እንዲረዱ ከእሑድ እስከ ዐርብ የተፈጠሩትን ፍጥረታት ልጆች እንዲያውቁና እንዲረዱ ማድረግ፣ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ የሚለው ቃል ቀላል አይደለምና የዓለም ባለቤት አምላክ መሆኑን ይረዱ። ቤተ ክርስቲያን፣ ልጆች ከሰባት ዓመት ዕድሜያቸው ጀምረው ትምህርት እንዲማሩ ሥርዓት እንዲያጠኑ ታዛለች። ከዚያም በፊት ወንድ በአርባ ቀን ሴት በሰማንያ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን በወላጆች ሞግዚትነት ሄደው ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልጅነትን አግኝተው ውሉድ ዘበጸጋ ተብለው የሚጠሩት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። ይህን ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ብዙ አስተማሪዎች እንዲኖሯቸው ሥርዓት ሠርታለች። በሥርዓቱም መሠረት ካሏቸው አስተማሮች የሚቀጥሉት ናቸው:-

፩ኛ. ወላጆች

፪ኛ. የክርስትና አባቶችና እናቶች

፫ኛ. የቀለም አባቶች ትምህርት ቤቶች

፬ኛ. የሰንበት ትምህርት ቤቶች

፭ኛ. የንስሐ አባቶች እየመደበች በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን እንዲማሩ ታደርጋለች።

አሁን ችግር ያስከተለው፣ ሁሉም በመመሪያው መሠረት ባለመከታተሉ፣ ልጆች ለችግር እየተጋለጡ ነው፤ በተለይ ባሁኑ ሰዓት መፍትሄ ላልተገኘለት በሽታ የሚዳረጉት የአስተዳደግ ጉድለት ያለባቸውና ሕገ እግዚአብሔርን ያልጠበቁ ናቸው።

በመንፈስ አስተዳደግና በሥነ ሥርዓት ተጠብቀው ባደጉ ወጣቶች ላይ ይህ ሁሉ ጉዳት አይደርስምና የልጆች አስተዳደግ፣ ማለት ልጆች ታንፀው ማደግ ያለባቸው፣

ሀ. በወላጆች

ለ. በጎረቤት

ሐ. በትምህርት ቤት

መ. በቤተ ክርስቲያን ነው።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ክፍሎች በልጆች አስተዳደግ ይዘት ደካሞች ከሆኑ የልጆች አቋምም የደከመና ተስፋ የሌለው ይሆናል፣ ማለትም ለራሳቸውም፣ ለወገናቸውም ለሀገራቸውም፣ ለፈጣሪያቸውም ተገዥና አገልጋይ አይሆኑም፤ በማጨስ በመጠጥ፣ በስርቆት በመሳሰሉት አሽከላዎች ይያዙና ባልተጠበቀ ዕድሜያቸው ይቀጫሉ።

በዚህ አደጋ ጊዜ ቀቢፀ ተስፋ ያለው ሐዘን ተማዘን፣ ልጆች የወንድ ማማችነት የእህትማማችነት ፍቅር እንዲኖራቸው፣ እንዲረዳዱ፣ እንዲፋቀሩ የታላቅና የታናሽ ደረጃቸው ምን ያህል እንደሆነ እንዲያውቁ እህት ዓለም፣ ወንድም ዓለም፣ እንዲባባሉ ተባብረው እንዲኖሩ ማድረግ መንፈሳዊ ሕይወት ነው።

ፈላስፋው ሲራክ እንዲህ ይላል በልቤ ያደነቅኳቸው ነገሮች ብዙ ናቸው ከብዙዎቹም በልጆች ደስ የሚለው ጥበብን ያገኘት የሚታዘዛትም ሰው የተደነቀ ነው መንፈሳዊ ጥበብን ያገኘ ልጅ ክቡር ነው። ነገር ግን እግዚአብሔርን መፍራት ከሁሉ ትልቃለች ሲራክ ፳፭፥፯–፲፩ ይላልና ለሁሉም ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል ለሁሉም ዕውቀት ነውና፣ ልጆችን በአካል፣ በአዕምሮ፣ በሃይማኖት አንጾ ማሳደግ የሁሉም ድርሻ ይሁን።

አባ ቁርሎስ

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የሰሜን ወሎና ዋግሕምራ

የአህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ✣

# «ዮም ተወልደ መድኅኔ ዓለም - ዮም ተወልደ ክሣቴ ብርሃን»

ከአባ ገሪማ ሊቀ ጳጳስ
የብፁዕ ወቅድስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤትና የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊ።



አምላክ ሰው ሁኖ በሥጋ ተገልጦ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዘመን ስንመለከት «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር...ልጁን ላከ» የሚለውን የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ዘይቤ ያመለክተናል (ገላ.፬፥፬)። ያ ዘመን አይሁድ የአምላካቸውን ተስፋ በመጠባበቅ የነበሩበት፣ ሮማውያን ቅኝ ገገሮች ከሥጋትና ከጦርነት ዐርፈው በሰላም የገዙበት፣ የሮማውያን ቅኝ ግዛቶች ተጠቃለው ዓለም ተብለው የተጠሩበት፣ የግሪክ ቋንቋ ዳብሮ በሁሉም ዘንድ እንደ ብሔራዊ ቋንቋ የሆነበት ለሁሉም የበጀ ጊዜ ነበር። (ሉቃ.፪፥፩–፫)

ያ ዘመን፣ ሙሴ በኦሪት የጻፈለት፣ ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት፣ ሱባኤ የተቆጠረለት፣ ጊዜው ደርሶ በጊዜው ጊዜ ሰውን ለማዳን በግብረ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ሰው ሁኖ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በዳዊት ከተማ ቤተ ልሔም ምድረ ኤፍራታ የዛሬ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የተወለደበትና የሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ» በማለት በአንድነት የዘመሩበት ዓመተ ኩነኔ፣ ዓመተ ፍዳ ያከተመበት፣ ዓመተ ምሕረት የተጀመረበትና የታወጀበት በመሆኑ የቅዳሴ፣ የውዳሴ፣ የዝማሬና የይባቤ ወቅት ነበር።

ያ ወራት በሌሊት መንጋቸውን በሜዳ ሲጠብቁ ያድሩ ለነበሩ እረኞች የጌታ መልአክ የታየበት፣ የክብር ብርሃንም የበራበት ወቅት ስለ ነበር ብርሃኑን ከማየታቸው የተነሣ ያደረባቸው የፍርሐት ስሜት እንዲወገድ የእግዚአብሔር መልአክ «አይዟችሁ አትፍሩ ለሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ደስታ የሚሆን መልካም ዜና ይገርላችሁ መጥቻለሁ። እነሆ ዛሬ በዳዊት ከተማ በቤተ ልሔም ምድረ ኤፍራታ መድኅን ክርስቶስ ተወልዷልና ደስ ይበላችሁ» አላቸው። (ሉቃ.፪፥፲–፲፩)

እነሆ አምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን በተፈጸመና ሕዝቡ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ በወጣ ጊዜ ቅድስት ድንግል ማርያምን ከገሊላ አውራጃ ከናዝሬት ከተማ ወደ ይሁዳ አውራጃ ወደ ዳዊት ከተማ ቤተ ልሔም ምድረ ኤፍራታ ሊያመጣት የቻለው የአውግስጦስ ቄሣር ልዩ ትእዛዝ መሆኑ ግልፅ ነው። (ሉቃ. ፪፥፩–፫)

አውግስጦስ ቄሣር ካመጣቻው የአመራር ለውጦች አንዱ የግብር አከፋፈል ትክክለኛ እንዲሆን የግዛቱ ሕዝብ እንዲቆጠር ማሰቡ ነበር። ይህ ዓይነቱ የሕዝብ ቆጠራ ቀደም ሲል የታቀደ ቢሆንም አምላክ ሰው ሁኖ እስከሚወለድ ድረስ ሳይሠራበት ቆይቶ ቅድስት ድንግል ማርያምን ወደ ቤተ ልሔም ሊያመጣት ምክንያት መሆኑ ለትንቢቱ ፍጻሜ ምልክት ሁኖ ተገኝቷል።

አምላክ ሰው ሁኖ የመወለዱ ተስፋ አስቀድሞ የተነገረለት አዳኝ መሆኑንና እግዚአብሔር በዘመነ አበው፣ በዘመነ ኦሪት ለሕዝቡ የሰጠውን የተስፋ ቃል የፈጸመውም በዚሁ ዘመን መሆኑ ነው። ይህም የአምላክ ሰው ሁኖ መወለድ በመካከላቸው ተወልዶ ላደገው ለእስራኤላውያን ድኅነት ብቻ ሳይሆን ለመላውም ዓለም ነው።

እግዚአብሔር ሰውን ስለወደደ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷም ነፍስን ነስቶ ሰው ሁኖ እንዲወለድና ዓለምን እንዲያድን አንድ ልጁን ወደዚህ ዓለም እንደላከው በቅዱስ መጽሐፍ በብዙ ቦታ ተጽፎ ይገኛል።

በዚያ ዘመን የነበሩ መናፍቃን ወይንም ክፉ አድራጊዎች «ክፋት የሚመነጨው ከግዙፉ ዓለም ጋር በሚደረገው ግንኙነት ስለሆነ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ከቶ ሰው ሊሆን ወይንም የሰብአዊነት ባሕርይ ሊኖረው አይችልም» ከማለታቸውም ጋር «ለሞራል አቋምም ሆነ ለሌላው ሰው ፍቅርን ማሳየት ከደኅንነት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም» ይሉ ስለ ነበር ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በአንደኛ መልእክቱ በምዕራፍ አራት ከቁጥር ሰባት እስከ አሥራ ሁለት ድረስ «ወዳጆች ሆይ! ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ እርስ በርሳችን እንፋቀር፣ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያፈቅር ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፣ እግዚአብሔርንም ያውቃል። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ እግዚአብሔርንና ሰውን የማያፈቅር ሁሉ እግዚአብሔርን አያውቅም። በልጁ ሕይወትን እንድናገኝ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። በዚህም የእግዚአብሔር ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ ለእኛ ተገልጧል። ፍቅርም ማለት እንደዚህ ነው፣ እኛ እግዚአብሔርን ስለወደድነው ሳይሆን እርሱ ስለወደደንና ኃጢአታችንን እንዲደመስስ ልጁን ስለላከልን ነው።

ወዳጆች ሆይ! እግዚአብሔር ይህን ያህል ካፈቀረን እኛም እርስ በርሳችን መፋቀር ይገባናል። እግዚአብሔርን ያየው ማንም ሰው የለም። እኛ እርስ በርሳችን ብንፋቀር እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል። ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ይሆናል» ይላል።

የምሥጢረ ሥጋዌው መሠረታዊ ትምህርት ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ መሆኑን ከልብ በማጤን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዐለ ልደት፣ በይቀጥላልም በዐለ ጥምቀቱንና አስተርእዮቱን ማክበር የሚገባን «ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም፣ ዮም ተወልደ ክሣቴ ብርሃን» በማለት እግዚአብሔርን በማመስገን የተቸገሩ ወገኖችንም በመርዳት መሆኑ የእምነት ግዴታ ይሆናል። ✣

www.ethiopianorthodox.org

# ሠሠግደፊ ፀሮ

ይህ ዓምድ መናፍቃንና አጽራረ ቤተክርስቲያንን የሚያጋልጡ ጽሑፎች የሚቀርቡበት የእመቤታችን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት አማላጅነት፣ ...ተራዳኢነት የሚተነተንበት፣ ይሆናል።

በዚህ ዓምድ የመስከረም እትማችን መልአከ ገነት ገብረሥላሴ በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አርዮሳውያንና የሉተር ተከታዮች በሚያስነሱዋቸው የኑፋቄ ጥያቄዎች ዙሪያ «ምሥጢረ ሥጋዌ» በሚል ርእስ ሰፊ ትምህርት አቅርበ ውልን ነበር። ለአሁንም ካቶሊካውያንና ጆሆቫዎች በምሥጢረ ሥላሴና ምሥጢረ ሥጋዌ ላይ የሚያነሱዋቸውን የተሳሳቱ አመለካከቶችን በማጋለጥ ሰፊ ትምህርት እንሆ ይሉናል።

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እና በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መካከል፣ በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ ልዩነት ተፈጥሯል። እርግጥ ልዩነቱ የመጣው ልዮን የሚባል ጳጳስ ተራቀቅኩ ብሎ ፊቃድ እና ባሕርይ ለየን አለ። የእስክንድርያ ሊቃ ጳጳስ ዲዮስ ቆሮስም፣ የለም ይኸማ እነ አትና ቴዎስ እነ ቅዱስ ቄርሎስ አንድ ባሕርይ ነው ያሉ፣ ሔዋርያትም አንድ ባሕርይ ነው ያሉ ይኸን አልቀበልህም አለው። አለቃህ ነው አሉት አለቃዩ ቢክድ እኔ አልክድም አለ። ሰባት ኤጲስ ቆጶሳት ከዲዮስቆሮስ ጋር ተሰደዱ፣ ያች ብርክልያ የምትባል ሴት (የመርቅያል ሚስት) ጥርሱን አስመትታ ጥርሱን አወለቀችው፣ መከራ ተቀብሎ «ተአማኒ በእግዚአብሔር» ብሎ በሃይማኖቱ አበው ያነሳዋል። ያ የተሰበረው ጥርሱ ዛቲ ይእቲ ፍሬ ሃይማኖትነ ብሎ ለእስክንድርያ ምዕመናን ልኮላቸው እንደ ፋና እያበራላቸው ይኖር ነበረ።

ስለዚህ በልዮንና በዲዮስቆሮስ ተለያየ እንጂ ከዚያ ቀደም ከ፬፻፶፩ ዓ.ም በፊት ሁለት ባሕርይ የሚል የለም። በመጽሐፍ ቅዱስም የለም። ነፍስ እና ሥጋ ሁለት ባሕርይ አይባሉም። መለኮት እና ሥጋም ሁለት ባሕርይ አይባልም አንድ ሆነው ይሠራሉ። አሁን እኛ ስንጾም ስንሰግድ፣ ስንጸልይ፣ ይኸ የነፍስ ሥራ ስንሠራ በሥጋ ነው የምንሰ ግደው፣ አብሮ ሥጋም ይሰግዳል ይጾማል፣ ይጸልያል፣ ስንበላም፣ ስንጠጣም የሥጋ ብቻ አይደለም «እስመ ነፍስ ተሐድር በደም» እንዲል የበላነው፣ የጠጣነው ደም ይሆናል። በዚያ ነፍስ አድራ አንድ ሰው ይባላል እንጂ «ኢይትረከብ ሕላዌ ዘእንበለ አካል ወአካልሂ ኢትረከብ ዘእንበለ ሕላዌ» ባሕርይ

## ሕጌን በልቦናቸው አኖራለሁ

ያለ አካል፣ አካል ያለ ባሕርይ አይገኝም፣ ባሕርይ ሁለት ካለ አካልም ሁለት ነው ያሰኛል። ስለዚህ ነው ክርክሩ የነበረ አንድነቱ እንደ ነፍስና ሥጋ ነው። ሰው አንድ አካል አንድ ባሕርይ ከተባለ (ነፍስና ሥጋ አንድ አካል ከተባለ) መለኮት እና ትስብእትም አንድ ነው መለያየት የለም።

መለኮት የብቻው ሥራ ትስብእትም ደግሞ የብቻውን ሥራ ይሠራል አይባልም። ይህ ሁለት አካል አሥኙቶ በዚህ ነው የተወጋገዙ።

ስለዚህ እኛ አንድ ነው የምንል ሥጋም አምላክ ሆኖአል የአምላክ ሥራን ይሠራል። ቃልም ሰው ሆኖአል የሰውነትን ሥራ ይሠራል። ታመመ፣ ሞተ የሚባል ማነው? ብትለው መልስ አያገኝም።

ታመመ ሞተ እሚባል ሥጋ ነበረ። የሥጋ ገንዘብ ለመለኮት ሆኖ መለኮት በሥጋ ታመመ መለኮት በሥጋ ሞተ፣ የሥጋን ገንዘብ ገንዘብ አደረገ፣ አንድ ስለሆነ። ዲዮስቆሮስ ወደ ሠርግ ቤት የተጠራ ማነው? አላቸው፣ እነዚያም ሲመልሱ ትስብእት ነው አሉት፣ ውሃውን ጠጅ ያደረገ ማነው? አላቸው፣ እነዚያም ሲመልሱ መለኮት ነው አሉ። እኽ! አሁን የተጠራው ትስብእት ነው ብላችሁኝ? አሁን ደግሞ ውሃውን ጠጅ ያደረገ መለከት አላችሁኝ መልካም።

«ዘዕውሩ ተወልደ» ዓይነ ሥውር ሆኖ የተወለደውንስ ያዳነው ማነው? አላቸው እነዚያም ሲመልሱ መለኮት ነው አሉ። ዲዮስቆሮስም፣ ለመለኮት ምራቅ አለው? ሲላቸው አፋቸው ተያዘ። ስለዚህ አንድ ሆኖ ሥራ ይሠራል እንጂ መለያየት የለም።

ይህ በምሥጢረ ሥጋዌ ያለን ልዩነት ነው። በምሥጢረ ሥላሴም እኛ ኦርቶዶክሳውያን መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሠረጸ ነው ብለን የምናምነው በካቶሊካውያን ዘንድ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ «ከአብ ከወልድ ነው የሠረጸው» ብለው የሚያስተምሩት እንደዚህ ያለው ከየት ነው ያገኙት? ቢባል፣ መነሻ ሐሳቡ ከየት እንደሆነ አይታወቅም።

ሠለስቱ ምዕት ያሉት መንፈስ ቅዱስ «ዘሠረፀ እምአብ» ከአብ የሠረፀ (የወጣ) ነው እንጂ «ወእም ወልድ» ከወልድም ሠረፀ አላሉም። እነሱ «መንፈስ ወልዱ» የልጁ የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ ካለ ከወልድም ሠረፀ (ወጣ) ያሠኛል ብለው ፈለሰፍን ብለው ነው እንጂ እስትንፋስ የሚገኝ ከልብ ነው፣ ከቃል አይደለም የሚወጣ። ነገር ግን ቃልም ከእስትንፋስ አይለይም፣ እስትንፋስም ከቃል አይለይም፣ ልብም አይለይም። አብ ልብ፣ ወልድ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ፣ ይለዋል። ሁለቱ ቃልና እስትንፋስ ከልብ ነው የሚገኙ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠረፀ ማለት እስትንፋስ ሆነ ማለት ነው።

እስትንፋስ ከልብ የሚወጣ እንደ መሆኑ መጠን እኛ «ዘሠረፀ እም አብ» ከአብ የወጣ ብለን እናምናለን። እነሱ ደግሞ በሕልውና የሚገኝ ዘቡበትን መገኛ አረጉት። ስለዚህ የእነሱ አካሄድ ስሕተት ነው።

ሌላው የማነሳው ጥያቄ መናፍቁ አርዮስ በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕ.፰ ቁጥር ፳፪ «ትቤ ጥበብ ፈጠረኒ እግዚአብሔር» በሚል አንቀጽ ምክንያት የወልድ የባሕርይ አምላክ ነትን ክዷል። ይህንን የተሳሳተ ትርጉም ይዘው በተለይ አርዮሳውያን (ጆህባውያን) ፈጥሮ ፈጠረበት» በማለት ብዙ ሰዎችን እያሳሳቱ በመሆኑ አርዮስ የተሳሳተበት፣ የትርጉም ዘይቤ እና የጥቅሱ ትክክለኛ ትርጉም ሰፋ አድርጎ መረዳት ያስፈልጋል። አርዮስ ፈጥሮ ፈጠረበት ሲል ዓለም ሳይፈጠር የነበረውን ያገኘው መስሎት ስሕተት ላይ ወደቀ፣ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ (ዘፍ.፩፥፩) አለ እንጂ «በቀዳሚ ገብረ ወልደ» በመጀመሪያ ወልድን ፈጠረ አላለም።»

«በቀዳሚ ገብረ ሰማየ ወምድረ» በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፣ እግዚአብሔር የሚባሉ ሦስቱም ናቸው። እግዚአ ብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እግዚ አብሔር ነው። ወይም አብ እግዚ አብሔር፣ ወልድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። «ፈጠረኒ» አለ ኋላ ፍጡር ሥጋን መዋሐዱ አስቀድሞ በልበ ሥላሴ ስለታወቀ፣ እግዚአብሔርነቱ ፍጡር ሥጋን ፈጠረ፣ ማለት ሥጋን ሦስቱ ይፈጥሩታል (ሥጋ ማርያምን) ለአብ ሲሰጥ «ገብረ አብ መቅደሰ ለወልዱ»

ለልጁ ማደሪያ (ሥጋን) ፈጠረ ይላል።

ለወልድ ሲሰጥ «ወኢተሳተፎ መኑሂ በፈጢረ ሥጋሁ» ሥጋውን በመፍጠር ማንንም አልተሳተፈውም (አልተራዳውም) ይላል።

ለመንፈስ ቅዱስ ሲሰጥ «ወገባሪሁ ለውእቱ ሥጋ መንፈስ ቅዱስ እስመ ውእቱ ቀብዖ ተዋሐደ ቦቱ አምላክ ቃል ወአናሚሁ መንፈስ ቅዱስ» ብሎ ለሦስቱ ይሰጣል። አርዮስ ሥጋን መፍጠርን ለአብ ብቻ ሠጥቶ «ፈጠረኒ እግዚአብሔር» አለ እግዚአብሔርነቱ ፈጠረኝ ከፍጡር ሥጋ ጋር አዋሐደኝ ማለት ነው እንጂ «ፈጠረኒ አብ» አብ ፈጠረኝ አላለም። ፈጠረኒ አብ አብ ፈጠረኝ ብሎ ቢሆን፣ ይኸ የሦስትነት ነውና፣ የአብም አጻፋ ወልድ ነውና በወልድ ነቱ ፈጠረ አላለም። እግዚአብሔር ደግሞ የሦስትነት ስም ነውና ሦስቱን ሥጋን እንደ ፈጠሩ ለማጠየቅ «ትቤ ጥበብ ፈጠረኒ እግዚአብሔር መቅደመ ኵሉ ተግባሩ»። ከንጹሐ ጠባይ፣ ከልጅነት፣ አስቀድሞ ጥበብ እግዚአብሔር ፈጠረኝ አለች ምሳሌ ፰ ቁጥር ፳፪ «ተግባሩ» የተባሉት ምዕመናን ናቸው።

ለምእመናን ምግባር ትሩፋት መሥራትን ፍጡር ሥጋን ተዋሕዶ ይኸንን በሥጋው ፍጡር የሥጋ ፍጡርነት ከወልድ ጋር የተዋሐደው የሥጋ ፍጡረነት አስቀድሞ በልበ ሥላሴ ስለታወቀ ነው። «እምከርሥ ስሕቱ ወነበቡ ሐሰተ» በማኅፀን ሳሉ ሳቱ፣ ሐሰትን ተናገሩ» ያለውን ንባብ ይመስላል።

እነዚህ በማኅፀን ያሉ ተፈጥረው ሐሰት መናገራቸውን በልበ ሥላሴ ስለታወቀ ነው። ወልድም ፍጡር ሥጋን ተዋሕዶ ለምግባር ለትሩፋት መሪ መሆኑ አስቀድሞ በልበ ሥላሴ የታወቀ ነው።

እንዲያውም «እምቅድመ ዓለም ነበረት በሕሊና አምላክ» እመቤ ታችን አለም ሳይፈጠር በሕሊና አምላክ ነበረች ይላል። ይኸን የመሰለ አስቀድሞ የሚነገረው፣ እስከ ምጽአት የሚሠራ ሁሉ በሥላሴ ዘንድ የታወቀ በመሆኑ ነው። ፈጣሪ፣ ፍጡር ሥጋን ለመወሐዱ አስቀድሞ በሥላሴ ዘንድ ስለታወቀ «ፈጠረኒ እግዚ አብሔር» ለሰው ልጅ ለንጽሐ ጠባይዕ፣ ለልጅነት፣ ፍጡር ሥጋን አዋሐደኝ አለ።

«ኢይቤ ፈጠረኒ አብ አላ ይቤ ፈጠረኒ እግዚአብሔር» አብ ፈጠረኝ ብሎ ቢሆን በአምላክነቱ ፈጠረው ያሰኝ ነበርና እግዚአብሔር አለብህ ብለውታል። እግዚአብሔር የሦስቱ ስም ነውና ሥጋን ሦስቱ ፈጥረውታል ማለት ነው። ጥበብ የሚለው ቃል ማንን ነው የሚተረጉመው ቢሉ፣ ወልድን ጥበብ ይለዋል «ጥበቢሁ ለእግዚአብሔር» የእግዚአብሔር ጥበቡ ይለዋል። (፩ቆሮ.፩፡፳፬)።

ጥበብ ከልብ ተገኝቶ በልብ እንዲኖር፣ እርሱም ከአብ ተገኝቶ በአብ ሕልው ሆኖ ይኖራልና። ቃል ይለዋል ቃል ከልብ ተገኝቶ በልብ እንዲኖር ወልድም ከአብ ተገኝቶ በልቡ በአብ ይኖራል ዝም ቢባልም ውስጥ ለውስጥ ይናገራል። (ዮሐ.፩፡፩)።

«ሕሊናሁ ለአብ» የአብ ሕሊናው ይለዋል። (ትምህርተ ኅቡአት) ሕሊና ከልብ ተገኝቶ በልብ እንዲታሰብ እሱም ከአብ ተገኝቶ በአብ ሕልው ሆኖ ይኖራልና። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተለያይተው አይሠሩም። እስትንፋስ ከቃል አይለይም፣ ልብም ከቃል ከእስት ንፋስ አይለይም። እስትንፋስም፣ ከልብ ከቃል አይለይም።

ሌላው ጥያቄ በኤርምያስ ምዕራፍ ፴፩ ቁጥር ፴፫ ላይ «ሕጌን በልቦናቸው አኖራለሁ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆና ቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል» ብሏልና። ከዚህም የተነሣ አንድ አንድ ሰዎች ግራ ይገባቸዋል። በመሠረቱ አሁንም ሕግ የሚሠራው በልብ ታስቦ ነው የቀደመው ሥርዓተ ሥጋ ነው። ሕጉን የሚጠብቁ በድንጋይ ከመወገር፣ ከመገረፍ ያድናቸዋል እንጂ፣ ገሐነም ከመውረድ አያድና ቸውም ነበር። ዛሬ ግን አማናዊ ሆኖአል። ሕግን ከጠበቅን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንጂ ወደታች (ወደ ገሃነም) አንወርድም።

ይህ አባባል ከታቦት (ከጽላት) ጋር ግንኙነት አለው? ወይስ የለ ውም? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ታቦት ደግሞ ታቦት ዘዶር፣ የብርሃን ታቦት፣ ኢየሩሳሌም ሠማያዊት፣ መንጦላዕተ ብርሃን፣ መንበረ ብርሃን፣ ከ፳፬ቱ አጠንተ መንበሩ ካህናተ ሰማይ የብርሃን ታቦት አለች (ራእይ ዮሐ.፲፩፡፲፱)። ያችን ለሙሴ በደብረ ሲና አሳየው።

«በከመ አርአይኩከ አርአያሃ ግበር ከማሁ» ይህችን ታቦት አስመስለህ ጽላተ ሙሴን ሥራ፣ (ዘጸ.፳፫፡፱) አለው። በሙሴ ጽላት ደግሞ የእኛ ጽላት፣ ያ ዓሠርቱ ቃላት ተጽፈውበት ነበር። ያ በብሉይ በአንድ ገጽ ነበር የሚያምኑ። ዛሬ የእኛ ጽላት ደግሞ በሐዲስ ኪዳን አልፋ ተብሎ ይጻፍበታል።

አ – አብ

ል – ወልድ

ፋ – መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው።

ከላይ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይሳላሉ።

ቀጥሎ እመቤታችን ቀጥሎ ጻድቅም፣ ሰማዕትም ቢሆን ይቀ ረጻል። ሦስት አካላት አንድ አምላክ ብለን ነው የምናምነው። እንጂ እንደ አይሁድ አንድ ገጽ ብለን አናምንም። በታቦት ዘዶር የሙሴ ጽላት፣ በሙሴ ጽላት የሐዲስ ኪዳን ጽላት ተተክቷል። ✣

መልአከ ገነት ገ/ሥላሴ



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ሃይማኖት



ብጹዕ አቡነ መርሐ-ክርስቶስ የትግራይ ሃገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

መግለጫ:- ይህ ጽሑፍ ሃይማኖትን መልመጃ ትምህርት ነው፡ ትምህርቱ የልጆችን አእምሮ፡ ፈጣሪን ለማወቅና ለማመን ያነቃቃል፡ ልብ ያስደርጋል፡ የሃይማኖትን ፍቅርና ትዝታ ያሳድራል።

ትምህርት አሰጣጡ ይቀጥላል ይኸው:-

ሀ. ልጆች – ሃይማኖትን ተለማመዱ፡
ሃይማኖት ያድናልና፡

«ያመነ እና የተጠመቀ ይድናል» እንዳለ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (ማር.፲፮፡፲፮ ተመልከቱ)

አስታውሱ ዕወቁ

ልጆች:- ታውቃላችኹን?
ማን ወለዳችኹ?
ማን እሳ ፈጠራችኹ?

ልጆች:- ሃይማኖት አላችኹን፡
በማን ታምናላችኹ፡
ማንን እሳ ታመልካላችኹ፡
ከእግዚአብሔር ምን ተስፋ አላችኹ፡
እግዚአብሔር ምን ይሰጣችኋል፡

ልጆች አሁን ቀጥሎ ነገርን አውቃችኋል።

እንግዲህ ይህን የተማራችኹን በግጥም ቃላት ዘምሩት፡

## ለ. መዝሙር

አባት እናታችን ወለዱን፡
እግዚአብሔር ፈጠረን፡
በእግዚአብሔር እናምናለን፡
እናመልካለን እግዚአብሔርን።
ከእግዚአብሔር አለን ልጅነት፡
አለን በረከት፡
አለን የዘላለም ሕይወት፡

**ጥንተ ትምህርት ዘሃይማኖት**
ለአዳጊ ሕፃናት
አባ መርሐ ክርስቶስ ሊቀጳጳስ

## ክፍል ሁለት

ባለፍናቸው ክፍሎች ሃይማኖትን ከቃል ተምረናል፡ በግጥም ዘምረናል፡ አሁን ደግሞ ከቃል የተማር

### መልስ ስጡ

ልናውቅ ልንማር ነው አሁን፡
አባት እና እናታችን
የፈጠረንማ እግዚአብሔር ነው፡
እግዚአብሔር ፈጠረን።

አዎን አለን ሃይማኖት፡
በፈጣሪ በእግዚአብሔር፡
እግዚአብሔርን እናመልካለን፡
ልጅነት፡ በረከት፡ የዘላለም ሕይወት፡
ልጆቹ ያደርገናል፡ ይባርከናል፡
የዘላለም ሕይወት ይሰጠናል።

ነውን የሃይማኖት ነገር በዚህ ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱስ እንማረዋለን፡

### ሀ. አባት እና እናታችን ወለዱን

ዕወቁ ተማሪዎች:- አባት እና እናታችን ሊወልዱን የቻሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ስለፈቀደላቸው ነው፡ መውለዱን በረከት አድርጐ ሰጥቷቸዋልና ይህን ያስረዳል መጽሐፍ ቅዱስ፡ (ዘፍ.፩፡፳፰)

ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፳፰ እንዲህ ይላል:- እግዚአብሔር ባረካቸው፡ አላቸውም «ብዙ ተባዙም ምድርንም ሙሏት»

መዝ.፻፳፯፡፫:- እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ጸጋ ናቸው፡ የኾድም ፍሬ የእርሱ ስጦታ፡ ሲል ያስተምራል መጽሐፍ ቅዱስ፡

ተጨማሪ ትምህርት:- ልጆች ለወላጆቻችኹ ታዘዙ፡ በጌታችን ይህ ተገቢ ነውና። እናንተም አባቶች ልጆቻችኹን አታስቆጡ፡ በእግዚአብሔር ትምህርት ኦንድጉ፡ በምክሩም ገስጹ እንጂ (ኤፌ.፮፡፩–፬)።

### ለ. እግዚአብሔር ፈጠረን

ተማሪዎች:- ሰዎች እኛ ማን እንደፈጠረን ማወቅ አስፈላጊአችን ነው፡ እና የፈጠረን እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር የፈጠረን ለመኾኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል:-

ኢሳ.፵፭፡፲፩–፲፪ የእስራኤል ቅዱስ ሰሪውም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ «…እኔ ምድርን ሰርቻለኹ ሰውንም በላይዋ ፈጥሬአለኹ» ብሏል።

መዝ.፺፪፡፫:- «እግዚአብሔር አምላክ እንደኾነ ዕወቁ፡ እርሱም ፈጠረነ እኛም አይደለንም» ብሏል።

ኤፌ.፪፡፲:- እኛ ፍጥረቱ ነንና በክርስቶስ ኢየሱስ የፈጠረን እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ላዘጋጀው ለበጎ ምግባር (የፈጠረን)፡ ብሏል።

ዘፍ.፩፡፳፯:- «እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፡ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው» ብሏል መጽሐፍ ቅዱስ። ተጨማሪ ጥቅስ ዘፍ.፩፡፳፯፡ ፭፡፩ ተመልከቱ።

የሐዋ.፲፯፡፳፯:- «እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ የሰውን ወገኖች ኹሉ ካንድ ፈጠረ» ብሏል።

አማኝ ንጉሥ ዳዊት:- «እጆችኽ ሰሩኝ፡ አዘጋጁኝ፡ አንተ ፈጠርኸኝ፡ እጅኽንም በላዩ አደረግኽ» ብሏል በመዝሙሩ። (መዝ.፻፴፰፡፭ ተመልከቱ)

ክብር እንስጠው:- (በግእዝ) «ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ–ናምልኮ» (ባማርኛ) እናመልከው ዘንድ እኛን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር ክብር ይኹን (ክብሮ ይግባው)

(የቅዱስ ያሬድ ምዕራፍ የሚባለው መዝሙር)

## ክፍል ሦስት

### ሀ. በእግዚአብሔር እናምናለን

ልጆች ዕወቁ:- ከኹሉ ነገር በእግዚአብሔር ማመን ይበልጣልና ማመን ያስፈልገናል፡ «ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል» እንዳለ ዳዊት። (መዝ.፸፪፡፳፰)።

መጽሐፍ ቅዱስም በእግዚአብሔር ማመን እንደሚያስፈልገን እና እንደሚጠቅመን ያስተምራል።

መዝ.፳፰፡፴፪:- እግዚአብሔርን ፈልጉ ሕያዋንም ኹኑ፡

መዝ.፻፬፡፫–፬:- እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው፡ እግዚአብሔርን ፈልጉ ትድናላችሁ ኹል ጊዜ ፊቱን ፈልጉ» ብሏል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ:- «በእግዚአብሔር (በአብ) እመኑ፡ በእኔም እመኑ» ብሏል (ዮሐ.፲፬፡፩)።

ጳውሎስ ሐዋርያ:- «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙት ዘንድ አይቻልም፡ ወደ እግዚአብሔር የሚመጣስ እግዚአብሔር እንደ አለ፡ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንደሚሰጥ አስቀድሞ ያምን ዘንድ ይገባዋል» ብሏል ዕብ.፲፩፡፮።

ጴጥሮስ ሐዋርያ:- «ወይ እዜኒ ሃይማኖትክሙ ወተስፋክሙ ይኩን በእግዚአብሔር» ማለትም «አሁንም ሃይማኖታችኹና ተስፋችኹ በእግዚአብሔር ይኹን» ብሏል (፩ጴጥ.፩፡፳፩ ተመልከቱ)።

### ምክር ከመዝሙረ ዳዊት

መዝ.፴፩፡፳፬:- በእግዚአብሔር የምታምኑ ኹላችኹ ታገሡ ልባችሁንም አጽኑ።

### ለ. እግዚአብሔርን እናመልካለን

ሰዎች እኛ ፈጣሪአችን እግዚአብሔርን ማምለክ ይገባናል፡ ባዕድን ግን ማናቸውንም ቢኾን ማምለክ አይገባንም፡ አይጠቅመንምም።

ስለዚህ ባዕድን እንዳናመልክ ይከለክለናል፡ እግዚአብሔርን ብቻ እንድናመልክ ያዝዘናል፡ ያስተምረናል፡ መጽሐፍ ቅዱስ።

ዘጸ.፳፡፫:- ስንመለከት «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኹኑልኽ» ብሏል እግዚአብሔር (መዝ.፹፡፱)።

ዘዳ.፮፡፲፫:- «አምላክኽን እግዚአብሔርን ፍራ እርሱን አምልክ» ብሏል።

ዘዳ.፲፡፲፪:- «እስራኤል አሁንስ እግዚአብሔር አምላክ ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? እግዚአብሔር አምላክኽን ትፈራው ዘንድ፡ በመንገዱም ኹሉ ትኼድ ዘንድ፡ በፍጹም ልብኽ፡ በፍጹም ነፍስኽ፡ ታፈቅረው ዘንድና ታመልከው ዘንድ… ነው እንጂ» ብሏል።

ምእመኑ መስፍን ኢያሱ:- «አሁንም እግዚአብሔርን ፍሩ በፍጹምና በእውነተኛም ልብ አምልኩት። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» ብሏል።

በመጨረሻ አንድ መልአክ አስጠንቅቆ ሲናገር ታይቷል፡ ተሰምቷል።

ራእ.፲፬፡፲፭:- …የዘላለም ወንጌል ያለው መልአክ በሰማይ መካከል ሲበር አየኹ፡ በታላቅም ድምጽ «እግዚአብሔርን ፍሩ፡ ክብርንም ስጡት፡ የፍርዱ ሰዓት ደርሷልና፡ ስገዱለትም፡ ሰማይና ምድርን፡ ባሕርንና የውኃ ምንጮችን ለሠራው» አለ።

### ብጽዕና

– እግዚአብሔርን ለሚያመልክ ሕዝብ ብጽዕና ይሰጣል፡ መጽሐፍ ቅዱስ።

መዝ.፻፵፫፡፲፭:- «እግዚአብሔር አምላኩ የኾነ ሕዝብ ብጹዕ ነው» ይላል።

ጸሎት – በቃልኽ አጠንክረኝ፡ የዓመጽን መንገድ አርቅ ከኔ፡ በሕግህም እዘንልኝ፡ የእውነትኽንም መንገድ መረጥኹ፡ ፍርድኽንም አልረሳኹም፡ ምስክርኽን ተከትያለኹና አቤቱ አታሳፍረኝ፡ በትእዛዝኽ መንገድ ሩጫለኹ፡ ልቤን ባሰፋኽው ጊዜ (መዝ.፻፲፰፡፳፰–፴፪)።

## ክፍል አራት

### ሀ. ከእግዚአብሔር ልጅነት አለን

ሰዎች እኛ፡ እግዚአብሔርን ካመንነው፡ አምነንም ካመለክነው፡ እግዚአብሔር ልጆቹ ያደርገናል፡

www.ethiopianorthodox.org

በእግዚአብሔር የሚያምኑ እና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚኸዱ (የሚኖሩ) ሰዎች፣ የእግዚአብሔር ልጆቹ እንደሚኾኑ፣ ወይም የእግዚ አብሔር ልጅነት እንዳላቸው መጽ ሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ዘጸ.፬፥፳፪:- ...እግዚአብሔር እን ዲህ ይላል «እስራኤል የበኵር ልጄ ነው»

፪ቆሮ.፮፥፲፰:- ...አባትም እኾና ችኋለኹ፣ እናንተም ለእኔ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች ትኾኑል ኛላችኹ ይላል እግዚአብሔር፣ ኹሉን የሚገዛ።

፩ጴጥ.፩፥፫:- ...ይመስገን እግዚ አብሔር፣ የጌታችን የኢየሱስ ክር ስቶስ አባቱ፣ በምሕረቱ ብዛት የወለደን...።

ዮሐ.፩፥፲፪:- ለተቀበሉት ግን ሥልጣንን ሰጣቸው፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይኾኑ ዘንድ፣ በስሙ ላመኑ...።

፩ዮሐ.፫፥፩:- አብ የሰጠን ፍቅሩ እንደምን ያለ እንደኾነ ዕወቁ፣ የእግዚአብሔር ልጆች እንኾን ዘንድ፣ ሁነናልም።

ሮሜ ፰፥፲፬:- በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ኹሉ እነዚያ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና...። በማለት ያስረዳል መጽሐፍ ቅዱስ።

ምስጋና እናቅርብ በሐዋርያ ቃል

በምሕረቱ ብዛት የወለደን፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባቱ እግዚአብሔር ይመስገን። ፩ጴጥ.፩፥፫።

### ለ. ከእግዚአብሔር በረከት (ቡራኬ) አለን

ተማሪዎች ዕወቁ:- እኛን ልጆቹን፣ እግዚአብሔር ይባርከናል፣ እንደሚባርከንም መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ዘጸ.፳፥፳፬:- ስሜን በማሳስብበት ስፍራ ኹሉ ወዳንተ መጥቼ እባርክ ኻለኹ።

ዘኁ.፮፥፳፪–፳፯:- ...እንዲኹ ስሜን በእስራኤል ልጆች ላይ ያደርጋሉ። እኔም እባርካቸዋለኹ» ብሏል እግዚአብሔር። (ቁ.፳፯)

መዝ.፳፰፥፲፩:- እግዚአብሔር ሕዝቡን በሰላም ይባርካል፣

መዝ.፷፯፥፯:- እግዚአብሔር አምላካችን ይባርከናል፣ እግዚአ ብሔር ይባርከናል።

መዝ.፸፩፥፲፯:- «የምድር አሕ ዛብ ኹሉ በእርሱ ይባረካሉ» ብሏል (ዘፍ.፳፪፥፲፰) ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ «ያባቴ ቡሩካን» ብሏቸዋል ወገኖቹን። (ማቴ.፳፭፥፴፬)።

ምስጋና እናቅርብ ለባረከን

በሰማያት ባለው በመንፈስ ቅዱስ በረከት ኹሉ በኢየሱስ ክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባቱ እግዚአብሔር ይመስገን። (ኤፌ.፩፥፫)።

### ሐ. ከእግዚአብሔር ዘንድ የዘላለም ሕይወት አለን

ያመኑበት የሚያመልኩት ከእግዚ አብሔር ዘንድ የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ታውቋል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳ ልና እንዲህ ሲል:-

ዮሐ.፫፥፴፯:- ...በወልድ የሚያ ምን የዘላለም ሕይወት አለው፣

ዮሐ.፲፩፥፳፭–፳፯:- ኢየሱስም እንዲህ አላት፣ «እኔ ነኝ ትንሣኤና ሕይወት፣ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይኾናል፣ በሕይወት ያለ እና የሚያምንብኝ ኹሉ ለዘላለም አይሞትም»

ዮሐ.፭፥፳፬:- እውነት እውነት እላችኋለኹ ቃሌን የሚሰማ እና የላከኝን የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፣ ወደ ፍርድም አይኸድም፣ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሯል እንጂ፣

ማቴ.፳፭፥፵፮:- ...ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይኼዳሉ፣

ቈላ.፫፥፫–፬:- ...ሕይወታችኹም ከእግዚአብሔር ዘንድ ተሰውራለች ከክርስቶስ ጋር፣ ሕይወታችኹም ክርስቶስ በተገለጠ ጊዜ በዚያ ጊዜ እናንተም ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችኹ (ትታያላችኹ)

፩ተሰ.፬፥፲፭–፲፰:- አንብቡ፣ የመጨረሻውም...እንዲሁ ኹል ጊዜ ከጌታ ጋር እንኾናለን፣ ይላል። ✣

## የበግ ደበሎ ለብሰው ከሚመጡ እ;ታላዮች ተጠበቁ

በስምንተኛው ትእዛዝ ስርቆትን ይከለክላል

መስረቅም ማለት ማናቸውንም የሰውን ገንዘብ ሁሉ በግፍ፣ በግድ፣ በተንኮል፣ ወይም በማታለል መውሰድ ነው።

ከጸፈቀ ዱር፣ ከጕድጓዳ ምድር፣ እንደ አንበሳ እንደ ነብር ሸምቆ ተደብቆ የሚወስዱት አወሳሰድ የሰውን ገንዘብ በግድ መውሰድ ሲሆን፣ ደግሞ የሎሌ፣ የገረድ፣ የሠራተኛ፣ ደመወዝ ማስቀረት በግፍ መውሰድ ነው። (ያዕ.፭፥፬–፭)

እንዲሁም፣ ቤት ምሰው አጥር ጥሰው የሚወስዱት አወሳሰድ የሰውን ገንዘብ በተንኮል መውሰድ ሲሆን ደግሞ በመሸጥ በመለወጥ ጊዜ በቀጣፊ ሚዛን በዓባይ ቁና ደልሎ፣ አታሎ፣ የሰውን ሀብት መውሰድ ይህ ሁሉ መስረቅ ነው።

ከላይ እንደ ተመለከተው፣ ወሳኙ ሰው ተወሳኙ ገንዘብ በመሆኑ፣ አንዱ ያንዱን ገንዘብ በግፍ ወይም በስርቆት እንዳይወስድ ሕግ ከልክሏል።

ዛሬ ግን ገንዘብን ሳይሆን ሰውን የሚሰርቁ የሃይማኖት ሌቦች ተነስተው ሰውን ከልበ ሥላሴ ሳጥንነት ለመው ሰድ መንደር ለመንደር ሲዘዋወሩ ይታያሉ።

ሕግ እንዳያግዳቸው ወንጌልን እንሰብካለን ይላሉ፣ ፖሊስ እንዳይ ዛቸው በቀን ይሄዳሉ፣ የሰውን ከብት የሚወስዱ የገንዘብ ሌቦች ብዙ የስር ቆት ዘዴ እንዳላቸው ሁሉ፣ የሃይማ ኖትም ሌቦችም ሰውን የሚሰርቁባት ብዙ የክህደት ዘዴአላቸው።

ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣ — ጥቅምት ፲፩/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

## ሕግን ሁሉ ይፈጽም ዘንድ በዮርዳኖስ ተጠመቀ



በባህርየ መለኮቱ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው፣ ዓለማትን በባህርይ ሥልጣኑ ፈጥሮ የሚገዛ ልዑለ ባህርይ እግዚአ ብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ እንደየተፈጥ ሮው የሚመራበት፣ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት፣ ለፈጣሪው የሚገ ዛበት ሕግን ሠርቶለታል። (መዝሙር ፻፵፰፥፩–፲፬) በተለይም ለሰው ልጅ ተመራምሮ የማወቅ ለባዊ አእምሮን አድሎታል፣ በዚህም አምላካዊ ስጦታ ተመራምሮ በሕገ ልቡና ፈጣሪውን አውቆ ሲያመልክ ኖሯል፣ በስሕ ተትም (በኃጢአትም) ከፈጣሪው ከተለየ በኋላ ብዙዎች ከፈጣሪያቸው በመለየታቸው ወደ ፈጣሪያቸው ተመልሰው ለፈጣሪያቸው የሚገዙበት ሕገ ኦሪትን ሠራላቸው። (ዘዳግም ፭፥፯–፳፩) ቀጥሎም ይህንኑ መጽ ሐፋዊ ሕግ የሚፈጽሙና የሚያስፈ ጽሙ ነቢያትን አስነስቶ በነሱ አን ደበት ሕጉን አስተማረ። (ሉቃ. ፩፥፸፱፤ ሮሜ ፩፥፩–፪) በመጨረሻም ቀድሞ ለሰው ልጆች የሠራውን ሕግ በነቢያት ያናገረውን ትንቢት ይፈጽም ዘንድ ልዑል ባህርዩን ዝቅ አድርጎ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆነ። (ገላ.፬፥፬) ሠራዒ ሕግ እሱ፣ ፈጻሚ ሕግም እሱ እንደሆነ ለማጠየቅ በመዋዕለ ስብከቱ (በተራ ራው ስብከት) በኦሪትና በነቢያት ከተጻፉት ሕግጋት አንዲ እንደ ማትወድቅ በተለይ ቤተ አይሁድ (የሙሴን ሕግ ሊሽርብን፣ ብፁዓን ብፁዓን የሚል አዲስ ትምህርት አመጣብን) እያሉ በምታንጐ ራጉርበት ጊዜ ኦሪትና ነቢያትን ልፈጽም እንጂ ልሽራቸው የመጣሁ አይምሰላችሁ! በማለት ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በአምላክነቱ የሠራውን ሕግ በሰውነቱ ለመፈጸም መምጣቱን (ሰው መሆኑን) አረጋገጠ። (ማቴ.፭፥፲፯) በመሆኑም ፈጻሚ ሕግ ሆኖ በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ? ቸርነቱን በውዳሴ የገለፀው መተርጕመ መጻሕፍት ቅዱስ ያሬድ «እግርያም ዘተወልደ አፍቂሮ ኪያነ መጽአ ኀቤነ ዘነቢያት ሰበኩለነ በዮርዳኖስ ተጠምቀ ከመ.ይፈጽም ኩሉ ሕገ ወአስተርአየ ገሀደ!! ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ብለው የሰበኩልን እኛን ወዶ፣ ወደ እኛ መጥቶ ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው (ክርስ ቶስ) ሕግን ሁሉ ይፈጽም ዘንድ በዮርዳኖስ ተጠመቀ በግልጽም ታየ!! ብሏል።

እንግዲህ የሥጋዌውን በሥጋዌ ውም የፈጸመውን የቸርነቱን ሥራ (ጥምቀቱን) በእርሱ በተጠቀሰው በቅዱስ ያሬድ መዝሙረ ስብሐት መሠረትነት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ጥምቀት (፲፱፻፺፪ኛ ዓመት) እንመለከታለን። በቅድሚያ በሐዲስ ኪዳን የሚከበሩ በዓላት ሁሉ ጥንታቸው ብሉይ ኪዳን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፣ ማለት ትንቢት ሲነገርላቸው፣ ምሳሌ ሲመሰልላቸው፣ ሱባዔ ሲቆጠርላ ቸው፣ ኑረው ዘመኑ ሲደርስ በሥጋ ዌው አማናውያን ሆነው የተፈጸሙ ናቸው» በመሆኑም የጌታችን የመድኃ ኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆንና ከኃጢአት በስተቀር የሰውን ሁሉ ሥራ (ሕግ) መፈጸም በትንቢትና በምሳሌ ሲገለጽ የመጣ ነው (ዘጸ. ፲፰፥፲፰፣ ኢሳ.፯፥፲፬፣ ኢሳ.፶፫፥፱፣ ፩ጴጥ.፪፥፳፪–፳፫) በተለይም በዚህ ጽሑፍ ስለጥምቀተ ክርስቶስ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የአበውን ትውፊት መሠረት በማድረግ የጥምቀትን አከባበር ታሪኩንና አመጣጡን ባጭር ባጭሩ እንግለጸው። በትንቢትም ሆነ በትንቢቱ ፍጻሜ የጥምቀት በዓል መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የጥምቀትን በዓል የምታከብረው በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውንና አበው ያቆዩትን ሃይማኖታዊ ሥርዓት (ቀኖና) ሳታፋ ልስ ጠብቃና አስጠብቃ ከአበው የተረከበችውን ለትውልድ በማስተ ላለፍ ነው። በዚህም ዕውነተኛ ጥንታዊት ሐዋርያዊትና ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን መሆኗን አስመ ስክራለች። ከላይ እንደተገለጸው የጥምቀት በዓል ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ተነስቶ ልዩ ልዩ ብሔራዊ ትውፊቶች (ሥርዓቶች) እንደሚገለጹበት በግ ልጽ የሚታወቅ ነው። ይህንን ወደመጨረሻው እናመጣዋለን እና አሁን ክርስቶስ ሕግን ሁሉ ለመፈጸም በዮርዳኖስ ተጠመቀ ሲባል ለምን እንደ ተጠመቀ ለመግለጽ ወደ መሠረታዊው ትምህርት እንመለስ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት፣ ክርስቶስ በዮርዳኖስ የተጠመቀበት ምክንያት በዮርዳኖስ እንደሚጠመቅ ትንቢት ተነግሯል፣ ምሳሌ ተመስሏል፣ በዮርዳኖስ፣ የዕዳ ደብዳቤያችን በዲያብሎስ ተጥሎ ነበርና ያን ለመደምሰስ፣ አንድነቱን ሦስትነቱን ለመግለጽና በመጨረሻም

www.ethiopianorthodox.org

የመዳናችን ራስ እሱ ስለሆነ ተጠምቀን ልጅነትን (ድኅነተ ነፍስን) እናገኝ ዘንድ ሥርዓተ ጥምቀትን ሊጀምርልንና ሊባርክልን ነው።

በዚህም መሠረት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ መጠመቁን አራቱም ወንጌላውያን በአንድ ቃል ጽፈዋል፤ ሁሉም አንድ ዓይነት ስለሆነ ስለ ጥምቀቱ በማቴዎስ ፫ ያለውን ብቻ እንመልከት። በነቢዩ በኢሳይያስ ትንቢት መሠረት (ኢሳ.፵፥፫) መጥምቁ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ በይሁዳ ምድር እየሰበከ መጣ። ዮሐንስ ለእውነተኞች ባህታውያን ገዳማውያን ምሳሌ መሆኑ ምግቡና ልብሱ ምቾት፥ ልስላሴና ከጣዕም የተለዩ መሆናቸው ለፍጹም ገዳማዊነቱ ማስረጃዎች ናቸው።

ከዮሐንስ ትክክለኛ ትምህርት አሰጣጥና ከመልካም የመምህርነት አርአያው የተነሳ በዮርዳኖስ ዙሪያ ያሉ ሁሉ ወደ እርሱ እየመጡ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር።

በአንጻሩም ጻድቃን መስለው ኃጢአታቸውን ሰውረው ለጥምቀት ሳይሆን ጉዳዩን ለመከታተል የሚመጡ እንደ ነበሩ በዚሁ ክፍል ተገልጿል። በመሆኑም ዮሐንስ ደግ መምህር ነውና ለንስሐ የመጡትን ተቀብሎ ሲያጠምቃቸው ለክትትል ከክፉ ሥራቸው ጋራ የመጡትንም እንደ ግብራቸው እፉኝት ልጆች ከሚመጣው መቅሰፍት እንድ ትሸሹ ማን አመለከታችሁን በማለት በተንኮል መምጣታቸው እንደማይጠቅማቸው ይልቁንም እንደሚጎዳቸው በብዙ ምሳሌ መክሮና አስተምሮ ለንስሐ የሚያበቃ ሥራ እንዲሠሩ አስጠንቅቋቸዋል። በዚህም ጻድቅ በመምሰል ጽድቅ እንደማይገኝ በተንኮል ወደ ቤተ እግዚአብሔር ቢቀርቡ በበረከት ፈንታ መርገም የሚከተል መሆኑን መረዳት ነው።

ዮሐንስ በስብከቱና በጥምቀቱ እኔ ለጠጅ ብርሌን፤ ለልብስ ገላን እንዲያ ጥቡለት ለጌታ አማናዊ ጥምቀት የሚያበቃ የንስሐ ጥምቀት አጠምቃችኋለሁ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ በፊት የነበረው እርሱ ከእኔ ይበረታል። እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል... እያለ በሚያስተምርበት ጊዜ (ማቴ.፫፥፩–፲፪) መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሰዎች በደል ሳይሠራና የሚናዘዘውም ኃጢአት ሳይኖርበት የሰዎችን ሕግ ለመፈጸም ብቻ በዮሐንስ እጅ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ዮሐንስ ግን እኔ ባንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል እንጂ አንተ ወደኔ ትመጣለህን አለው ጌታ ግን «ሕድግ ምዕረሰ እስመ ከመዝ ውእቱ ተጽኅ ለነ ወይደልወነ ከመንፈጽም ኵሎ ጽድቀ» አንድ ጊዜስ ተው ይህ ለእኛ ተድላችን ነውና ጽድቅን፤ ትንቢተ ነቢያትን ልንፈጽም ይገባናል ብሎታል። የጌታ ትሕትና የዮሐንስ ክብር በዚህ ተገልጧል። ከዚህ በኋላ ዮሐንስ ፈቃደኛ ሆኖ ሊያጠምቀው ወደወንዙ ወረዱ፤ ጌታ ተጠምቆ ከውሃው ሲወጣ ሰማያት ተከፈቱ (ምሥጢራት ተገለፁ) አብ በደመና ሆኖ ይህ የምወደው የምወልደው በእርሱ ደስ የሚለኝ የባህርይ ልጄ ነው። ብሎ በመናገሩ፤ መንፈስ ቅዱስም በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ በማረፉ (በመቀመጡ) አንድነት ሦስትነት (ሥላሴ) ተገለጸ ማቴ. ፫፥፲፫–፲፯ በጥምቀት በዮርዳኖስ የተገለጸው አንድነት ሦስትነት ከዚያ በፊት በመጻሕፍት የተጻፈ ቢሆንም በግልጽ ያወቀው እንዳልነበረ ጎርጎርዮስ ገባሬ ተአምራት እንዲህ ሲል ገልጾታል።

«ከሰው ወገን ማንም አያውቃቸውም ነበር አብ በዮርዳኖስ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ ከመሰከረ፤ መንፈስ ቅዱስንም ከሰደደ በኋላ ነው እንጂ» ብሏል (ሃይ አበው ዘጎርጎርዮስ ም.፲፫/ክፍል/፩/ቁ.፱፥፲) በዮርዳኖስ የመጠመቁ ምሥጢር ትንቢቱን ምሳሌውን ለመፈጸም ነው።

ሀ. ትንቢት «አቤቱ ውሆች አዩህ አይተውህም ፈሩ ጥልቆችም ተነዋወጡ አይተውህም ጮሁ (መዝ. ፸፮፥፲፮) ባሕር አየች ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደኋላው ተመለሰ ተራሮች እንደ ኮርማዎች (ጊደሮች) ዘለሉ» (መዝ.፻፲፫፥፫–፬)።

ይህንኑ ቅዱስ ያሬድ ሲተረጉመው «ወተሀውከ ማየ ዮርዳኖስ እምግርማ መለኮት ወደንገፀ ኵሉ ኃይለ ሰማያት ወምድር» ከመለኮቱ ግርማ (ማስፈራት) የተነሳ የዮርዳኖስ ውኃ ተናወጸ የሰማያትና የምድር ኃይላትም ደነገጡ ብሎታል።

በበዓለ ጥምቀት ከሚነበበው የስንክሳር አርኬ (ሶበ ርእዩከ ቀለያት ደንገጹ ወፈርሁ ማያትኒ በርእስከ ፈልሁ) ጥልቆች አይተውህ ፈሩ ውኃዎችም በራስህ ላይ ፈሉ፡ ማለት ዘለሉ ይላል። ይህ ሁሉ የሚያስገነዝበን በትንቢቱ ፍጻሜ ማለት ጌታ በተጠመቀ ጊዜ ሰማየ ሰማያት እመቀ ዕመቃት የማይወስኑት አምላክ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በፍጡሩ እጅ ለመጠመቅ በዮርዳኖስ ወንዝ ቆሞ ሲያዩት ውኃው ተራራው ግርማ መለኮቱ ተገልጾላቸው ለክብሩ በሰው አዕምሮ የማይመረመር ልዩ ልዩ እንቅስቃሴ ማሳየታቸውን ነው።

ለ. ምሳሌ:- ብዙ ምሳሌዎች ተነግረዋል ተፈጽመዋልም ጥቂቶቹን ብቻ እንጠቅሳለን።

ዮርዳኖስ ከላይ ነቅዑ ሦስት ከታች ተገናኝቶ አንድ ይሆናል ይህም ጌታ በዮርዳኖስ ተጠምቆ አንድነቱን ሦስትነቱን እንደሚገልጽበት በምሳሌነቱ መገለጹን ሊቃውንት ያብራራሉ።

እስራኤል ዘሥጋ ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስትን እንደ ረሱ፤ እስራኤል ዘነፍስ (ክርስቲያኖች) በጥምቀት ገነት መንግሥተ ሰማያት ለመግባታቸው ምሳሌ ነው።

ኢዮብ፤ ንዕማን በዮርዳኖስ ተጠምቀው ከደዌ ሥጋ ተፈውሰዋል። ምዕመናን በክርስቶስ ስም ተጠምቀን ከደዌ ነፍስ ለመዳናችን ምሳሌ ነው።

እንግዲህ በዚህ መልክ የክርስቶስን ጥምቀት አብነት አድርገን ክርስቲያኖች ተጠምቀን የክርስቶስ አባላት ለመሆን የመጀመሪያው መግቢያ በር ነው። እኛ ስንጠመቅ ልጅነት እናገኛለን፤ ከኃጢአታችን እንነፃለን። (ህዝ.፴፮፥፳፭) መንግሥተ ሰማያትን? (ዮሐ.፫፥፭) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን መጠመቁ፡ ለአርአያ እንጅ ልጅነት አገኝበታለሁ አይል ቅድመ ዓለም የአብ የባህርይ ልጅ ነው። ሥርየተ ኃጢአት አገኝበታለሁ አይል ንጹሐ ባሕርይ ነው (፩ጴጥ.፪፥፳፪–፳፫) በተለይ በዮርዳኖስ መጠመቁ የዕዳ ደብዳቤያችንን ለመደምሰስ እንደ ሆነ ከላይ ተገልጿል። ስለ ዕዳ ደብዳቤው ወሰጠጠ መጽሐፈ ዕዳሆሙ ለአዳም ወለሔዋን ባለው ትርጓሜ ይመለከቷል።

ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ደምሰሰ ለነ መጽሐፈ ዕዳነ በሥርዓቱ...» በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰልን ያለው በዲያብሎስ አስገዳጅ ትእዛዝ የተጻፈውን የተንኮል ጽሑፍ በጥምቀቱና በመስቀሉ መደምሰሱን ለመግለጽ ነው።

ለማጠቃለል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጠመቅ ወደ ዮርዳኖስ የወረደበትን ሥርዓት መሠረት በማድረግ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታቦታትን የዮርዳኖስ ምሳሌ ወደሆነ ወንዝ (ባህር) ይዛ በመውረድ ሥርዓቱን ትፈጽማለች። እውነተኛ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የሚያሰኛትም ይህ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮችም በባሕረ ጥምቀቱ የሚፈጸመውን ሥርዓት ከፈጸሙ በኋላ ከባሕረ ጥምቀቱ እስከ መንበረ ታቦቱ ድረስ ታቦቶቻቸውን አጅበው ካህናቱ በይባቤ፤ ወጣቱ በሆታ፤ ሴቱ በእልልታ፤ አዛውንቱ ባጀብ፤ የሚያሳዩት ሃይማኖታዊ ሥርዓት (ተድላ ደስታ) ይህ ለእኛ ተድላችን ነው ጽድቅን ልንፈጽም ይገባናል ያለውን የክርስቶስ ቃል ያሳስበናል። በመሆኑም ነው ከመንፈሳዊ ደስታቸው የተነሳ ሴቱም ወንዱም ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ በሚል ባህላዊ ዘይቤ ክርስቲያናዊ ሥርዓታቸውን በከፍተኛ ደስታ የሚገልጹት፤ እንግዲህ የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ሕግን ሁሉ እንደፈጸመ ተከታዮቹ ምዕመናን የእርሱን ቸርነት እያስታወስን አባታችን ቅዱስ ያሬድ የቅዱስ ወንጌልን ቃል ጠቅሶ ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላእክት ትቶ ስለጠፋው ስለአዳም በባሕር መካከል ቆመ፤ ተጠምቆም በሰላም ወጥቶ ተመለሰ ሲል አምላካችንን ባመሰገነበት ምስጋና እኛም ለአምላካችን ምስጋና በማቅረብ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን እንፈጽማለን በመጨረሻም ሁላችንንም ለከርሞ ሰው ይበለን። ✣

ስብሐት ለእግዚአብሔር

መልአከ አርያም ሐረገ ወይን ብርሃኑ

## ቧልተኛው

አንድ ቧልተኛ (ቀልደኛ) ሰው በጉን ሊሸጥ ገበያ ይዞ ሄደ። በገበያም ተቀምጦ ሳለ በግ ፈላጊ መጣና በዘንጉ የበጉን ጀርባ ነካ ነካ አድርጎ እንዲህ አለው።

ገዥ «ባለበግ»

ሻጭ «አይሸጥም ለዘንግ»

ገዥ «ምን ይላል አንተ?»

ሻጭ «ቧ ይላል»

ገዥ «ምን የሚያራ ነው?»

ሻጭ «በጠጥ»

እንዲህ እያለ ቢያላግጥበት ገዥ ተናደደና ጕራዴውን ውልቅ አደረገ (መዘዘ) በዚህን ጊዜ ባለበጉ ይባስ ብሎ፤

«አየንልህ ሁለት ጨው ያወጣ ልሃል» አለው (በዛን ጊዜ ጨው እንደ ገንዘብ መገበያያ ሆኖ ያለግል ስለ ነበር ነው።)

መዝገበ ፊደል ፲፱፻፳ ዓ.ም

## ደም

አንድ ክፉ ሰው ጕራዴውን ያለልክ ሳለና ስለቱን ለማየት በውሻው ጀርባ ላይ ሳብ ቢያደርገው ውሻው ከሁለት ክፍል ብሎ ሞተ። እሱም ለውሻው ጥቂት ሳያዝን «ኧከደከድዬ ጕራዴዮን የውሻ ደም ነካብኝሳ» ብሎ ጕራዴውን ሊያጥብ ወደ ወንዝ ወረደ። በወንዝም ተቀምጦ ሲያጥብ መንገደኞች ወንድማቸውን ሽፍታ ገድሎባቸው ጠፍቶ ነበርና ያንን ሽፍታ ሲፈልጉ ደም የነካው ጕራዴ ሲያጥብ ሲያዩት ይህ ነው ወንድማችንን የገደለው ብለው ደብድበው ገደሉት። ከዚህም የተነሳ «እግዚአብሔርም የውሻ ደም እንኳ አያስቀርም» ይባልል። ሰው እንግዳ ቢሆን እግዚአብሔር ባላገር ነው።

መዝገበ ፊደል ፲፱፻፳ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

# እኔም ወጣት ነበርኩ



**የ**ዛሬ እንግዳችን ብላታ ልሳኑ ሀብተወልድ ይባላሉ። የ፺፪ ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ናቸው። ብላታ ልሳኑ ከንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ጀምረው እስከ ደርግ ዘመን መጀመሪያ ድረስ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በተለያየ የኃላፊነት ደረጃ ሠርተዋል።

ሥራ የጀመሩት በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጸሐፊነት ነው። ከዚያም የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዩ ጸሐፊ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር ዋና ዳሬክተር፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸሐፊ፣ የመወሰኛ ምክር ቤት አባል በመሆን አገራቸውን አገልግለዋል። በአምስቱ ዓመት የጠላት ወረራ ዘመን በአርበኝነት በመሰለፍ ለሀገራቸው ነፃነት ደማቸውን አፍስሰዋል።

ብላታ ልሳኑ ሀብተ ወልድ ሥራ ወዳድ፣ ጀግና፣ ደፋርና የፍትሕ ሰው እንደ ሁኑ በቅርብ የሚያውቋቸው ሁሉ በአንድነት ይመሰክራሉ። ለቤተክርስቲያናችን «የክፉ ጊዜ መጠሪያ» የሚሆንዋት ሕንፃዎችና ቤቶች ያሠሩት ብላታ ልሳኑ ናቸው። ገንዘብ ሚኒስቴር ለመጀመሪያ ጊዜ ሥርዓት ያለው የግብር ክፍያ አሠራር እንዲኖረው ያደረጉም እኝህ ሀገር ወዳድ የሥራ ሰው ናቸው።

ብዙ ሰዎች ብላታ ልሳኑን ይዋል ይደር ሳይሉ ለነገሮች አፋጣኝ መፍትሔ በመስጠታቸውና አድልዎ በሌለበት ዳኝነታቸው ያውቋቸዋል። ተላላኪ ይሁን የመምሪያ ኃላፊ፣ ጳጳስ ይሁን ዘበኛ ለብላታ ልሳኑ እኩል ናቸው። ማንም ሰው (ባለጉዳይ ይሁን ሌላ) ወደ ቢሮአቸው ሲገባ ብድግ ብለው ይቀበሉታል። በትህትና ያነጋግሩታል።

በቅርቡ ልናነጋግራቸው ወደቤታቸው ብቅ ባልንበት ወቅት ግን እበር ድረስ ወጥተው እጅ ነስተው አልተቀበሉንም፣ ዛሬ ብላታ ልሳኑ ለእርጅናና ለሕመም እጃቸውን ሰጥተዋል። ቀንም ሌሊትም አልጋ ላይ ተጋድመው መቁጠሪያቸውን እየቆጠሩ ከፈጣሪያቸው ጋር እየተነጋገሩ ነው ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት። በአርበኝነት ወቅት ጥይት በአፋቸው ገብታ ጉሮሮአቸውን በስታ የወጣችበት ቦታ በስተ እርጅና ጊዜያቸው እህል አላስበላ ውሃ አላስጠጣ አላናግር እያለች ታስቸግራቸዋለች።

በመሆኑም እንደ ተመኘነው፣ እንደ ፈለግነው ልናነጋግራቸው አልቻልንም። ብላታ ልሳኑ አልጋቸው ላይ ጋደም፣ ትራሳቸውን ደገፍ ብለው በደከመ አቅማቸው በታመመ አንደበታቸው የሚችሉትን ያህል ተባብረውናል። እንደዛም ሆኖ ከብላታ ጋር ካደረግነው አጭር ቃለ መጠይቅ ወጣቱ ብዙ ትምህርት ይቀስማል የሚል እምነት አለን።



ቃለ መጠይቅ

**ፈ**ለገ ጥበብ – የትና መቼ እንደ ተወለዱ ቢገልጹልን?

**ብ**ላታ ልሳኑ – ሰኔ ፲ ቀን ፲፱፻፪ ዓ.ም እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ነው የተወለድኩት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በቤተክህነት (በአብነት) ትምህርት እስከ ምን ድረስ ተምረዋል? ዘመናዊውስ?

**ብ**ላታ ልሳኑ – ድጓ፣ ጾመድጓ፣ ቅኔ ተምሬአለሁ፣ በኛ ጊዜ ዘመናዊ ትምህርት ስላልነበረ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ብቻ ነው የተማርኩት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ሥራ መቼና የት ቦታ ነው የጀመሩት?

**ብ**ላታ ልሳኑ – በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጸሐፊነት ነው ሥራ የጀመርኩት በጸሐፊነት አምስት ዓመት ሠርቻለሁ ከዛ ኢ.ጣሊያ እስከ ገባ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ድረስ የጃንሆይ ልዩ ጸሐፊ በመሆን አገልግያለሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የአምስቱ ዓመት የጠላት ወረራ ዘመን የት ነው ያሳለፉት?

**ብ**ላታ ልሳኑ – አምስት ዓመት ሙሉ በአርበኝነት ነው ያሳለፍኩት፣ ብዙ ውጊያዎች ላይ ተሳትፌአለሁ ያልደረስኩበት ቦታ የለም። አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፍኩት ከራስ አበበ ጋር ነው። ከነፃነት በኋላ ተመልሼ በቤተ መንግሥት በልዩ ጸሐፊነት ሥራ ማገልገል ጀመርኩኝ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከዛስ?

**ብ**ላታ ልሳኑ – ለስምንት ዓመት ያህል በልዩ ጸሐፊነት ከሠራሁ በኋላ ደከመኝ ብዬ ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ተዛወርኩኝ፣ ገንዘብ ሚኒስቴር በዋና ዳሬክተርነት ማዕረግ ነበር የሠራሁት፣ እዛም እያለሁ እየተጠራሁ በመመላለስ በልዩ ጸሐሪነት እሠራ ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከገንዘብ ሚኒስቴር በኋላ የት ነው የሄዱት?

**ብ**ላታ ልሳኑ – ቤተክህነት ነው የመጣሁት፣ ዘመኑም በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም ነበር፣ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ዘጠኝና አሥር ዓመት ያህል አገልግያለሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የጠቅላይ ቤተክህነት ሥራ አስኪያጅ ሆነው በሠሩባቸው ዓመታት ከከናወኗቸው አበይት ተግባራት መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው በቤቶች (ሕንፃዎች) ያካሄዱት ግንባታ ነው። ለመሆኑ ይህንን ለማድረግ ያነሳሳዎ ምን ነበር? የወደፊቱን ሁኔታ ታይቶዎት ነበር? ገንዘቡስ ከየት አመጡት?

**ብ**ላታ ልሳኑ – እየሀ ቤተክርስቲያን ገንዘብ ታገኝልኝ መሬት ነበራት፣ ገንዘብ እጥታ አታውቅም፣ ያም በገንዘቡ ግን አትጠቀምበትም፣ ያም በዛ ይጉንጣል ይህም በዚህ ይጉንጠዋል፣ ገንዘቡ ብኩን ነው። እኔ አዲስ የተለየ ገንዘብ አላመጣሁም፣ ያደረግኩት ቢኖር ሁሉም ነገር እንዳይነካ አድርጌ በሥነ ሥርዓት በእኔ እጅ ብቻ ያዝኩት (ገንዘቡን ሳይሆን ገንዘብ የማዘዝ ሥልጣኑን...ሳቅ) ይህ በማድረጌ ብዙዎቹ ተንጫጩ፣ ብዙ አሉ...ዘለሉ፣ በመጨረሻ በኮሚሲዮን ተወስነባቸውና እኔ በጀመርኩት እንድገፋ ተደረገ። በአጭሩ ያን ያህል ልሠራ የቻልኩት በመጀመሪያ ገንዘብ እጄ ስለገባ በዛው ላይ ደግሞ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፈቃድም ስለ ነበረበት ነው።

የሳቸው ፈቃድ ግን በግልጽ አልነበረም። ምክንያቱም በግልጽ ይሁን እንዳይሉ ሁሉም የሚጮህባቸው ሆነ። በኋላ አንተ እንደ ፈለግክ አድርገው ብለው ሥልጣኑን ሰጡኝ። ሰዎች ሲናገሩዋቸው «እርሱ ከመንግሥት ታዞ ነው የመጣው ምንም ማድረግ አልችልም ይሥራ» ይሏቸዋል። እነርሱ ግን በዚህም አልተመለሱም ጃንሆይ ዘንድ ከሰሱኝ ጃንሆይም ኮሚሲዮን አቋቋሙ። ኮሚሲዮኑ ዛሬ ነገ ሲል ጊዜ ወሰደ፣ በዚህ መሃል እኔ ብዙ ሥራ ሠራሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በእርስዎ ጊዜ ምን ያህል ቤቶችና ሕንፃዎች እንደተሠሩ ያስታውሳሉ?

**ብ**ላታ ልሳኑ – ሁሉም ሕንፃ እኔ ነኝ ያሠራሁት፣ ቤት ብቻ አይደለም ሌላም ብዙ ሠርቻለሁ፣ ሥራውን ግን እንደዚሁ በቀላሉ አይደለም ያሠራሁት፣ እዛም እዛም ተቃዋሚ ብቻ ነው፣ እዛም እዚህም አቤት ባይ፣ ከሳሽ ብቻ ነው፣ እዛ ቤተክህነት አካባቢ ያለው ፲፰ ሺህ ካሬ ሜትር መሬት የጭሰኛ ነበር። ቤተክህነት የነበራት አንድ ቤት ብቻ ነበር። ያንን ሁሉ ግምት እየከፈልኩ፣ እያስነሳሁ ነው ያሠራሁት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ወደ ኋላ ልመልስዎትና አዲስ አበባ ተወልጄ አዲስ አበባ ውስጥ ነው ያደግኩት ብለዋል፣ በዚህ ዓይነት የቆሎ ተማሪ ሆነው አያውቁም ማለት ነው?

**ብ**ላታ ልሳኑ – ቆሎ ተማሪማ ሁኛለሁ፣ ነበርኩኝ፣ ሰኮሩ ማርያም የምትባል አለች ደብረብርሃን በታች እስከ መጨረሻው እዛ ነበር የተማርኩት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እዛ ድረስ ለምን ሄዱ?

**ብ**ላታ ልሳኑ – እዛ ጥሩ ጥሩ አስተማሪዎች ነበሩ፣ ደግሞ በዛን ጊዜ እዚህ አዲስ አበባ የተገኙ ብዛት አያስተምርም፣ (ሳቅ...)

**ፈ**ለገ ጥበብ – አሁን ደግሞ ወደ ሥራ አስኪያጅነት ጊዜዎ እንመለስ፣ ብዙ ሰዎች የሚሰጡት ውሳኔ አድልዎ ያልነበረበት ቢሆንም ኃይለኛና ቁጡ ነበሩ ይላሉ ይህንን ቢያብራሩልን?

**ብ**ላታ ልሳኑ – ይህንን የሚሉበት ምክንያት ይሆናል ካልኩኝ ይሆናል፣ አይሆንም ካልኩኝ አይሆንም ስለምል ይህን ለምን አለ ነው? በተረፈ ኃይለኛ ሁኜ የመታሁት፣ ደመወዙን የቆረጥኩበት፣ ከሥራ ያነሳሁት የለም። ድሮ ከኔ ጋር ሲሠሩ የነበሩ ሰዎች ሲያገኙኝ አባታችን እንጂ እንዲህ አደረግከን፣ በደልከን የሚል ሰው አላጋጠመኝም፣ የለም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እንግዲህ እርስዎ ከቤተ መንግሥት ሌላ በገንዘብ ሚኒስቴርም በፓርላማም በቤተክህነትም ሠርተዋል፣ የቤተክህነት አሠራርና ሠራተኛ ከሌላው መሥሪያ ቤት ጋር ሲያነጻጽሩት እንዴት ይገመግሙታል? (ምን ይመስላል?)

**ብ**ላታ ልሳኑ – ቤተ ክህነት ዛሬም ያው ነው፣ ለምን ቤተክህነት መጓተት ይወዳል ቶሎ ውሳኔ አይሰጥም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ለመሆኑ በመጀመሪያ ወደ ቤተ ክህነት የመጡት በትእዛዝ ተገደው ነው ወይስ ወደውና ተሹመው?

**ብ**ላታ ልሳኑ – ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ጃንሆይን አስፈቅደው ነው የወሰዱኝ፣ አባቱ መልአከ ሕይወት ሃብተ ወልድ የቤተ ክህነት ሰውና አገልጋይ ስለ ነበሩ እኔም የቤተክርስቲያን ልጅ በመሆኔ እርሱ ነው የሚረዳኝ ብለው ነው የወሰዱኝ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የቤተ ክርስቲያን ልጅ ከመሆንዎ ለተወሰነ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንዋን በሥራ አስኪያጅነት መርተዋል፣ በእርስዎ እምነት ቤተ ክርስቲያናችን ለወደፊቱ ይበልጥ ልታድግ የምትችለው በምን ሁኔታ ነው ይላሉ?

**ብ**ላታ ልሳኑ – ድሮ አንድ ካህን በዓመት መቶ ብር እንኳን አያገኝም፣ ለሕይወቱ ለነፍሱ ብሎ ነው የሚያገለግለው፣ ንብረት እይዛለሁ ይህንን እገዛለሁ ብሎ አይደለም፣ ለቤተ ክርስቲያን ብሎ ነው የሚኖረው። አሁን ያ ቀርቶ ቤተክርስቲያን አገልጋዮቿን በገንዘብ ትገዛለች፣ አሁን የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የገንዘብ አገልጋይ ነው እንጂ የእግዚአብሔር አገልጋይ አይደለም፣ ቤተ ክርስቲያን የምታድገው ለእግዚአብሔር ብለው የሚያገለግሉ



www.ethiopianorthodox.org

ሠራተኞች ሲኖርዋት ብቻ ነው። ለዚህ ከእግዚአብሔር ፍርድ በቀር የሚሻል መፍትሔ አይታየኝም።

ፈለገ ጥበብ — በአሁኑ ጊዜ መንግሥት እርስዎ ያሠሩዋቸውን ሕንፃዎች ጨምሮ የቤተክርስቲያንዋ ቤቶች ለባለቤቷ እየመለሰ ነው፤ ምን ይሰማዎታል?

ብላታ ልሳኑ — ጥሩ ነው፤ ብቻ ቤተ ክህነት እስከ አሁን የተቀበለችው ትልልቆች ብቻ ነው ሲባል ሰምቻለሁ እነርሱም ቢሆን ክነ መሬታቸው አልተመለሰላትም፤ ይህም በገዛ ንብረቷ ጥገኛ (ጭሰኛ) ሆናለች ማለት ነው።

ፈለገ ጥበብ — ሊመሆኑ በእርስዎ ጊዜ የቤተ ክርስቲያንዋ ቤቶች ሁሉ ሕጋዊ ይዞታ የሚያሳይ ካርታ ነበራቸው?

ብላታ ልሳኑ — ካርታውን በግብፁ አቡነ ማቴዎስ ጊዜ የአፄ ምኒልክ ጳጳስ የነበሩት እሳቸው ራሳቸው ናቸው ያስነሱት ካርታው ቅርብ ጊዜ ድረስ ቤተ ክህነት ውስጥ ነበር። አሁንም ይኖራል ብዬ አምናለሁ። ሌሎችም ሁሉ አላቸው።

ፈለገ ጥበብ — ከመልስዎ ለመረዳት እንደ ቻልኩት ከአፄ ኃይለ ሥላሴ በፊት ሥራ እንደ ጀመሩ ነው፤ ሁኔታው እንዴት እንደ ነበር ቢገልጹልን?

ብላታ ልሳኑ — እንግዲህ አፄ ምኒልክ የሞቱት የስድስት ዓመት ሕፃን እያለሁ ነው። በዘጠኝ ዓመቴ ንግሥት ዘውዲቱ ነገሡ። እኔም ሥራ የገባሁ በሳቸው ጊዜ ነው።

ፈለገ ጥበብ — ሁሉም የኢትዮጵያ ነገሥታት የእግዚአብሔር አገልጋዮች የቤተ ክርስቲያን ተንከባካቢዎች እንደ ነበሩ ቢታወቅም በተለይ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በይበልጥ ቤተ ክርስቲያንን አፍቃሪ ነበሩ ይባላል በቅርብ የሚያውቋቸው ከሆኑ ስለሳቸው ቢነግሩን?

ብላታ ልሳኑ — ንግሥት ዘውዲቱን በቅርብ አውቃቸዋለሁ፤ አንድ ነገር ግን ልንገርዎ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ ሥራቸው ቤተክርስቲያን ነው ሌላ ሥራ አልነበራቸውም። አለዝያ ጦርነት ነው። እና ቤተ ክርስቲያን ተከብራ ትኖር ነበር። አፄ ኃይለ ሥላሴ ናቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ራስዋን ትቻል ብለው የለቀቁዋት፤ ከዛን ጊዜ ወዲህ እንዲህ ሆና ቀረች። ከዛ በፊት ነገሥታት አስተዳደርዋን ብቻ ሳይሆን ሃይማኖቱንም ይቆጣጠሩ ነበር። አፄ ኃይለ ሥላሴ ግን ሀገር የጋራ ሃይማኖት የግል ብለው ለቀቅዋት።

ፈለገ ጥበብ — ዋናው ትኩረታችን ወደ ሆነው ወጣቱ ትውልድ ደግሞ እንምጣ፤ አሁን በወጣቱ ላይ የሚታየው የሥነ ምግባር ጉድለት ምንጩ (ምክንያቱ) ምንድነው ይላሉ? ጥፋቱ ከራሱ ከወጣቱ ነው ወይንስ ከወላጆች?

ብላታ ልሳኑ — ጥፋቱ የሱም የወላጆችም አይመስለኝም። ዘመን ነው ተሸክሞ ያመጣበት፤ ወላጆችም እንዳያዙት እርሱም እንዳይታዘዝ ያደረገው፤ ለዚሁ መፍትሔው መከራ ነው። ከመከራ በቀር መፍትሔ የለውም፤ መከራውም ይዞታል በመጨረሻም ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ መፍትሔ አያገኝለትም።

ፈለገ ጥበብ — ከዚሁ ጋር በተያያዘ በእናንተ ጊዜ ያልነበረ ዛሬ የኤድስ በሽታ መጥቷል። ለዚሁስ መፍትሔው ምንድነው ይላሉ? በሌላ አባባል ወጣቱ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?

ብላታ ልሳኑ — ሰማህ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠ ሕግ የለም፤ ትእዛዝ ሰጥቷል፤ ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሉዋት ብሎ ሲል አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ተብሎ የተወሰነ ነገር ነው። የእግዚአብሔር ሕግ ከፈረሰ በኋላ ይህ በዚህ ይሆናል በዚህ ያዋጣል ማለት አይቻልም፤ መድኃኒቱ ያንን ያፈረሰውን ሕግ መልሶ መጠበቅ ነው። ወጣቱ ማወቅ ያለበት መማር ያለበት ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ።

፩. ወጥተህ ወርደህ በላብህ ሠርተህ ብላ፤

፪. አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ፤ እነዚህ ሁለት ነጥቦች የማይዘለሉ ናቸው። በተረፈ ለሚደርሰው ጥፋት አንዱ በአንዱ ማመካኘት አይችልም። ተጠያቂው ጥፋተኛው ራሱ ነው።

ፈለገ ጥበብ — በመጨረሻ ወደ ራስዎ ሞያ ልመለስ፤ ድጓ መማርዎን ነግረውናል፤ በአሁኑ ጊዜ ያለው የድጓ ትምህርት ይዘት ከእናንተ ጊዜ ጋር ሲያነፃፅሩት እያደገ ነው ወይስ እየተዳከመ ነው የሚገኘው?

ብላታ ልሳኑ — ዛሬ ገንዘብ ስላለ ማንም ይወደዋል፤ ጥራቱ ግን እንደ ድሮው አይደለም፤ ዛሬ ድጓ ሰንበት አምኜ ብቻ እርሷን ነው እንጂ መዝገበ ድጓ ገብቶ የሚማር የለም። ጾመ ድጓ ትንሽ ነው የሚማረው፤ ዝማሬ መዋስዕት፤ አቋቋም፤ ቅኔ ይህን ሁሉ ሰብስቦ የሚማር የለም።

ፈለገ ጥበብ — በአባትነትዎ ለወጣቱ የሚያስተላልፉት ተጨማሪ መልእክት ካለ?

ብላታ ልሳኑ — ወጣቱ ትውልድ ችግር ላይ ነው ያለው። እንደ ሐሳቡ መሄድ አይችልም፤ ልማር ቢል በሃሳቡ መጠን አይማርም፤ በጣም ችግር ላይ ነው ያለው፤ ወላጆቹ፣ የሚተካ አይደለም፤ የጥንቱ ወጣት ጠንካራ ነበር፤ ምክንያቱም ድሮ ድሎት የለም። ከትልቅ ጀምሮ እስከ ትንሽ ድረስ ጧት ምናልባት እናቱ አቢራ እንዳይመታህ ብላ ይህችን ጉረስ ብላ አንድ ጉርሻ ታጉርሰዋለች፤ ከዛ ሄዶ ውሎ ማታ ሲመጣ ነው የሚበላው። ስለዚህ ለሱ መከራ ችግር ምኑም አይደለም። ለምሳሌ ሁላችንም አዲስ አበባ ነው የተወለድነው፤ በአርበኝነት ስንሄድ አክስት የለን፤ አጎት የለን፤ ምን የለን ዝም ብለን ነው የወጣነው፤ ሦስት አራት ቀን ጦማችን ውለን ስናድር እግዚአብሔርን አመስግነን ዝም ነው። የዛሬ ልጅ ይህንን ማድረግ ይችላል?

ትምህርቱም ቢሆን የዛሬ ልጅ ይከብደዋል፤ የጥናት ልምድ የለውም፤ ድሮ ትምህርት «ሀ» ሲል በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይልና ይጀምራል። ከዛ የፈለገውን ሲነግሩት በዕለቱ ይይዛል። ድሮ ተማሪው በመጽሐፍ የሚማረው ዳዊት ብቻ ነው ሌላውን በቃሉ ነበር የሚማረው፤ የአሁኑ የዛን ዓይነት ልምድ የለውም። ✣

ፈለገ ጥበብ — እግዚአብሔር ያክብርልን።

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር



# ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

## ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

### መሥዋዕተ ወንጌል (ሥጋ ወደሙ)



ወልደ እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ወድዶ በአቀረበልን በሥጋው በደሙ ቅዱስ ቁርባንነት እኛ ሁላችን እንከብር ዘንድ ለሚያምኑ ሁሉ መንጻት፤ ሥርየተ ኃጢአት፤ ክብር፤ ሕይወት፤ የሚገኝባትን አንዲት መሥዋዕት ለዘለዓለም የማትሻር የማትለወጥ አድርጎ ሠራ። ይህችም መሥዋዕተ ወንጌል ናት። (ዕብ.፲፥፲፬)

አይሁድ ስለ ኃላፊው መብል ብቻ አጥብቀው ሲፈልጉት፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለኃላፊው መብል ሳይሆን ዘለዓለም ለሚኖረው ምግብ አስቡ» ቢላቸው «አባቶቻችን ከሰማይ እንጀራ በሉ አንተስ ከዚህ የተሻለ ምን ተአምራት ታደርጋለህ?» አሉት።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ይህ ሙሴ የሰጣችሁ እንጀራ አይደለም። ይህ ከሰማይ የወረደ ኅብስት ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው። እኔም የምሰጣችሁ ኅብስት ሥጋዬ ነው፤ በእኔ የሚያምን አይራብም፤ አይጠማም፤ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ እንጀራ በሉና ሞቱ፤ ከዚህ ኅብስት የሚበላ ግን ለዘለዓለም ይኖራል እንጂ አይሞትም፤ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ለዘለዓለም ሕይወት የምሰጠው ምግብ ሥጋዬ ነውና በእውነት እነግራችኋለሁ የወልደ ዕጓለ እመሕያውን ሥጋውን ከአልበላችሁ ደሙንም ከአልጠጣችሁ የዘለዓለም ሕይወት የላችሁም ብሎ አስተምሮዋቸዋል። (ዮሐ.፮፥፳፮–፶፰)።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሙስ ማታ አይሁድ በብሉይ ኪዳን ሥርዓት በጉን በመቅደስ አርደው፤ ሲመሽ ወስደው፤ በቤታቸው ከተካፈሉት በኋላ ምሳሌ የነበረው በግዐ ፋሲካ አልፎ «ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም» የተባለው አማናዊ መሥዋዕት ተተካ። (ዘጸ.፲፪፥፫–፲፫፤ ዮሐ.፩፥፳፱)

በብሉይ ኪዳን ስለ ፋሲካ በዓል አከባበር በሚደረገው ማዕድ ላይ ተቀምጦ ሳለ አምላካችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፋሲካው ራት ከቀረበው ኅብስት አንሥቶ አመስግኖ ባርኮ ቆርሶ ስለ እናንተና ስለብዙዎች ቤዛ የሚፈተትና የሚሰጥ ሥጋዬ ይህ ነው። እንኩ ብሉ» ብሎ ሰጣቸው። እንዲሁም ጽዋውን አንሥቶ፤ አመስግኖ አክብሮ «ስለ እናንተ ስለዓለም ሕይወት የሚፈሰው አዲስ ሥርዓት ሁኖ የሚሰጠው ደሜ ይህ ነው። እንኩ ጠጡ» ብሎ ሰጣቸው። (ማቴ.፳፮፥፳፮–፳፰፤ ማር.፲፬፥፲፮–፳፭፤ ሉቃ.፳፪፥፲፬–፴፰፤ ዮሐ.፮፥፶፮–፶፱፤ ፩ቆሮ.፲፩፥፳፫–፳፮)

እነሱም አምነው ተቀብለው ሥጋውን በሉ ደሙን ጠጡ። ፈጣሪያችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ምሥጢርን ሠርቶ አሳይቶ «መታሰቢያዬን እንደዚህ አድርጉ» ብሎ ስለ አዘዛቸው ሐዋርያት ከክርስቶስ የተቀበሉትን ትእዛዝ ለቤተ ክርስቲያን በመስጠታቸው ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ሕማሙን፤ ሞቱን ትንሣኤውን ዕርገቱን፤ ዳግም ምጽአቱን በልብ እየአሰበች፤ በአፍዋ እየመሰከረች በሐዲስ ኪዳን ለሐዲስ ሥርዓት የተሰጠውን የዓለሙን ኃጢአት የሚያስተሠርየውን ሥጋ ወልደ እግዚአብሔርን ደመ ወልደ እግዚአብሔርን ስትቀበል ስታቀብል ኖራለች ትኖራለች።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ይህ ኅብስት ሥጋዬ ነው ይህ ጽዋ ደሜ ነው ብሎ ኅብስቱን ወይኑን ሥጋውን ደሙን አድርጎ ለደቀ መዛሙርቱ በመስጠቱ የሐዲስ ኪዳን ቃሉን በደሙ አተመ «ይህ ኅብስት ስለ ብዙ ሰዎች ቤዛ የሚፈተት ሥጋዬ ነው። ይህ ጽዋ ስለ ዓለም ሕይወት ስለ ኃጢአት ሥርየት የሚፈስሰው የሐዲስ ሥርዓት ደሜ ነው» ያለው ቃሉ መሥዋዕተ ኦሪትን ሽሮ መሥዋዕተ ወንጌልን ተካ (ዕብ.፲፥፫–፱)።

የሐዲስ ኪዳን ቍርባን ምሳሌ ወይም መታሰቢያ አይደለም። ሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ይህ ኅብስት ሥጋዬ ነው ይህ ጽዋ ዕደሜ ነው ብሎ እንደ ነገረን እውነተኛ ሥጋው እውነተኛ ደሙ ነው እንጂ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስቱን ወይኑን በምሥጋና አክብሮ ቀድሶ ማለት ኅብስቱን ወይኑን ሥጋውን ደሙን አድርጎ በፍጹም ሃይማኖትና በንጽሕና ልንበላውና ልንጠጣው ስለሰጠን «መታሰቢያዬን አድርጉ» በአለው መሠረት ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ኅብስቱን በጻሕል፤



www.ethiopianorthodox.org

ወይኑን በጽዋ ታቀርባለች፤ በጸሎት በቡራኬ ኅብስቱን ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑን ደመ ወልደ እግዚአብሔር አድርጋ ታቀርባለች።

ቤተ ክርስቲያን ሥጋውን ደሙን በምታከብርበት በምትቀድስበት ጊዜ መገረፉን፣ መሰቀሉን፣ መቸንከሩን፣ መወጋቱን፣ ሕማሙን፣ ሞቱን ታስባለች፣ ታሳስባለች።

ካህኑ ኅብስቱን በጻሕል፣ ወይኑን በጽዋ አድርጎ እንደ ሥርዓቱ ሲባርከው ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ይሆናል።

«ነአምን በቍርባን እምቅድመ ይቄድሶ ካህን ኅብስት ወወይን ወሶበ ይቄድሶ ካህን ይትመየጥ ወይትዌለጥ ወይን እምከዊነ ወይን ኅበ ከዊነ ደም ዘወልደ እግዚአብሔር በህላዌሁ (ሃይማኖተ አበው አትናቴዎስ) ብሎ እንደ ተናገረው ሥጋውን ደሙን የተቀበለ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን አግኝቶ ይኖራል።

ስለዚህም አንደኛ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሙስ ማታ «ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ» ብሎ እንደ ሰጠን፣ ሁለተኛ ካህናት በቤተ መቅደስ ዘወትር የሚያቀርቡት ኅብስቱ ወይኑ የክርስቶስ ሥጋው ደሙ እንደ ሆነ፣ ሦስተኛ በኅብስት በወይን መልክ ቢታይም ካህናት የሚሰጡን እኛም የምንቀበለው ኅብስቱ ወይኑ በእውነት የአምላካችን የአማኑኤል ሥጋው ደሙ እንደሆነ እናምናለን።

## የሥጋ ወደሙ ጥቅም

ሥጋ ወደሙ የተቀበለ ለዘለዓለም ሕያው ሁኖ ይኖራል ማለት በነፍስ አይሞትም፣ ሲዖል ገሀነም አይገባም፣ በገነት በመንግሥተ ሰማያት ይኖራል (ዮሐ.፮፥፶፩–፶፴)።

ሥጋ ወደሙ የተቀበለ ክርስቶስን ተዋሕዶ፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ ሁኖ ይኖራል፤ ክርስቶስም በጸጋ ያድርበታል። (ዮሐ.፮፥፶፮–፶፰) ክርስቶስ ሥጋውን የቆረሰው ደሙን ያፈሰሰው ለቤዛ ብዙኃን ስለ ሆነ ሥጋ ወደሙ የሥጋም የነፍስም መድኃኒት ነው (ሉቃ.፳፪፥፲፱–፳፩፤ ማር.፲፬፥፳፬፤ ፩ቆሮ.፲፩፥፳፬–፳፭)።

«ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ነውና ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው እኔም በኋለኛይቱ ቀን አስነሣዋለሁ የላከኝ አብ ሕያው እንደሆነ እኔም ከአብ ስለ ተወለድሁ ሕያው እንደ ሆንኩ ሥጋዬን የበላም ስለ እኔ ሕያው ሆኖ ይኖራል» እንደ አለው ሥጋውን ደሙን የተቀበሉ ሁሉ ሁለተኛው ሞት የለባቸውም፤ ለዘለዓለም ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ (ዮሐ.፮፥፶፴–፶፯)።

ሊቁ አባ ሕርያቆስም «እሳት ማኅየዊ ለርቱዓነ ልብ ለእለይገብሩ ፈቃዶ» ብለዋል። እሳት ነው ብዩ ብነግራችሁም አንድነቱን ሦስትነቱን ዐውቀው፣ ሕማሙን ሞቱን አምነው ኃጢአታቸውን ለመምህረ ንስሐ ነግረው መምህረ ንስሐ ያዘዘውን ሠርተው በሚገባ ለሚቀበሉ ሰዎች የሚያድን እሳት ነው ማለቱ ነው። እሳት በመጠን የሞቁት እንደ ሆነ የበሉትን የጠጡትን ያስማማል፣ ደዌ ይከፍላል። ሥጋው ደሙም ከኃጢአት ነጽቶ ቢቀበሉት ሕይወተ ሥጋ፣ ሕይወተ ነፍስ ይሆናል፤ ደዌ ነፍስ ያርቃልና።

ይኸው አባ ሕርያቆስ በሌላ ቦታ «ኦ ኅብስት እንተ እምኔኪ ለእለ ይበልዕ እምኔሁ በአሚን ዘይሁብ ሕይወተ ወመድኃኒተ፤» ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ሰው እንደ ሆነ በማመን፤ ሥጋው ደሙም እንዲለወጥ በማመን ለሚቀበሉ ሰዎች ሕይወትን፣ ድኅነትን የሚያድል ከአንቺ የተገኘ ኅብስት ምን ይረቅ ምን ይደንቅ በማለት እመቤታችንን እያደነቀ አመስግኖዋል። በመቀጠልም ከ፫ቱ አካላት አንዱ አካል ሰው እንደ ሆነ ሥጋው ደሙም እንደሚለወጥ በማመን ለሚቀበሉት ሰዎች «ከአንቺ የተገኘ ጽዋዕ ቋንቋ የሚያናግር ምሥጢር የሚያስተረጉም፣ ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስን የሚያድል መሆኑ ምን ይረቅ ምን ይደንቅ» ብሎ አመስግኖዋል።

## ሥጋ ወደሙን ከመቀበል በፊት ስለሚደረገው ጥንቃቄ

ሀ. ሥጋውን ደሙን የሚቀበል ሁሉ አምኖ መቀበል አለበት ሳያምን ቢቀበል ፍዳ ይሆንበታል። በልብ ቂም በቀልንና የመሰለውንም ክፉ ግብር ይዞ መቍረብ አይገባም (፩ቆሮ.፲፩፥፳፯–፴)።

ለ. ቍርባን መቀበል ንስሐ ገብቶ ከኃጢአት ነጽቶ ነው። ከክርስቲያን ወገን ማንም ሰው የክርስቶስን ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ትንሣኤ ዘለሕይወትን ሊወርስ ቢወድ ልቡን ከቂም ከበቀል፣ ሰውነቱን ከበደል ንጹሕ አድርጎ መቀበል አለበት። ይህም ማለት ሰው ስለሚያውቀው ኃጢአት ተናዝዞ ስለማያውቀው ይቅር በለኝ እያለ በንጹሕ ይቍረብ ማለት ነው።

ሐ. የሚቆርቡ ሰዎች ከመቍረባቸው በፊት ፫ ቀን ከቍርባን በኋላ ፪ ቀን ከሩካቤ ሥጋ መከልከል ይገባቸዋል።

መ. ሥጋ ወደሙ ለመቀበል ፲፰ ሰዓት ከእህል ከውሃ ተከልክሎ መጾም ይገባል። (ኢይንሣዕ መኑሂ ቍርባነ ዘእንበለ ይጹም በንጹሕ) (ፍት.መን.፲፫፣ ረሰጠብ ፵፯)።

ሠ. ሰው ዝንየት (ርስሐት) ከአገኘው በዚያ ቀን አይቆርብም።

ረ. ካህንም ሆነ ምእመን በሚቆርብበት ቀን ዕንቅፋት ቢያገኘው ማለት ነስር፣ ትውኪያ (አንቃር) ብስና ማንኛውም የአካል መድማት ቢያጋጥመው ወይም ጥርሱ በመፋቂያ ቢደማ ወይም አፉ ወደ አፍ የሚገባ እንደ ትንኝ ዝምብ ይህን የመሰለ ሁሉ ቢያጋጥመው በዚያው ዕለት መቍረብ አይገባውም። ከቍርባን በኋላ ከአለመ ጠንቀቅ የተነሣ እንዲህ ያለ ነገር ቢያጋጥመው ንስሐ ሊሰጠው ይገባል። ንስሐውን ሳይፈጽም እንደ ገና መቍረብ አይችልም (ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ)።

## ሥጋ ወደሙን በድፍረት በመቀበል ስለሚያመጣው ቅጣት

«ወምስለ ውእቱ ኅብስት ቦአ ሠይጣን ውስተ ልቡ ለይሁዳ ሥጋውን ሲቀበል በይሁዳ ልብ ሠይጣን ገባ» ብሎ ቅዱስ ወንጌል እንደ ተናገረው ሥጋ ወደሙን ንስሐ ሳይገቡ፣ ልብን ሳያነጹ ቢቀበሉት መንፈስ ቅዱስን በማሳደር ፈንታ መንፈስ ርኩስን ያሳድራል፤ ፍዳ ያመጣል፤ በሥጋም ሆድ ቁርጠት፣ ቁርጥማት፣ ራስ ምታት ሁኖ በክፉ ደዌ ያስመታል (ዮሐ.፲፫፥፳፯)።

ማንም ሰው ንስሐ ሳይገባ ከኃጢአት ሳይነጻ ቢቆርብ የጌታ– ሥጋ እንደ ሆነ አላወቀምና እንደ ምድራዊ ምግብም አቃልሎታልና በኃጢአት ሳለ ያለ ኀፍረት በድፍረት ሥጋውን ደሙን በመቀበሉ ሥላሴ ይፈርዱበታል (፩ቆሮ.፲፩፥፳፫–፳፱)።

«መንሡትኪ ነሢእ ሥጋሁ በድፍረት ወተመጥዎ ደሙ ዘእንበለ ሐፍረት እንዘ ቦ ላዕሌሁ ነውረ ኃጢአት፣ ኀጢአት እያለበት ሥጋውን ደሙን ያለ ሐፍረት በድፍረት መቀበል ጥፋት እኮ ነው» ብሎ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደ ተናገረው መቅሰፍት ፍዳ ያመጣል።

ሊቁ አባ ሕርያቆስም «እሳት በላኢ ለዐማጽያን ለእለ ይክህዱ ስሞ» ብሎዋል። ስመ አምላክነቱን ለሚክዱ ሰዎች የሚያቃጥል እሳት ነው። ከኃጢአት ሳይነጹ ቢቀበሉት በፍዳ ላይ ፍዳ የሚያመጣ ስለሆነ፣ እሳት ከወረደው ነበልባሉ ከመረተው ፍሕሙ ቀርበው ያለ መጠን ቢሞቁት ያቃጥላል ሥጋ ወደሙም በማይገባ ቢቀበሉት ፍዳ ያመጣልና።

ሊቃውንት ሥጋውን በእሳተ ባቢሎን ደሙን በማየ ግብፅ መስለው ይናገራሉ። እሳተ ባቢሎን ሠለስቱ ደቂቅን ሳይነካ በአፍአ ያሉ የባቢሎንን ሰዎች አቃጥሎዋቸዋል። ሥጋውም ከኃጢአት ነጽተው የሚቀበሉትን ያድናቸዋል፤ ከኃጢአት ሳይነጹ የሚቀበሉትን ያጠፋቸዋልና። ማየ ግብፅ ግብፃውያንን ሲያጠፋ እሥራኤልን አላጠፋም። ዛሬም ቀሳውስት ይህን ምሳሌ ይዘው የበደላችሁትን ሳትክሱ የቀማችሁትን ሳትመልሱ ከኃጢአት ሳትነጹ ሳትበቁ ብትቀበሉት ሥጋው ደሙ በነፍስ በሥጋ ያስፈርድባችኋል እያሉ በፍሬ ቅዳሴ መጀመሪያ ላይ ዐዋጅ ይናገራሉ። ይኸው አባ ሕርያቆስ በመቀጠል «አንድነቱን ሦስትነቱን፤ ሥጋ ወደሙ መለወጡን ባለማመን ለሚቀበሉ ሰዎች ከአንቺ የተገኘ ኅብስት የማይሳመጥ ጽኑ ኀያል የአድማስ ደንጊያ ነው «የብረት ቆሎ፤ የደንጊያ ንፍሮ» እንዲሉ። እንዲሁም ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ሰው እንደ ሆነ ሥጋው ደሙ እንዲለወጥ ባለማመን ለሚቀበሉት ከአንቺ የተገኘ ጽዋ የሚያስክር፣ የሚያንገደግድ፣ የሚጥል፣ ኃጢአትን በማስተሥረይ ፋንታ ኃጢአትን የሚጨምር ነው» ብለዋል።

## ሥጋውን ደሙን በመራቅ ወይም በመሸሽ ስለሚያመጣው ቅጣት

የወልደ እጓለ እመሕያው የክርስቶስን ሥጋውን ያልበላ ደሙንም ያልጠጣ ሕይወት የለውም በሥጋ ብቻ ሳይሆን በነፍስም ይሞታል፤ ሲዖል፣ ገሀነመ እሳት ይገባል፤ ገነት፣ መንግሥተ ሰማያት ሊገባ አይችልም (ዮሐ.፮፥፶፫)።

## ከቍርባን በኋላ የሚደረግ ጥንቃቄ

ሀ. ከቆረቡ በኋላ ንጽሕናን ጠብቆ በጽኑ ሃይማኖትና በምግባረ ሠናይ መኖር ነው። በዚያው ዕለት ወደ ፍርድ ቤት መሄድና መሟገት ክልክል ነው። (ጉባኤ ኒቅያ) በሌላም ጊዜ ልበ ሰፊ፣ ነገር አላፊ፣ ሐዳጌ በቀል ሁኖ መኖር ያስፈልጋል።

ለ. በቆረቡበት ቀን ከሚስት መገናኘት፣ አብዝቶ መብላት፣ መጠጣት፣ ጥፍር መቁረጥ፣ ጠጉር መላጨት፣ በውሃ መታጠብ፣ ከልብስ መራቆት ክልክል ነው። (ሥርዓተ ቅዳሴ ቁ.፶፮)

## የሥርዓተ ቍርባን ትርጕም

ሥጋ ወደሙ ከመቀበላቸው በፊት ፫ ቀን ከሴት ተከልክለውና ተጠብቀው እንዲቆዩ የተደረገበት ምክንያት በአሪቱ ዳዊትና ከርሱ ጋር የነበሩት ወደ ካህኑ ወደ አብያታር (አቢሜሌክ)' በመጡና የሚበሉት የቍርባን ኅብስት እንዲሰጣቸው ካህኑን በጠየቁት ጊዜ ከሴት ከራቃችሁ ሦስት ቀን ሞልቷችኋል ወይ? ብሎ መልስ ጠይቋቸው ነበረ። እነሱም ከቤታችን ከወጣንና መንገድ ከጀመርን ሦስት ቀን ሆኖናል። ብለው ሲመልሱለት ኅብስተ ቍርባኑን ሰጥቶዋቸው ዳዊትና ሠራዊቱ ስለበሉ የዚያ ምሳሌ ነው። ከዚያም ቀደም ብሎ እሥራኤል ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በተጠሩ ጊዜ ሦስት ቀን ከሴት እንዳይገናኙ ሙሴ ያዘዘ ስለሆነ የዚያ ምሳሌ ነው (ዘጸ.፲፱፥፲፭፤ ፩ሳሙ.፳፩፥፩–፮)።

ካህናት ወንጌል ሲነበብ አክሊላቸውን የሚያወርዱት ጌታ ከተጠመቀ በኋላ በፍልስጥኤምና በምድረ





www.ethiopianorthodox.org

ይሁዳ በግልጽ የማስተማሩና የመታየቱ ምሳሌ ነው።

ታቦት የእመቤታችን፣ ጽላት ከእመቤታችን የነሣው ሥጋና ነፍስ፣ በጽላት ላይ ያለ ቃል የተዋሐደው አካላዊ ቃል ምሳሌ ነው።

ምሥዋዑ (መሠዊያው) ጻሕሉ፣ ጽዋው፣ የመንበረ ጻባዖት፣ የጎል፣ የመቃብር ምሳሌ ነው።

መሶበ ወርቅ፣ ማዕጠንተ እሳት፣ የእመቤታችን ምሳሌ ነው፤ ፍሕም የመለኮት፣ ዕጣን የትስብእት፣ መዐዛው የመዓዛ መሥዋዕት ምሳሌ ነው።

ኅብስተ ቍርባኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጻሕል የሚለብሰው ማኅፈድ ጌታ ሲወለድ የተጠቀለለበት ጨርቅ፣ ሲሞት የተገነዘበት መግነዝ ምሳሌ ነው። ይኸውም ኅብስቱ የሚጠቀለልበት ማኅፈድ ነው።

ከላይ የሚለብሰው ማኅፈድ ጌታ ሲወለድ እናቱ ያለበሰችው ቈጽለ በለሶን ምሳሌ ነው (የልደት ድጓ)

ጻሕሉ ከላይ የለበሰው ሁለተኛው ማኅፈድ በበረት ሲወለድ የተነጠፈለት መንጸፍ ምሳሌ ነው።

በታቦት ላይ የሚነጠፈው ማኅፈድ የመንጦላዕተ እሳት ምሳሌ ነው (ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ሠራዊት)

ጻሕሉ ከላይ የለበሰው ፫ኛው ማኅፈድ የጌታ መቃብር ድንጋይ ምሳሌ ነው፤ ምሥዋዑ የሚለብሰው የሚከደንበት ልብስ ጌታ የተገነዘበት በፍታ ምሳሌ ነው።

ዕርፈ መስቀል (መንካ) የሱራፌ ጉጠት ምሳሌ ነው (ኢሳ.፮፥፭–፯)። ዲያቆን ደም ይሰጥበታል ሱራፌ ለነቢዩ ኢሳይያስ ፍሕመ እሳት በጉጠት ሰጥቶት ኢሳይያስ ከለምፁ የመንጻቱ ምሳሌ ነው። ፍሙ የሥጋው የደሙ ምሳሌ ነው። ለምፁ የኃጢአት ምሳሌ ነው። ሱራፌ የዲያቆኑ ምሳሌ ነው።

ፍሕሙን ሱራፌ በእጅ አለመያዙ በጉጠት መያዙ ሥጋውን ደሙን በእጅ ለመንካት ያልበቃ በዕርፈ መስቀል መስጠት ያለበት መሆኑን ያመለክታል። ኢሳይያስ የምእመናን ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ በሱራፌ ጉጠት ፍሕም ከለምፁ መዳኑ ምእመናን ሥጋውን ደሙን ሲቀበሉ ከኃጢአት የመዳናቸው ምሳሌ ነው።

## ቍርባኑ በጻሕሉ ላይ መቀመጡ ጌታ በመቃብር የመቀበሩ ምሳሌ ነው።

ዕርገተ ዕጣን የደመ ዐቤል፣ የቍርባነ ኖኅ፤ የሂሩተ አብርሃም፣ የመባዐ ይስሐቅ፣ የመልእክተ ሙሴ ምሳሌ ነው ዘፍ.፬፥፱–፲፪፤ ፳፥፩፻፳፤ ፲፪፥፩–፫፤ ፳፱፥፪–፲፰፤ ዘጸ.፫፥፲–፳፪፤ ፬፥፩–፫።

ቡራኬ ፵፪ መሆኑ ይኸውም የሕዝቡ ፳፩፣ የሥጋ ወደሙ ፳፩ መሆኑ ጌታችን በዕለተ ዓርብ ከሌሊቱ በ፫ ሰዓት ከመዓልቱ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ፲፰ ሰዓት ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ለመቀበሉ፣ ሦስት መዓልት፣ ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ለማደሩ ምሳሌ ነው። መዓልትና ሌሊት ሳይቈጠር በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ ፪ ሰዓት መቆየቱንና የወረደበትን ፩ ሰዓት በመቍጠር ፳፩ ሰዓት ስለሚሆን ምሳሌው በዚህም ይሆናል።

የሠራዒ ካህን ዑደት ሰባት መሆኑ ኢያሱ ወልደ ነዌ የኢያሪኮን ግንብ ሰባት ጊዜ ዞሮ እንዳፈረሰ ቄሱም ፯ ጊዜ እየዞረ በሚጸልየው ጸሎት በሚያጥነው ማዕጠንት የምእመናንን የኃጢአት ግንብ ስለሚያፈርስ የዚያ ምሳሌ ነው (ኢያ.ዕብ.፲፩፥፴)።

ካህኑ ዑደት በሚያደርግበት ጊዜ መብራት የያዘው ንፍቅ ዲያቆን ከካህኑ ፊት ቀድሞ የሚሄደው የመጥምቁ ዮሐንስ ምሳሌ ነው። ካህኑ ከንፍቀ ዲያቆን ቀጥሎ ተከትሎ የሚዞረው የጌታ ምሳሌ ስለሆነ ነው። ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ ከጌታ መንፈቅ ቀድሞ ወንጌልን አስተምሮዋልና ከካህኑ ቀጥሎ በኋላው ሆኖ ሠራኢው ዲያቆን መስቀል ይዞ የሚዞረው የቅዱስ እስጢፋኖስ ምሳሌ ነው። ከጌታ ቀጥሎ መከራ የተቀበለ ቅዱስ እስጢፋኖስ ነውና (ዮሐ. ፲፥፶፰)።

በወንጌል ዑደት ጊዜ መብራት የያዘው ንፍቁ ዲያቆን መቅደሙ የነቢያት፣ ንፍቅ ካህን ወንጌል ተሸክሞ መከተሉ የመጥምቁ ዮሐንስ፣ ሠራዒ ካህን እያጠነ ንፍቁን ቄስ ተከትሎ መዞሩ የጌታ፣ ሠራዒ ዲያቆን በኋላ ሆኖ መዞሩ የእስጢፋኖስ፣ ምሳሌዎች ስለሆኑ ነው።

ንፍቅ ቄስ ወንጌሉን ተሸክሞ ከካህኑ ፊት ከዞረ በኋላ ለካህኑ የሚሰጠው መጥምቁ ዮሐንስ መንፈቅ ከጌታ ቀድሞ ከአስተማረ በኋላ ጌታ ወንጌልን የማስተማሩ ምሳሌ ነው (ማቴ.፬፥፲፪–፲፰)።

የንፍቅ ካህን ዑደት ፫ ጊዜ መሆኑ የ፫ቱ ሥላሴ አምሳል ነው (ማቴ. ፳፰፥፲፱)።

የጳውሎስ መልእክት ወደ ምዕራብ የሚነበበው የጳውሎስ መልእክትና ትምህርት የተሰጠው ማለት ጳውሎስ ያስተማረው በምዕራብ ሀገሮች ነው።

የሐዋርያት ሥራና የሐዋርያት መልእክታት በሰሜንና በደቡብ የሚነበበበት ሐዋርያት በሰሜኑም በደቡብም ክፍለ ዓለማት እየተዘዋወሩ ወንጌልን ስለ ሰበኩ ነው (ማቴ.፳፰፥፲፱፤ ዮሐ.፩፥፰)።

ወንጌል ወደ ምሥራቅ የሚነበበው «ውእተ አሚረ ይሠርቅ ለከሙ ፀሐየ ጽድቅ ወሕይወት ታሕተ ክንፈሁ» የተባለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የምትሰብክ ስለሆነ ነው (ሚልክያስ ፬፥፪) ያረገውም ወደ ምሥራቅ ነው። የሚመጣውም ከምሥራቅ ስለሆነ ነው (መዝ. ፷፯፥፴፫፤ 3 ማቴ.፳፬፥፳፯)።

ወንጌል ከተነበበ በኋላ «ዲያቆኑ ንዑስ ክርስቲያኖች ውጡ» ብሎ የሚያውጅበት ምክንያት ንዑስ ክርስቲያን የሚባሉት የክርስትናን ትምህርት ገና በመማር ያሉትና ያልተጠመቁት ስለሆኑ ለመቊረብ የማይችሉ በመሆናቸው ነው።

ሠራዊት ሦስት ጊዜ መባሉ የሦስትነት ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ ነው።

ከመጋረጃ በአፍአ ሠራዊት የሚሉት ንፍቅ ቄስና ንፍቅ "የዖ" ሕዝቡ የነቢያት፣ ከመጋረጃ ሀ ‹ጥ ሠራዊት የሚሉት ሠራዒ ካህን፣ ዲያቆን አብረ ካህን የሐዋርያት ምሳሌዎች ናቸው።

«አርኅው» ሲል በር ወይም መጋረጃ መክፈቱ ጌታ በገበያ ቀን በአደባባይ የመሰቀሉ ምሳሌ ነው።

ካህኑና ሕዝቡ እየተቀባበሉ ፵፩ እግዚኦታ ማድረሳቸው የጌታ የግርፋቱ፣ ካህኑ ፵፩ኛውን ብቻውን የሚለው የአዳም ቀኖና ምሳሌ ነው።

ደሙን ሲቀበል ሁለት ጊዜ አሜን ወአሜን መባሉ ደሙ ሁለት ጊዜ ከሞት በፊትና ከሞት በኋላ የመፍሰሱ ምሳሌ፣ ከሥጋው ጋር ፫ ጊዜ መባሉ «ለቀድሶ ሥጋ ወነፍስ ወመንፈስ» ሥጋውን መቊረሱን ይተረጉማል።

ድርገት ሲወረድ ሕዝቡ ከመሬት የሚወድቀው ጌታ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በመንገድ ቅዱሳት አንስትን አግኝቷቸው «በሀከን» ሲላቸ ድምፁን ሰምተው ከመሬት የመውደቃቸውና የመስገዳቸው ምሳሌ ነው።

ድርገት ወደ ምዕራብ መውረዱ ጌታ ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ ለመሰቀሉ ምሳሌ ነው «እስመ ገጹ ለእግዚአብሔር መንገለ ምዕራብ ከመ ይነጽር ኵሎ ሕዝበ፣ መንገለ ብርሃኑ ዘይሠርቅ» እንዲል። ወደ ምሥራቅ መመለሱ የዕርገት ምሳሌ ነው፤ ያረገው ወደ ምሥራቅ ነውና።

ዲያቆን ከዕርገት በኋላ «ንእኵቶ» እያለ በቅድስት መዞሩ ከጌታ ዕርገት በኋላ እስጢፋኖስ በቅድሚያ አስተምሮ ሰማዕትነት የመቀበሉ ምሳሌ ነው።

አንብሮ እድ እንዲሁም ካህኑ ሕዝቡን በእጁ መባረክ በአረገ ጊዜ ጌታ ሐዋርያትን በአንብሮተ እድ ባርኮ የማረጉ ምሳሌ ነው።

ከካህናት ቀጥሎ አዲስ የተጠመቁ ሕፃናት እንዲቆርቡ የተደረገበት ምክንያት ጌታ የተወለደ ዕለት በመጀመሪያ ያመሰገኑ መላእክት ናቸው ከዚያ በኋላ የእነሱን ዝና ሰምተው ኖሎት (እረኞች) ያመሰገኑ ስለሆነ ነው (ሉቃ.፪፥፲፫–፳) «ጸልዩ» ያለበት የሐዳፌ ነፍስ ጸሎት ጸልዩ እስከሚለው ወደ ምዕራብ፣ ጸልዩ ከአለ በኋላ ወደ ምሥራቅ የሚጸልየው አዳምና ልጆቹ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በሲኦል ከኖሩ በኋላ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከሲኦል ወደ ገነት መመለሳቸውን ለማዘከር ነው (፩ጴጥ.፫፥፲፰–፳፪)።

## ሥጋ ወደሙ ከተቀበለ በኋላ መስገድ የተከለከለበት ምክንያት

፩ኛ. ወዙ እንዳይንጠፈጠፍ ነው።

፪ኛ. ድኅነት በሥጋው በደሙ ሳይሆን በትሩፋት ዳንን እንዳያሰኝ ነው። ❖

ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ
የሊቃውንት ጉባኤ ዐባልና የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መምህር

## በክብርና በጸናጽል መዘመር

ነቢዩ ዳዊት ሰብሕዎ በክበር ሰብሕዎ በጸናጽል ባለው መሠረት ነው። መዝ.፻፶፥፫–፮

## አጽሕሶ

አጽሕሶ ማለት መዘምራን በማስረገጥ የሚያሳዩት ሥነ ሥርዓት ነው፤ ይኸውም ከሰማያውያን መላእክት የተወረሰ እንጂ ልብ ወለድ አይደለም።

መላእክት ፈጣሪያቸውን በሚያመሰግኑበት ጊዜ አክሊላቸውን አውርደው፣ በእግራቸው እያሸበሸቡና እየሰገዱ ያመሰግናሉ፤ በዚህ መሠረት ነው። (ራእ ዮሐ.፬፥፲–፲፩)

## ፅዕዳዌ ልብስ

በጣዕማዊ ማኅሌት ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚያቀርቡት ካህናትና መዘምራን ልብሳቸው በወርቅ ያጌጠና ፀዓዳ መሆኑ ከመላእክትና ከካህናተ ኦሪት አሮን የተወረሰ ነው እንጂ እንግዳ ነገር አይደለም።

ይኸውም «በዙፋኑ ዙርያ ሃያ አራት ወንበሮች አሉ፣ በነዚያ ወንበሮች ላይ ሃያ አራት አለቆች ተቀምጠዋል ነጭ ልብስ ለብሰዋል፣ በራሳቸውም ላይ የወርቅ አክሊል ነበር» ያለው ነው። ራእ.ዮሐ.፬፥፬።

ካህኑ አሮንም ለማዕጠንት ሲገባ የሚለብሰው ልብሰ ተክህኖ በደረቱ ልብሰ እንግድዓ የሚባል ስድስት አዕናቍ ያሉበት፣ እንደ ፀሐይ የሚያበራ በትከሻው ልብሰ መትከፍ የሚባል ስድስት አዕናቍ ያሉበት እንደ ፀሐይ የሚያበራ ለብሶ ወደ ደብተራ ኦሪት ይገባ ነበር። ዘሌ.፰፥፯–፱።

ዜና ቤተ ክርስቲያን – መስከረም ፲፱፻፺፪

www.ethiopianorthodox.org

# ጽዮንን የሚጠልዋት ይፈሩ

ሊቀ ካሕናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ



«ጽዮን የሚለው ቃል ሲነሣ፡ ከሁሉ አስቀድሞ በኢትዮጵያውያን አእምሮ የሚቀረፅ ትዝታ ወይም የሚታወስ ቁም ነገር አለ። ይኸውም በታሪክ፡ በሥነ ጥበብና በቅድስና ያጌጠች፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ የሆነውን በሌላው ዓለም የማይገኘውን ታላቅ ምስጢር በእቅፍዋ ይዛ የዓለም ኅብረተሰብን የምታማልል የአኵስም ጽዮንን ነገር ነው።

አኵስም ጽዮን፡ የምድራዊና የሰማያዊ ጥበብ መገኛ፡ የእግዚአብሔር መመስገኛ፡ የሰውና የመላእክት አደባባይ ናትና ትዝታችንም ሆነ አባባላችን እውነትን መነሻ ያደረገ በመሆኑ ብዙ ሰው ይስማማበታል፤ ይሁን እንጂ አሁንም «ጽዮን» የሚለው ቃል በዚህ ብቻ ሳይወሰን ብዙ ዘርፍና አፅቅ ያለው ቃል በመሆኑ ሌላውንም ቁም ነገር አብረን ማየትና ማገናዘብ ይኖርብናል። በዚህ መሠረት፡ ለመሆኑ «ጽዮን» ማለት ምን ማለት ነው? ታሪካዊ አመጣጡስ እንዴት ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን መነሻ እናድርግና፡ ጥቲቶቹን እውነታዎች እንመልከት።

በመሠረቱ «ጽዮን» የሚለው ቃል የዕብራውያን ቃል ነው። ቃሉ ዕብራይስጥ ወይም አረማይክ ሆኖ ትርጉሙም፡ ፀወን፡ አምባ፡ መጠጊያ ማለት ነው። ስለሆነም ጽዮን በሚለው ቃል ሥር በስፋት ሊታዩ የሚገባቸው ሌሎች ቁም ነገሮች መኖራቸውን ለማስተማር ነቢያት እግዚአብሔር ብዙ ጽፈዋል። ይል ቁንም ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ለጽዮን ያለውን ክበሬታና ፍቅር በየመልኩና በየዘርፉ ገልጿል፤ ለምሳሌ:-

## ፩ኛ. ጽዮን ኢያቡስ

### (የዳዊት ከተማ)

«ጽዮን» የሚል ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠቀስ የምናየው በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ምዕራፍ ፭፥፯ ላይ ነው። በዚህ አባባል ጽዮን የምትገኘው የኢያቡሳውያን መንደር በነበረች ኢያቡስ በምትባል ሰፈር ሲሆን ነዋሪዎችዋም ኢያቡሳውያን እየተባሉ ይጠሩ ነበር። ኋላ ግን ንጉሡ ዳዊት፡ አምባዪቱን ጽዮንን ይዞ ኢያቡሳውያንን ካስገበረ በኋላ ኢያቡስን የዳዊት ከተማ ብሎ ጠርቷታል (ሰይሟታል)። ከዚህ በኋላ ጽዮን የሚለው ስያሜዋ እየገነነ፡ እየሰፋ ሊሄድ ችሏል። ሳሙኤል ካልዕ ፭፥፯–፲። ዜና መ.ቀ.፲፩፥፬–፯። ጠቢቡ ሰሎሞን እግዚአብሔር እንዲሠራው የፈቀደለትን ቤተ መቅደስ ሠርቶ፡ ታቦተ ጽዮን ከድንኳን ወጥታ ወደ ቤተ መቅደስ እስከ ገባችበት ዘመን ድረስ በድንኳን የኖረችው በጽዮን ላይ ነበር። ጽዮን የሚለው ስምም በኢያቡስ ላለችው ተራራ ብቻ የተሰጠ ስም ነበር። መጽ.ነገ.፰፥፩–፲፯። ዜና መ.ካ.፫፥፩–፭።

ታቦተ ጽዮን ከድንኳን ወጥታ ሰሎሞን ወደአሠራው ቤተ መቅደስ በታላቅ ክብር ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ ግን ጽዮን የሚለው ስያሜ ስፋት እያገኘ በመምጣቱ ከኢያቡስ አልፎ ኢየሩሳሌምን በጠቅላላ ወክሎ የሚነገር ስም ሆኖ እናየዋለን። ኢሳ.፳፬፥፳፫። ሚክ.፬፥፯።

## ፪ኛ ጽዮን ኢየሩሳሌም

ጽዮን ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር መመስገኛ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፡ የእግዚአብሔር በረከትና ጸጋ የሚገኝባት ሀገር ቅድስት ስለመሆንዋ ብዙ ተጽፎአል። ጽዮን ኢየሩሳሌም፡ ለእግዚአብሔር መመስገኛነት የተመቸች ሆና በመገኘቷ የተመረጠች የእግዚአብሔር ከተማ ለመባል በቅታለች።

እሥራኤል ዘሥጋ በናቡከደነፆር ተማርከው ከኢየሩሳሌም ወጥተው የባቢሎን ምርኮኞች ሆነው በአሕዛብ እጅ በወደቁበት ዘመን ትልቁ ችግራቸውና ጭንቀታቸው ጽዮን ኢየሩሳሌምን ማጣታቸው ነበረ። ለዚሁም «በባቢሎን ወንዞች አጠገብ በዚያ ተቀመጥን ጽዮንንም ባሰብናት ጊዜ አለቀስን። በአኻያ ዛፎችዋ ላይ መሰንቆቻችንን ሰቀልን። የማረኩን በዚያ የዝማሬን ቃል ፈለጉብን፤ የወሰዱንም:- የጽዮንን ዝማሬ ዘምሩልን አሉን። የእግዚአብሔርን ዝማሬ በባዕድ ምድር እንዴት እንዘምራለን? ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ። ባላስብሽ ምላሴ በጉሮሮዬ ይጣበቅ። ...» በማለት፤ ለቅድስት ሀገራቸው የነበራቸውን ታማኝነት እንደሚገልጹ ትንቢት ተናግሮላቸዋል። መዝ.፻፴፮፥፩–፮። ሌላው እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ እጅግ ደስተኞች ሆነን። በዚያ ጊዜ አፋችን ደስታችን፤ አንደበታችንም ሐሤትን ሞላ፤ ተብሎ የተነገረውን ማስታወስ ይቻላል። መዝ.፻፳፫፥፩–፫። በዚህ አኳኋን ጽዮን ብሎ ኢየሩሳሌምን ለመግለጽ ከሚጠ ቀሱት መካከል የሚከተሉትን በተጨ ማሪ መመልከት ይቻላል። መዝ.፵፰፡ ፹፱፡ ፻፴፫፥፫፡ ኢሳ.፩፥፰፡ ፫፥፲፯፡ ፱፡ ፫፡ ፲፡ ፳፬፡ ፶፪፡ ፩፡ ፰፡ ፲፬።

## ፫ኛ ጽዮን ድንግል ማርያም

ሀ. የጽዮን ትርጉሙ ፀወን፡ አምባ፡ መጠጊያ ነው ካልን፡ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን በመውለዷ ፀወነ ነፍስ ፀወነ ሥጋ፡ ፀወነ ጻድቃን ፀወነ ኃጥአን የሆነችን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። እና ጽዮን ተብላለች። እመቤታችን ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ በመዋሐድ በማኅፀን የነገሠባት ስለሆነች በመንበረ ክብሩ፡ እንዳለ፤ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፡ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ማኅፀንዋን ዓለም አድርጎ ተመስግኖባታልና ጽዮን ደብረ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ተብላለች። መዝ.፪፥፯። እግዚአብሔር ወልድ ማኅፀነ ድንግልን ዓለም አድ ርጎ ሲመሰገን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋናውን ትሰማና ምስጢሩን ታውቅ ነበር። «ድንግል አጽንነት ርእሳ መንገለ ከርሣ» እንዲል።

ለ. «እስመ ሐረያ እግዚአብሔር ለጽዮን ወአብደራ ከመትኩኖ ማኅደሮ፤ እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወዶአታልና።» መዝ.፻፴፩፥፲፫። ይህ ቃል የሚያስት ምረን ለጊዜው ጽዮን ኢየሩሳሌምን ከአገር ሁሉ ለመመስገኛው፤ ለክብሩ መገለጫ እግዚአብሔር እንደመረጣት ቢሆንም ፍጻሜው ግን፤ በንጽሕናዋ፤ በቅድስናዋ በፍጹም ድንግልናዋ ማኅደረ ወልድ እመ አምላክ ትባል ዘንድ የሚገባት መሆኑን፤ እግዚአብሔር ለእናትነት የመረጣት ማኅደረ መለኮትነትዋን፤ ለዘለዓለም ወላዲተ አምላክ፤ ዘለዓለም ቅድስት ዘለዓለም ድንግል መባልዋን ነው።

ሐ. ጽዮን ድንግል ማርያም በቅድስናዋና በዘለዓለማዊ ድንግልናዋ፡ እመ አምላክ፡ እመ መድኅን፡ በመሆንዋ፡ በማይሻር ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳንዋ ተስፋ ብዙኃን (የብዙዎች ተስፋ) በመሆንም እግዚአብሔር በንጽሕና እና በቅድስና ያጸናት፡ የበረከትና የድኅነት መገኛ በመሆንዋ ሰው ጽዮን ድንግል ማርያም እናታችን ይላል ለሷ ተስማሚ ሆኖ ተገኝቷል። መዝ.፹፭፥፭፤ ሉቃ.፩፥፵፰።

መ. «መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን ያበድሮን እግዚአብሔር ለአናቅጸ ጽዮን፡ መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው፡ ...እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይመርጣቸዋል።» መዝ.፹፯፥፩።

ከዚህ ቃል እግዚአብሔር በክበበ ትሰብእት የሚገለጥበት የጽዮን ድንግል ማርያም መገኛዋ ሥርወ ልደቷ፡ እግዚአብሔር የወደደው እግዚአብሔር የመረጠው የቅድስና ምንጭ መሆኑን ከሌሎች ደናግል ይልቅ የእመቤታችን ሕዋሳት ለተዋሕዶ መመረጣቸውን እንማራለን። ስለሆነም መገኛሽ፡ ሥርወ ልደትሽ እግዚአብሔር የመረጠው፡ ሀገረ እግዚአብሔር ጽዮን ድንግል ማርያም ሆይ ስላንቺ የተነገረው ሁሉ ዕፁብ ነው፡ ድንቅ ነው እያልን ጽዮን ድንግል ማርያምን እናከብራታለን እናገናታለን።

ሠ. «እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ፡ ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው። ስፍራው በሳሌም ማደሪያውም በጽዮን ነው።» ተብሎ መጻፉ፡ እግዚአብሔር ከነገደ ይሁዳ ከተወለደች ከእመቤታችን በነሣው ሥጋ በተወለደ ጊዜ፡ የማይታየው ባሕርየ መለኮት፡ ታየ፡ ታወቀ፡ ተረዳ፡ ስሙም በእሥራኤል ዘነፍስ የከበረ የገነነ ሆነ። ማደሪያውም ጽዮን እመቤታችን ናት፤ ማለት መሆኑን በግልጽ እንረዳ ዘንድ ነው። መዝ.፸፭፥፩–፪።

## ፬ኛ. ጽዮን ቤተክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ክብሩ፡ ልዕልናው፡ ገናናነቱ፡ መሐሪነቱና ቸርነቱ የሚገለጥባት፡ በረከቱና ጸጋው ለሕዝበ ክርስቲያን የሚገኝባት፡ የመንግሥተ ሰማያት በር በመሆንዋ ጽዮን ተብላለች። ፀወነ ምእመናን ናትና። እግዚአብሔር ዓቢይ በጽዮን ሲባል በጽዮን ምድራዊት በቤተ ክርስቲያን የሚመሰገን፡ እግዚአብሔር ታላቅ ነው። ማለት እንደሆነ እንገነዘባለን። መዝ.፺፰፥፪።

ምእመናን በፍቅር በሰላም የሚኖሩባት፡ የእግዚአብሔር ማደሪያው መመስገኛው የምትሆን ጽዮን ቤተክርስቲያንን በልዕልና መሥርቷታል በረድኤትም ይጠብቃታል። መዝ.፸፯፥፳፰።

በኪዳነ ኖኅ፡ በኪዳነ አብርሃም፡ ይስሐቅ ወያዕቆብ ጸንታ የምትኖር ጽዮን ቤተክርስቲያን ድንቅ ነገር ይፈጸምባታል፡ ልጅነት ይሰጥባታል፡ ወይን ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር፡ ኅብስት ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር እንዲሆን የሚያደርግ ረቂቅ ሥልጣን የተሰጣት ድንቅ ነገር ረቂቅ ምስጢር ይፈጸምባታል። የበረከተ ሥጋ የበረከተ ነፍስ ምንጭ በመሆንዋ ፀወነ ሥጋ ፀወነ ነፍስ ትባላለች።

ፍቅረ ጽዮን በልቡ የተሳለው ቅዱስ ያሬድም፡ በጽዋትወ ዜማው ለጽዮን አያሌ ቦታ ሰጥቶ ክብሯን፡ ገልጿል፡ ትርጉሟንና አገልግሎቷን በሚገባ አመሥጥሮ አስረድቷል ለምሳሌ፡ «እምነ ጽዮን በሀ ቅድስት ቤተክርስቲያን ሥርጉት በስብሐት» (ጾመ ድጓ ዘመጻጉዕ እገዚል ዘሠሉስ ወይምዚቅ ዘነጳር ጽዮን።)

«ነያ ሀገር መድኃኒት ጽዮን ቅድስት ቤተክርስቲያን ጽኑዕ ጥቅማ» (ሠለስት ዘሰኑይ)።

## ፭ኛ. ጽዮን ኢየሩሳሌም ሰማያዊት

የጽዮን፡ ልዕልናዋ፡ ክብሯና ምሳሌነቷ በምድር ብቻ ተገልጾ የቀረ አይደለም፡ ጽዮን ሀገረ እግዚአብሔር፡ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት መሆንዋም፡ እንዲህ ተብሎ ተጽፎ አል። «ወአንትሙሰ በጻሕክሙ ኀበ ጽዮን ሀገረ እግዚአብሔር ሕያው ኢየሩሳሌም እንተ በሰማያት እናንተ ግን የሕያው እግዚአብሔር አገር ወደምትሆን በሰማያት ወዳለች ወደ ጽዮን ኢየሩሳሌም ደርሳችኋል» ዕብ.፲፪፥፳፪።

«ከዚህ በኋላ ያ በግ በጽዮን ተራራ ላይ ቆመ፤ ከእሱም ጋር ስሙ፡ የአባቱ ስም፡ የቅዱስ መንፈሱም ስም በግንባራቸው የተጻፈባቸው አሥራ አራት እልፍ ካራት ሺሕ ነበሩ።» ራእ.፲፬፥፩–፫፡ ፲፪። ዳን.፯፥፲።

ጽዮን የእግዚአብሔር የጌትነቱና የገናናነቱ መገለጫ፡ እግዚአብሔር የሚመሰገንባት፡ ጽዮን ፀወነ ሥጋ ፀወነ ነፍስ፤ ጽዮን ፀወነ ጻድቃን ፀወነ ኃጥአን፡ ጽዮን የእግዚአብሔር የምስጋና ጌጥ፤ ጽዮን የንጉሥ ክርስቶስ ዙፋን፡ ጽዮን እመ አምላክ ድንግል ማርያም በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ፡ የሚገኝባት በመሆንዋ ሰው እናታችን ጽዮን ወይም ጽዮን እናታችን ብሎ ይማፀናታል። ይመካባታል። በጽዮን አድሮ የሚኖር እግዚአብሔር በረድኤት ይጠብቀኛል ብሎ ተስፋ ያደርጋል። በረከተ ጽዮንን በፍጹም እምነት ይጠብቃል።

በዚህ መሠረት ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት፡ ፍቅረ ጽዮን፡ በረከተ ጽዮን እንዳይጓደልበት በእጅጉ ስለሚሳሳ፡ «ኵሎሙ እለ ይጸልእዋ ለጽዮን ወይኩኑ ከመሣዕረ አንሕስት» ጽዮንን የሚጠሏት ሁሉ ይፈሩ፡ ይዋረዱ ድል ተነስተው ወደ ኋላ ይቅሩ፡ ሳያጭዱት እንደሚደርቅ፡ ለሚያጭዱትም በእጅ እንደማይሞላ፡ ነዶውንም ለሚሰበስበው በእቅፉ እንደማይሞላ፡ በሰገነት፡ ላይ እንደ በቀለ ሣር ይሁኑ ይላቸዋል። በእርግጥም ጽዮንን የሚጠሉ፡ ሰውን ከእግዚአብሔር በረከት የሚለዩ አጋንንት ናቸውና ወይም ሰዎችን ከበረከተ ጽዮን የሚለዩ ሁሉ የአጋንንት መልእክተኞች ናቸውና ሰይጣናዊ ኃይላቸው ይድከም፡ በክፉ ተግባራቸው ይፈሩ፡ ይመከሩ። እንላለን።

በረከተ ጽዮን አይለየን

እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቀን አሜን።





www.ethiopianorthodox.org

# መላእክት እና ተራዳኢነታቸው

መምህር ቀለመወርቅ ኪ/ማርያም

የደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ኃላፊ



«...ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?» (ዕብ.፩፥፲፬)

በትምህርተ መላእክት ልንረዳቸው ከሚገባን ብዙ የትምህርት ክፍሎች ሦስቱን እና ዋና ዋናዎቹን እንመለከታለን።

፩. ተፈጥሮተ–መላእክት (የመላእክት ተፈጥሮ) (The Nature or the Origin of Angels)

፪. አስማተ–መላእክት (የመላእክት ስሞች) (Names of Angels)

፫. ግብራተ–መላእክት (የመላእክት ሥራዎች) (Tasks of Angels)

## ፩. የመላእክት ተፈጥሮ (The Nature of Angels)

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት «በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ።» (መዝ.፴፪፥፮) የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል መሠረት በማድረግ እና «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።» (ዘፍ.፩፥፩) ከሚለው ቃል ጋራ በማያያዝ የቅዱሳን መላእክት ተፈጥሮ በመጀመሪያው የፍጥረት ቀን (እለተ እሑድ) (ኩፋሌ ፪፥፯) (እምኀበ አልቦ) (Out of nothing or free of materiality) ያለ ምክንያት በቃለ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ይስማማሉ።

ዳዊት «መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል።» (መዝ.፻፫፥፬) ሲል የተናገረውን መነሻ በማድረግ የቅዱሳን መላእክት ተፈጥሮ ከእሳት እና ነፋስ እንደሆነ የሚያምኑ ክፍሎች አሉ። ይሁን እንጂ «ከእሳት እና ነፋስ ተፈጥረውስ ቢሆን ኑሮ እንደ እኛ በሞቱ ነበር።» የሚለውን እና በመጽሐፈ አክሲማሮስ ዘኤጲፋንዮስ (ዘ ዕለተ እሑድ) የተመዘገበውን በተጨማሪም ቀደም ሲል ያየነውን «...ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ።» (መዝ.፴፪፥፮) ሲል ነቢዩ የተናገረውን መሠረት በማድረግ «መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል።» የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ለተልእኮ መፋጠናቸውን ለመግለጽ እንደሆነ በመተርጐም (ትርጓሜ ዳዊት ገጽ ፪፹፱) የመላእክት ተፈጥሮ እንደ ነፍስ በቃለ እግዚአብሔር ብቻ እምኀበ አልቦ መሆኑን ብዙኃኑ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ያምናሉ።

## ፪. አስማተ–መላእክት (የመላእክት ስሞች) (Names of Angels)

መላእክት ማለት «ለአከ» ላከ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተመሠረተ ሲሆን መልአክ መልእክተኛ መላእክት መልእክተኞች ማለት ነው። «ለማገዝ የሚላኩ...» (ዕብ.፩፥፲፬) የሚለው እና የጽሑፍ መነሻ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል የስማቸውን ትርጉም ይገልጻል። «ተመልአከ» አለቃ ሆነ የሚለውን የግዕዝ ግሥ መሠረት በማድረግ መልአክ ማለት አለቃ ማለት እንደሆነ የሚተረጉሙ ክፍሎች አሉ።

በብዙዎቹ የመላእክት ስሞች በስተመጨረሻው «ኤል» የሚል ቃል አለ። ኤል ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ አምላክ ማለት ነው (አማኑኤል) መጽሐፈ ሰዋሰው ዘኪ.ወ.ክ ገጽ ፪፻፳፪ «...ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሰሩ ይቅር አይልም እና አታስመርሩት።» (ዘጸ.፳፫፥፳፩) በሚለው ቃለ እግዚአብሔር መሠረት በቅዱሳን መላእክት ስም የእግዚአብሔር ስም ስለ አለ የመላእክትን ስም መጥራት የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ነው በመሆኑም በቅዱሳን መላእክት ስም የእግዚአብሔር ኃይል አለ።

## ፫. ግብራተ–መላእክት (የመላእክት ሥራዎች) (Tasks of Angels)

የቅዱሳን መላእክት ሥራዎች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

### ፩. እግዚአብሔርን ማመስገን (The glorification and service of God)

ቅዱሳን መላእክት በጊዜያቸው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ «ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር።...አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ...እያሉ ይጮኹ ነበር።» (ኢሳ.፮፥፪–፬) «...የብዙ መላእክትን ድምጽ ሰማሁ። የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል።» (ራእ.፭፥፲፪)

### ፪. አማላጅነት (The protection of men and care for their salvation)

የቅዱሳን መላእክትን አማላጅነት ከማየታችን በፊት አማላጅነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንመለከታለን። አማላጅነት ማለት በፊደላዊ ትርጉሙ ማስታረቅ፤ ማስማማት እና አንዱ የሌላውን ሐሳብ እንዲቀበል ማድረግ ነው። በምስጢራዊ ትርጉሙ አማላጅነት ማለት የእግዚአብሔር የስጦታው ማስተላለፊያ መንገድ ነው። እንደ እግዚአብሔር ቃል ምስክርነት የእግዚአብሔር ሥራ በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ይፈጸማል።

፩. እምኀበ አልቦ (ያለምክንያት)

፪. ግብር እምግብር (በምክንያት)

፩. እምኀበ አልቦ (ያለምክንያት) ከተፈጸሙ የእግዚአብሔር ሥራዎች ሰማይን እና ምድርን በቃሉ ብቻ ፈጥሮአል (ዘፍ.፩፥፩) የመቶ አለቃውን ልጅ በቃሉ ብቻ ፈውሷል (ማቴ.፰፥፱)

፪. ግብር እምግብር (በምክንያት) ከተፈጸሙ የእግዚአብሔር ሥራዎች በሙሴ በትር ውሃ ከድንጋይ አመንጭቷል (ዘኁል.፳፥፲፩)፣ በጭቃ እና በሰሊሆም ውሃ እውር ሆኖ ለተወለደው ሰው የዓይን ብርሃንን ሰጥቷል። (ዮሐ.፱፥፩) በቅ.ጳውሎስ ጨርቅ በሽተኞችን ፈውሷል። (የሐዋ.፲፱፥፲፪) በሙሴ በትር፣ በሰሊሆም ውሃ እና በቅ.ጳውሎስ ጨርቅ ኃይሉን ያስተላለፈ እግዚአብሔር የፍጡራኑን (የእመቤታችን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም፣ የቅዱሳን መላእክት፣ ቅዱሳን፣ ጻድቃንና ሰማእታት) የምልጃ ጸሎት ኃይሉን ያስተላልፋል። «እግዚአብሔር በወጀብ እና በአውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው።» (ናሆ.፩፥፫) ሲል የእግዚአብሔር ነቢይ እንደ ተናገረ እና ኢዮብ «እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላም ይናገራል ሰው ግን አያስተውለውም።» (ኢዮ.፴፫፥፲፬) ሲል እንደ ተናገረ አማላጅነት የእግዚአብሔር የኃይሉ ማስተላለፊያ መንገድ ነው።

ቀጥለን የቅዱሳን መላእክትን አማላጅነት ከእግዚአብሔር ቃል እንመለከታለን።

«የእግዚአብሔር መልአክም ዘርሽን እጅግ አበዛዋለሁ። ...እግዚአብሔር መቸገርሽን ሰምቷል እና (ዘፍ.፲፮፥፲–፲፪) ለአጋር መቸገሯን እግዚአብሔር እንደ ሰማት የነገራት የእግዚአብሔር መልአክ ለእኛም መቸገራችንን እግዚአብሔር እንደሰማን እንደሚነግረን እናምናለን።

«ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ...።» (ዘፍ.፵፰፥፲፮) ቅዱሳን መላእክት ከክፉ ነገር ሁሉ ያድናሉ። «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋል እና።» (መዝ.፺(፺፩)፥፲፩) ይህ ቃል የተነገረው ፍጻሜው ስለ ክርስቶስ ቢሆንም ለጊዜው የቅዱሳን መላእክትን ጠባቂነት ለሚያምኑ ሁሉ ነው። «ናቡከደነጾርም መልሶ መልአኩን የላከ ከአምላካቸው በቀር ማንንም እንዳያመልኩ...ብዬ አዝዣለሁ።» (ዳን.፫፥፳፰) ራሱን አምላክ አድርጐ የነበረውን ናቡከደነጾርን በመላእክቱ ኃይል እና በእርሱም አምላክነት እንዲያምን ያደረገ እግዚአብሔር «እኔ እና ገብርኤል እኩል ነን» የሚሉ ትዕቢተኞችን በመልአኩ ኃይል እንደሚያሸንፋቸው እናምናለን።

«...አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ።» (ዳን.፮፥፳፪) ለዳንኤል የአንበሶችን አፍ የዘጋ መልአክ ሊውጠን የተዘጋጀውን የዲያብሎስን አንደበት ይዘጋል። (፩ጴጥ.፭፥፰)

«ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ።» (ዳን.፲፥፲፫) ይህ ኃይለ ቃል ሦስት ነገሮችን ይገልጻል።

፩. ዳንኤልን ሊረዳው የመጣ መልአክ ማን እንደሆነ (ቅዱስ ሚካኤል እንደሆነ)

፪. መዓርጉን (ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ መሆኑን)

፫. ሥራውን (ሥራው ሰዎችን መርዳት መሆኑን) «በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል።» (ዳን.፲፪፥፩) ይህ ኃይለ ቃል «በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው እኔ ገብርኤል ነኝ።» (ሉቃ.፩፥፲፱) ከሚለው የእግዚአብሔር ቃል ጋራ ተመሳሳይነት አለው። ቅዱሳን መላእክት የእኛን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ስጦታ ወደ እኛ ለማድረስ በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ።

«የእግዚአብሔር መልአክ መልሶ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ እነዚህ ሰባት ዓመታት የተቈጣኸቻቸውን ኢየሩሳሌምን እና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው? እግዚአብሔርም መልሶ...ወደ ኢየሩሳሌም በምሕረት ተመልሻለሁ።» (ዘካ.፩፥፲፪–፲፯) ሲል ነቢዩ እንደ ተናገረ እግዚአብሔር በቅዱሳን መልአክት የምልጃ ጸሎት ኃጢአተኞችን ይቅር ይላል።

ዘካርያስ «...ጸሎትህ ተሰምቶልሃል እና አትፍራ...» (ሉቃ.፩፥፲፫) ሲል የነገረውን የመልአኩን ቃል ባለመቀበሉ ድዳ ሆኗል (ቁ.፳) ዛሬም የቅዱሳን መላእክትን የአማላጅነት ኃይል የማያምኑ ሰዎች የመንፈስ ድዳዎች ናቸው። «እነሆም የጌታ መልአክ ቀረበ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ ጴጥሮስን ጐድኑን መትቶ አነቃው እና ፈጥነህ ተነሣ አለው ሰንሰለቶችም ከእጁ ወደቁ።» (የሐዋ.፲፪፥፯) የክርስቲያኖች የነፍስ እና የሥጋ እሥራት በቅዱሳን መላእክት እርዳታ ይቆረጣል። የቅዱሳን መላእክት እርዳታ አያስፈልገኝም ማለት የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ ከተሰጠው (ማቴ.፲፮፥፲፱) ቅዱስ ጴጥሮስ እኔ እበልጣለሁ ማለት እና ፍጹም ትእቢት ነው። በዚሁ ክፍል «...ወደብረቱ መዝጊያ ደረሱ እርሱም አውቆ ተከፈተላቸው።» (ቁ.፲) የሚል ቃል እናነባለን። ግዕዛን–ሰብእ የሌለው የብረት መዝጊያ መልአክ መሆኑን አውቆ ተከፈተ እቃ የሆነው መዝጊያ ያከበረውን መልአክ አላከብርም ማለት አእምሮን ግዑዝ ከሆነው ከመዝጊያው ማሳነስ ነው። «ጴጥሮስም ወደልቡ ተመልሶ ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅ እና የአይሁድ





www.ethiopianorthodox.org

ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንዳዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ አለ።» (ቁ.፲፩) ቅዱስ ጴጥሮስ ለመሠከረለት መልአክ አዳኝነቱን እንመሰክራለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ትርጉም ያልገባቸው ደካሞች «ቅዱሳን መላእክት ከእግዚአብሔር ወደሰው እንጂ ከሰው ወደ እግዚአብሔር አይላኩም።» በሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ስተው ለማሳት ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። ይህ አባባላቸው ፍጹም ስህተት ለመሆኑ ቅዱስ ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ እንዲህ ይላል። «የቅዱሳን ጸሎት ከዕጣኑ ጢስ ጋራ ከመልአኩ እጅ ወደ እግዚአብሔር ወጣ።» (ራእ.፰፥፬) ጸሎታችን የሚያርግበት የመልአኩ እጅ ያስፈልገናል።

## ስግደት ለመላእክት

ለቅዱሳን መላእክት እኛ ልናቀርብላቸው ከሚገባን አንዱ የጸጋ (እግዚአብሔር በተፈጥሮ እና ተልእኮ ስለ አከበራቸው የሚቀርብ) ስግደት ነው። «ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ... ሉጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሣ ፊቱንም ደፍቶወደ ምድር ሰገደ።» ዘፍ.፲፱፥፩ ሉጥ ለቅዱሳን መላእክት በመስገዱ ስህተት ሆኖ አልተቆጠረበትም ይልቁንም ሕይወቱን ከእሳት እንዲያድን ቅዱሳን መላእክት ነገሩት እንጅ «...የእግዚአብሔር መልአክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ፤ ሰግዶም በግምባሩም ወደቀ...» (ዘኁ.፳፪፥፴፩) ወዶ የመልአኩን ቃል ያላከበረ በለአም በመልአካዊ ኃይሉ ተገዶ እንደ ሰገደ ቅዱሳን መላእክትን ወደው ያላከበሩ ትእቢተኞች የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ በመላእክቱ ኃይል ተገደው እንደሚያከብሩአቸው እናምናለን። «...እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት ሁኜ አሁን መጥቻለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደ እና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድን ነው? አለው። (ኢያሱ.፭፥፲፫) ፀሐይን እስከማቆም ድረስ ከእግዚአብሔር ኃይል የተሰጠው ኢያሱ ለሰገደለት መልአክ መስገድ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። «...የእግዚአብሔር መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ አረገ ማኑሄ እና ሚስቱም ተመለከቱ በምድርም በግምባራቸው ተደፉ።» (መጽ.መሳ.፲፫፥፳) ለእግዚአብሔር መልአክ የሰገዱ ማኑሄ እና ሚስቱ በእግዚአብሔር ኃይል የተሞላ ሶምሶንን ወልደዋል። በመንፈሳዊ ኃይል የፀና ልጅን ለመውለድ የሶምሶን ወላጆች ለሰገዱለት መልአክ መስገድ ተገቢ ነው። «ዳዊትም ዓይኖቹን አነሳ የእግዚአብሔር መልአክ በምድር እና በሰማይ መካከል ቁሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ሁኖ ወደ ኢየሩሳሌም ተዘርግቶ አየ። ዳዊትም ሽማግሌዎቹም ማቅ ለብሰው በግምባራቸው ተደፉ።» (፩ዜና.፳፩፥፲፮) እውነተኛ ክርስቲያን ልበ አምላክ ዳዊት ለሰገደለት መልአክ ይሰግዳል። ነቢዩ ዳንኤልም የመልአኩን ውለታ በስግደት መልሷል። (ዳን.፰፥፲፱) «በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ። እርሱም:- እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ።»(ራእ.፳፪፥፰) ይህን ቃል በተሳሳተ መንገድ መነሻ በማድረግ ዮሐንስ ተሳስቶ ሰገደ እንጂ ለመላእክት መስገድ ተገቢ አይደለም የሚሉ ክፍሎች አሉ የመልአኩን አባባል ባለመረዳት እንጂ በጻፈው ወንጌል ምስጢረ ሥላሴን አጉልቶ የጻፈ (ዮሐ.፩፥፩) ክርስቶስን እስከ መስቀል ድረስ የተከተለ እና እመቤታችንን በአደራ የተቀበለ (ዮሐ.፲፱፥፳፭) በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት ለወደፊት የሚሆነውን ሁሉ ያየ እና የጻፈ (ራእ.፩፥፪) ዮሐንስ የሰገደ ተሳስቶ ሳይሆን ለቅዱሳን መላእክት መስገድ ተገቢ መሆኑን ተረድቶ ነው። መልአኩ «...አትስገድልኝ...» ያለው እንደሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን አተረጓጎም ስግደት የበላይነት እና የበታችነት ምልክት ነው በመሆኑም ዮሐንስ በክብር ከመልአኩ ጋራ ተስተካክሎ ስለነበር መልአኩ በክብር እኩል ነን አንተ ለእኔ ልትሰግድልኝ አይገባም ማለቱ ነው። ዮሐንስ ተሳሳተ ማለት የጻፋቸው መጽሐፎች ሁሉ በስሕተት የተጻፉ ናቸው ማለት ይሆናል።

. ለሦስቱ የእግዚአብሔር ሰዎች እሳትን ያጠፋ መልአክ (ዳን.፫፥፳፰) በክርስትና ሕይወታችን እሳት የሆነ ብንን ሁሉ የማጥፋት ኃይል አለው።

. ለዳንኤል የአንበሶችን አፍ የዘጋ መልአክ ሊውጠን የተዘጋጀውን የዲያብሎስን አንደበት ይዘጋልናል (፩ጴጥ.፭፥፰)፤ ለቅዱስ ጴጥሮስ የታሠረበትን ሰንሰለት የቆረጠለት የእግዚአብሔር መልአክ የነፍስ እና የሥጋ እስራታችንን ይቆርጥልናል) (የሐዋ.፲፪፥፯)።

. ለክርስትና ሕይወታችን መሠረት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደ በብስራተ መልአክ ነው። (ሉቃ.፩፥፳፮)

. ለቅዱስ ዮሴፍ ህፃኑ ክርስቶስን ከሔሮድስ ሰይፍ እንዲያድን የተናገረ መልአክ ከክፉ ነገር ሁሉ ሕይወታችንን እንድናድን ይነግረናል። (ማቴ.፪፥፲፫)

. አባታችን ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ የተጠመቀ በመልአኩ ትእዛዝ ነው። (የሐዋ.፰፥፳፮) በመሆኑም ኢትዮጵያዊ ክርስትና በመልአክ እግዚአብሔር እርዳታ የተመሠረተ ነው።

«በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ፤ እነሆ እኔ መልአክን በፊትህ እሰዳለሁ» (ዘጸ.፳፫፥፳)። ✣

ስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወለዲቱ ድንግል ለዓለመ ዓለም

አሜን።



# ከ ወ ጣ ቱ ለ ወ ጣ ቱ

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር



**ገ**ነነው ውብእሸት ገ/ሚካኤል የሃያ አምስት ዓመት ወጣት ነው። ተወልዶ ያደገው እዚሁ አዲስ አበባ ከፍተኛ ፯ ቀበሌ ፳፯ ውስጥ ነው፤ መርካቶ አካባቢ። ወጣት ገነነው በጣም ትሁት፤ ዝምተኛና ትእግሥተኛ ነው፤ ሁኔታው ፍሬ ያዘለ የስንዴ ዘለላ ዓይነት ነው። ንግግሩ ቁጥብ ነው፤ ከአንደበቱ የሚያፈልቃቸው ውሱን ቃላት ግን በቁም ነገር የተሞሉ ናቸው።

ገነነው ከአንደበቱ ይልቅ በጣቶቹ አማካኝነት በብሩሹ ብዙ መናገር፤ ማስተማር፤ መስበክ ይችላል። ገነነው በሥዕል ት/ቤት ገብቶ ዘመናዊውን የሥዕል ጥበብ አልተማረም፤ እንደ ዛም ሆኖ እግዚአብሔር ባደለው ልዩ የተፈጥሮ ችሎታው እየታገዘ የሚስላቸው ሥዕሎች በሞያው ለዓመታት ት/ቤት ገብተው የሠለጠኑ ባለሞያዎች ከሚነድፉዋቸው የጥበብ ውጤቶች የሚያንሱ አይደሉም። ከሁሉ የሚገርመው በዘመናዊ የሥዕል ት/ቤት ገብተው የሚማሩ ተማሪዎች የሚሠለጥኑት በመረጡት አንድ የሥዕል ዓይነት (በርካታ የአሳሳል ጥበቦች አሉና) ነው። ችሎታቸውም እንደ ዚሁ፤ እርሱ ግን ሁሉንም የሥዕል ዓይነቶች ይስላል።

ገነነው ገና ከልጅነቱ ለሥዕል ፍቅርና ተሰጥኦ ነበረው። በተለይ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ በነበረበት ወቅት (የድሮ ወሰን ሰገድ የአሁኑ የካቲት ፳፫ ት/ቤት) ስማቸው ለጊዜው የማያስታውሳቸው መምህር የሥዕል ሞያ በልጅነት አእምሮው ውስጥ ኮትኩተው እንዳሳደጉለት ይናገራል። ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ ወደ ሥዕል ሞያ የገባው ግን የ፲፪ኛ ክፍል ትምህርቱን ካጠናቀቀ ከ፲፱፻፹፩ ዓ.ም በኋላ ነበር።

ወጣት ገነነው በይዘትም በዓይነትም የተለያዩ ሥዕሎችን ይስላል። በአብዛኛው የሚስላቸው መንፈሳዊ ሥዕሎች ናቸው። ባነጋገርኩት ወቅት ከአስተዳደጉ ቀጥየ ያነሳሁለት ጥያቄ «በተለይ ወደ መንፈሳዊ የሥዕል ሥራ እንዴት ልታዘነብል ቻልክ?» የሚል ነበር። ገነነውም በስሜት በተመሰጠ ሁኔታ:-

## በብሩሹ የሚሰብከው ወጣት

«የቤተ ክርስቲያናችን ሥዕሎች ሳያቸው የመማረክ፤ የመመሰጥ በእጠ ቃላይ እኔነቴን የመግለጽ ባሕርይ አላቸው፤ ከዚህም በላይ እነዚህ ሥዕሎች የኢትዮጵያውያን አባቶች ልዩ የጥበብ ውጤቶች መሆናቸውንና የሌሎቹ ዓለም ሠዓልያን ሊደርሱባቸው ያልቻሉ የጥበብ ሥራዎች መሆናቸውን አባቶች ሲያስተምሩ ስሰማ በይበልጥ እየተሳብኩ መጣሁ» አለኝ። በዚህ ግን አላበቃም። በመንፈሳዊ ሥዕል እንዲማረክ ምክንያት ከሆኑት ነገሮች በሁለተኛ ደረጃነት ያነሳው ነጥብም ነበር። «ከውጭ እየመጡ በየመንገዱ የሚሸጡ ሥዕሎችን ሳይ ስሜቴ ይረበሻል፤ እጅግ አስደናቂ ሥዕሎችን ሠርተው አልፈዋል። ታድያ እኛ የአባቶቻችንን ኮቴ ተከትለን ጥበባቸውን ወርሰን ከቻልንም ያንን አበልጽገን መከተል ሲገባን ባለማድረጋችን ምናለ ከአባቶች ምክርና እርምት እየተ ቀበልን የራሳችንን ብንሠራ የሚል ሃሳብ መጣልኝና ጀመርኩት» አለኝ።

የገነነው አስገራሚ ባሕርይና ገጠመኝ በዚህ የሚያበቃ አይደለም። ገነነው የቤተ ክህነት የአብነት ትምህርት የተከታተለው በጣም ለአጭር ጊዜ በሕፃንነቱ በጨቅላነቱ ጊዜ ነው፤ የአጋጣሚ ነገር ሆኖ በቤታቸው ግቢ አንድ የኔታ ነበሩ። ገነነው ‹ሀ› ግዕዝ ‹ሁ» ካዕብ...ብሎ ፊደል ቆጠረ፤ እስከ ወንጌል ድረስ የኔታ ዘንድ ተማረ፤ በታ ከዛ በኋላ ደብተርና እስክሪፕቶ በቦርሳው ተሸክሞ ከእኩያዎቹ ጋር ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ገባ። የኔታ በጨቅላ አእምሮው የዘሩለት የፊደል ፍሬና መንፈሳዊ ስንቅ ግን ዛሬ ድረስ የሕይወቱ ዋልታና ማገር ሆኖ ያገለግለዋል።

ከዚህ በተረፈ ከአዲስ አበባ ወጥቶ ጥንታውያን ገዳማትን፤ የብራና መጻሕፍትንና የብራናና የግድግዳ ላይ ሥዕሎችን የማየት ዕድል አላገጠመውም። እዚህ አዲስ አበባ ያሉትንም ቢሆን ሁሉንም አላየም።

«ራሴን የማግለል ባሕርይ ስላለኝ ብዙ ቦታ ሄጄ አላይም ሰዎችንም አልጠይቅም» ነበር ያለኝ፤ ምክንያቱን ለማወቅ ላቀረብኩለት ጥያቄ ሲመልስልኝ።

በአዲስ አበባ ውስጥ ካያቸው የአብያተ ክርስቲያናት ሥዕሎች ይበልጥ የሚማርከው በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ ያለው ሥዕል እንደሆን ይናገራል። ገነነው ይህንን አስመልክቶ ሲናገር «ተክልየ ውስጥ ያለ ሥዕል በጣም ይመስጠኛል፤ ብዙ ጊዜም እየገባሁ እየዋለሁ በተለይ እዛ ያለው የእመቤታችን ሥዕል እጅግ እወደዋለሁ...በጥበብ ደረጃ ግን ቅዱስ ጊዮርጊስ ውስጥ ያለው የሜትር የአርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ሥዕልን አደንቃለሁ።»

ከሥዕል ሞያ ጋር በተያያዘ ይበልጥ የሚማርኩት የሥዕል ዓይነቶችና የሚያደንቃቸው ሠዓልያን እንዳሉ እንዲገልጽልኝም ጠይቄው ነበር፤ ወጣት ገነነው በፊት የውጭ ሠዓልያንን ያደንቅ እንደ ነበር ገልጾ አሁን ግን ያለው አመለካከት የተለየ መሆኑን ሲያስረዳ። «እድሜዬ እየገፋ ሄዶ ነገሮችን ማገናዘብ ስጀምር ከሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሥዕል ከባድና ምስጢሩም ጥልቅ መሆኑን ማየት ጀመርኩኝ፡ ስለሁኔታው ይበልጥ እያወቅኩ በመጣሁ ቁጥርም በመንፈሳዊ የሥዕል ጥበብ እየተማረኩ መጣሁ።

ከመንፈሳዊ ውጭ የባህል ሥዕሎች በይበልጥ ደግሞ የአፍሪቃውያን ሥዕሎች እኔነቴን የሚያመለክቱኝ ስለሚመስለኝ እወዳቸዋለሁ። ዘመናዊያን የአውሮጳውያን ሠዓሊዎች መሠረታቸው የአፍሪቃ የሥዕል ጥበብ ነው። ሞያውን ከኛ ኮርጀው አሻሽለው የሠሩት ነው የሚመስለኝ» ይላል።

## ኢትዮጵያዊነት ከተዋሕዶ እምነት የማይነጣል ነው

ወጣት ገነነው ውብእሸት እስከ አሁን ከ፫ በላይ መንፈሳዊ ሥዕሎችን ስሏል። ከላይ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው ገነነው በመንፈሳዊ ትምህርት ብዙም የገፋ ባይሆንም በተግባር ሲታይ መንፈሳዊ ሕይወቱና ዕውቀቱ «ተማርን» ከሚሉ አንዳንድ ወገኖች የላቀ ነው። ለዚህ ደግሞ የሳላቸው ሥዕሎች በራሳቸው ምስክር ናቸው። በቂ የመጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን ዕውቀት የሌለው ባለቅኔ የጠለቀ የመጠቀ መልእክት ያለው ቅኔ መቀኘት እንደማይችል ሁሉ የተሟላ መንፈሳዊ ዕውቀት ያልሰነቀ ሠዓሊም የተሟላ መንፈሳዊ መልእክት ያለው ሥዕል መሳል አይሆንለትምና።

ወጣቱ ከሳላቸው ሰባ ሥዕሎቹ መካከል የጥቂቶችን ይዘት እንዲገልጽልኝ ገነነውን ጠይቄው ነበር። ገነነው ሁኔታውን እንዲህ ነበር የገለጸው።

«...እምነትን በሚመለከት ከሳልኩዋቸው መካከል በኃጢአት ጠፍቶ መመለስ፤ ኃጢአት በጣም በዝቶ እግዚአብሔር ያንን ኃጢአት ይቅር እንደሚል፤ ኃጢአት ሰዎችን በምን ያህል ዓይናቸውን እንደሚሸፍን፤ የእመቤታችን ርኅራኄ፤ የመስቀል ኃይል (መስቀል በቤተ ክርስቲያናችን ኃይሉ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ)፤ የክርስቶስን መከራ፤ ቅዱሳን አባቶቻችን ያደረጉዋቸው ተጋድሎና እግዚአብሔር የሰጣቸው ኃይል፤ የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል። በተጨማሪም በተለይ በኔ እድሜ ላሉ **ወጣቶች ግብረ ገብ ምን ያህል ጥቅም እንዳለው መልእክት የምታስተላልፋ «በጠፋው ልጅ» አማካኝነት አንድ የሳልኩዋት ጥሩ ሥዕል አለች።**

ከዚህ በተረፈ ኢትዮጵያዊነት ራሱ ከተዋሕዶ እምነታችን የማይነጣል መሆኑን ለማሳየት የቻልኩትን ያህል ሞክሬአለሁ። ከዚህ ከመንፈሳዊ ሳልወጣ በአብስትራክት የሥዕል ጥበብ በአንድ ሥዕል ሦስት አራት መልእክቶችን ለማስተላለፍም ጥረት አድርጌአለሁ።

ወጣት ገነነው ውብእሸት በአሁኑ ወቅት ኅብረተሰቡን በተለይ ደግሞ ወጣቱን እየቀሰፈ ስላለው ኤድስን አስመልክቶ የሳለው ወቅታዊ ሥዕልም አለው። በዚሁ ሥዕሉ ኤድስ



ከቤተ ክርስቲያናችን ውጭ መድኃኒት እንደ ሌለው አሳይቷል። ሥዕሏን ያዩ ሰዎች ሁሉ አድናቆታቸውን እንደገለጹለትም ይናገራል።

ወጣት ገነነው በዚች ሥዕሉ በዘንዶና በእሳት የተከበቡ ሁለት ሰዎችን በአብስትራክት (በረቂቅ) የአሳሳል ጥበብ አስቀምጧል። መልእክቱ እሳት ማንም ምንም ነገር ይበላና የመጨረሻ ውጤቱ አመድ ያደርጋል።





ዘንዶ አፍ ውስጥ የገባች ትንሽ ሥጋም አትወጣም፤ ኤድስ የያዘው ሰውም እንደዚሁ። ወጣቱ ሠዓሊ በዚህ ሥዕሉ ያስተላለፈው (ለማስተላለፍ የፈለገው) መልእክት ይህ ብቻ አይደለም። ከዚህ መከራ (ከዘመኑ አስከፊ በሽታ) የሚያወጣ ብቸኛ መድኃኒት የሚገኘው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሆኑን፤ እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያን መልካም መድኃኒት እንደሚሰጥ በሥዕሉ ለማሳየት ሞክሯል። በአጭሩ ገነነው በብሩሹ ሰብኳል ማለቱ ይቀላል።

«ሥዕሎች በተለይ ደግሞ መንፈሳዊ ሥዕሎች በሰው ሕይወት ውስጥ ያላቸው አስተዋጽኦ (ድርሻ) እንዴት ይገለጻል?» ገነነው ለዚህ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ የሚከተለው ነበር።

«ሥዕሎች ብዙ ይናገራሉ፤ ሰዎች ንባብን ቢያነቡት ቀለሙን ብቻ ነው አንብበው የሚያልፉት፤ ለመረዳት ብዙ ያስቸግራል። ሥዕሎች ግን ከቀለማቸው ጀምሮ እስከ አገባባቸው የመሳብ ችሎታ አላቸው። ታሪክን በአንድ መጽሐፍ ከመጻፍ ይልቅ በትንሽ ሥዕል ላይ ያንን መጽሐፍ መግለጽ ይቻላል። በተለይ ደግሞ መንፈሳዊ ሥዕሎች በከፍተኛ ደረጃ ሰውን የመሳብ፤ ሃይማኖትን የማጠንከር ባሕርይ አላቸው ብዬ አምናለሁ።»

## ሁላችንም ራሳችንን እንሁን

ገነነው በንግግሩ መሃከል ‹ራስን መሆን› የሚለውን አባባል ደጋግሞ ይጠቀማል። እንደ ገነነው እምነት ከሁሉ በፊት ራስን መሆን መቅደም አለበት፤ ራስን መሆን ማለት ኢትዮጵያዊ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፤ ኢትዮጵያዊ ሆኖ መገኘት ማለት ደግሞ በመልክ ብቻ ሳይሆን በግብርም አበውን መስሎ መገኘት ነው። አበውን መስሎ መገኘት ማለትም በተዋሕዶ እምነት ጸንቶ በሥነ ምግባር ታንጾ፤ ሕገ እግዚአብሔርን አክብሮ መገኘት፤ በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያንና በሀገር ፍቅር ታንጾ ማደግ ማለት ነው።

ለዚህም ነው ወጣት ገነነው «ለወጣቱ የምታስተላልፈው መልእክት ምንድነው?» ስል ላቀረብኩለት ጥያቄ «ከሁሉ በፊት ሁላችንም ወጣቶች ራሳችንን እንሁን ነው የምለው» ሲል የመለሰልኝ። ገነነው ቀጠለ «...እኛ ወጣቶች እምነታችንን አክብረን፤ ሀገራችንን ወደን፤ መልካም ነገርን ለማድረግ መጣር አለብን። አባቶቻችን ያስተላለፉልን መልካም ሥነ ምግባርን በከፍተኛ ሁኔታ መንከባከብ አለብን፤ ካልሆነ ግን የመጣብን በሽታንም ሆነ ሌሎች ችግሮቻችንን ማቃለል የምንችል አይመስለኝም። እኛ ወጣቶች በአሁኑ ሰዓት እያለቅን የምንገኘው ከእግዚአብሔር ርቀን እምነታችንን የሚፃረር ተግባር በመፈጸማችን ነው። እንደ አውሮጳውያን እንደዘመኖቹ እንሁን እያልን አስከፊ በሽታ ውስጥ እየገባን እያለቅን ነው። ከዚህ ከመጣብን መቅሰፍት ለመዳን ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጠግተን፤ ራሳችንን ሰብስበን፤ ራሳችንን ሆነን፤ የማንንም ሳንሻ፤ የሀገራችንን ባህል የራሳችንን እምነት ይዘን በኢትዮጵያዊነታችን መዝለቅ አለብን። ይህን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ የምንችለው» በማለት ነበር የመለሰው።

ገነነው ለሀገራችን ወጣቶች ያስተላለፈው ሌላም መልእክት አለ። «በአሁኑ ጊዜ ወጣቱ በወጣትነት አእምሮው ከእምነቱና ከሀገር ፍቅር ርቆ ሄዷል፤ ስለሆነም ወጣቱ ከአባቶች የሚነገረውን ሰምቶ መልካም ዘር መልካም ዚጋ የሚያፈራበት ጊዜ እናፍቃለሁ። ወጣቱ በአንድ ወቅት ከነገሮች ተምሮ ወደዚህ ይመለሳል ብየ አምናለሁ ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳን» ብሏል። ወጣቶች እውቀታቸውን፤ ጉልበታቸውን አስተባብረው ቤተ ክርስቲያናቸውን ማገል ገል እንዳለባቸው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም ወጣቶች ተሰባስበው የሚሠሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት እንዳለባት ወጣቱ ሳይጠቅስ አላለፈም።

ወጣት ገነነው በሥራው ሁሉ የቤተሰብ ድጋፍ እንዳልተለየው እንድያውም ለዚህ ደረጃ የደረሰው በቤተሰቡ የተሟላ እገዛና እንክብካቤ መሆኑን ገልጾልኛል። በተለይ ታላቅ ወንድሙ ለሥዕል ሥራው የሚያስፈልገውን ወጪ ከመሸፈን አልፎ የሞራል ድጋፍ እንደሚያደርግለት ቤተሰቡችም ለሥዕል መሥሪያ የሚሆን የተለየ ክፍል እንደሰጡት በእርካታ ገልጿል። የጓደኞቹ የሞራል ድጋፍም የዚያን ያህሉ አበረታች መሆኑን ነው የሚናገረው። እርሱ ራሱ እንዳለው «በዚህ በኩል እድለኛ ነው» ማለት ይቻላል።

አሁን ስለ ወጣት ገነነ የቀረን አንድ ነገር ብቻ ነው፤ በሰንበት ት/ቤቶች ያለው ተሳትፎ። ወጣት ገነነ ካለው የብቸኝነት ባሕርይ የተነሳ በሰንበት ት/ቤት ያለው ተሳትፎ ከሌላው ወጣት የተለየ ነው ማለት ይቻላል። በአብዛኛው ጊዜውን የሚያሳልፈው በሥዕል ሥራ ስለሆነ በሰንበት ት/ቤት እንቅስቃሴ አዘውትሮ አይሳተፍም። በእርግጥ በየማታው በሚካሄዱት ጉባኤዎች ይሳተፉል። በክብረ በዓላት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን አይጠፉም። ከሁሉ በላይ ገነነን የሚማርከውና የሚስበው የሕፃናት ተሳትፎ ነው።

«እኔን በተለይ ደስ የሚለኝ ግን ሕፃናት በሰንበት ት/ቤት ተምረው ሲመረቁ ሳይ ነው። በዚህን ጊዜ እረካለሁ፤ ሕፃናት መድረክ ላይ ለብሰው ሲዘምሩ፤ ትያትር ሲያሳዩ፤ ሳያቸው መታደላችን ይታየኛል» ይላል ገነነ።

ብዙ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች እንደሚያውቅና ወጣቶችም የተለያዩ ምክሮችና እገዛዎች እንደሚያደርጉለት ብዙ ዕውቀትንም እንደሚያካፍሉት ወጣት ገነነ በእርካታ ይናገራል። ካለፈው ዓመት ጀምሮ በየቦታው እየተካሄዱ ያሉት ጉባኤያት በእጅጉ እንደጠቀሙትም መስክሯል። ገነነ በአሁኑ ጊዜ በግል የሥነ ጥበብ ት/ቤት የዘጠኝ ወራት ሥልጠና መጀመሩን ነግሮኛል። ለወደፊቱም ከቻለ በአዲስ አበባ የሥዕል ጥበብ ት/ቤት ገብቶ ለመማርና ባህላዊውን የቤተ ክርስቲያን አሳሳል ከአበው ለመቅሰም ብሎም እስከ መጨረሻው በሞያው ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ዕቅድ አለው።

. ስለ ገነነ አንድ የመጨረሻ ላውጋችሁና ልሰናበት። ገነነ ውብእሸት አጥቢያው አዲሱ ሚካኤል ነው። ነገር ግን ቅዳሜና እሑድ ይሁን በዕለተ ቅዱስ ሚካኤል፤ ቅዱስ ገብርኤል፤ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወዘተ ብቻ በበዓላት ጊዜ ሁሉ የሚያስተድሰው፤ ጸሎቱን የሚያደርሰው በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም እየመጣ ነው። ሌላው ቀርቶ «በፍልሰታና በዓብይ ጾም እዚህ መምጣቱ ይቀለኛል» ባይ ነው። «ለምን?» ብየው ነበር፤ «የሚያውቁኝ ሰዎች ሁሉ እዚህ ሲያገኙኝ ይህን ሁሉ አገር አቋርጠህ ለምን ትመጣለህ ይሉኛል ምክንያቱ ግን እኔም ራሴ አላውቀውም፤ ሰው ይገርመዋል እኔንም ራሴ ይገርመኛል። እመብርሃን የለመነኋትን ሁሉ ተሎ ስለምታሳካልኝ ነው መሰለኝ። ብቻ ከደጅዋ መራቅ አልፈልግም።...» ነበር መልሱ።

ለሁላችንም የእመብርሃን ረድኤትና በረከት አይለየን አሜን። ❖



www.ethiopianorthodox.org

# እስትግቡእ

(እስትግቡእ — ጥርቅም፣ የተቀመመ፣ የተሰባሰበ ማለት ነው)

ዳግና በትግራይ ክልል በማዕከላዊ ዞን በናእዴር ወረዳ ከአክሱም ከተማ በስተ ደቡብ ፸ ኪ.ሜ ያህል ርቆ ከታላቁ የወርኢ ወንዝ ሸለቆ ጠርዝ ፩ ሺህ ፮ መቶ ሜትር ከባሕር ጠለል በላይ ከፍታ ባለው በእምነ በረድ ድንጋይ በተሸፈነ መልክዓ ምድር ላይ የተመሠረተ የ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጥንታዊ ገዳም ነው።

ይህ አካባቢ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ጥቅጥቅ ባሉ የቆላና የወይናደጋ ዛፎች የተሸፈነ፣ የዝሆን፣ የአንበሳ፣ የነብር፣ የአጋዘን፣ የአሳማና የከርከሮ፣ የጅብና የዝንጀሮ፣ የእባብና የዘንዶ፣ ዋንኛ መራቢያና መናሐሪያ የነበረ ሲሆን የጥንቶቹ ኢትዮጵያውያን አዳኞች በዚህ አካባቢ ተሰማርተው የአደን ተግባራቸው ሲያከናውኑበት የነበረ ነው።

በሌላ መልኩ ግን ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ይህንን ዓለም መንነው በዱርና በገደል ተሰማርተው፣ የቀን ፀሐይ፣ የሌሊት ብርድ፣ ድምፀ አራዊትን፣ ረሀብና ጥማትን፣ ታግሰው እጅግ በጣም መራራ የሆነውን ምናኔያዊ ገድላቸውን ለመፈጸም ቆርጠው ሲነሱ እንደ አባይና ተከዜ፣ ወርኢና መረብ፣ የመሳሰሉትን ታላላቅ ወንዞችና ሸለቆዎችን ተከትለው በዓተ ቅዱሳንን በመፍጠር እድል ያጋጠማቸውና እግዚአብሔር ያሳካላቸው በግል ይጸልዩባቸው በነበሩ በዓቶች አካባቢ እስከ ዘመናችን ድረስ የዘለቁ ታላላቅ ገዳማትን መስርተው በማለፍ ለታሪካችን መሠረት የሆኑ ሃይማኖታዊ ቅርሶችን አበርክተውልን አልፈዋል።

ከፊሎቹ ደግሞ ከላይ በጠቀስናቸው ታላላቅ ወንዞች ደን ለበስ ሸሎቆዎችና ዋሻዎች ሲጸልዩ፣ ሲሰግዱ፣ ዘመናቸውን ያሳለፉ ኅቡዓን በአህዝ ለመቍጠር የማይቻል ጉዳይ ነው። በእነዚህ አካባቢዎች በሺ የሚቆጠሩ መናንያን ተሰማርተው አጥንታቸው ያረፈበት የቅዱሳኑ ጸሎት ያረገበት ረድኤተ መንፈስ ቅዱስ ያልተለየው የቅዱሳንም ዓፅም ያረፈበት አካባቢ ለመሆኑ ግን እስከ ዘመናችን ድረስ ታሪካቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የኢትዮጵያ ቅዱሳን ገድል እናነባለን። ለአብነት የዋልድባን፣ የደብረ አባይን፣ የደብረ ፅሞናን፣ የደብረ ሃሌሉያን፣ የአሰቦትን፣ የጕንዳ ጕንዲን፣ የመዝባእን፣ የማህበረ ሥላሴን፣ የደብረ ዓሳን፣ መካነ ቅዱሳን ገዳማት ታሪክ ብንመለከት በእነዚህ አካባቢዎች በሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ዓፅም ያረፈበትና ገድለ ቅዱሳን የተፈጸመበት ለመሆኑ ከምናነባቸው የኢትዮጵያ ቅዱሳን ገድላት ለመረዳት እንችላለን።

ይሁንና በዛሬው ጽሑፋችን ለመግለጽ የምንፈልገው በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተነሡት የኢትዮጵያ ቅዱሳን መካከል አንዱ የሆነው አባ ገብረ ክርስቶስ ዘገዳመ ዳግና በተመለከተ ሲሆን የገብረ ክርስቶስ መሠረታዊ ታሪክ እንዴት እንደሆነ በገዳመ ዳግና ከተገኘው ገድሉ ያገኘነውን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

## ዳግና አቡነ ገብረ ክርስቶስ ገዳም

ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በ፫፻፴፫ ዓ.ም በአብርሃ ወአጽብሃ ዘመን መንግሥት ከሣቴ ብርሃን አባ ሰላማ ወደ እስክንድርያ ሄዶ መዓርገ ክህነትን ጥምቀተ ክርስትናንና ሥርዓተ ቍርባንን፣ መጻሕፍተ ሐዲሳትን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ በአክሱም ታቦተ ጽዮንን ያገለግሉ የነበሩ ካህናተ ኦሪትን አስተምሮ፣ አጥምቆ፣ አቍርቦ፣ ካህናተ ቤተ ክርስቲያን ሲያደርጋቸው በወቅቱ የነበረው ካህነ ኦሪት እንበረም በመጀመሪያ መዓርገ ዲቁናን፣ ቀጥሎ መዓርገ ቅስናን ሰጥቶ በመሾም ስሙንም ለውጦ ሕዝበ ቀድስ ብሎ በመሰየም ከእኡ በታች ሕዝብን አስተምር፣ አጥምቅ፣ አቍርብ፤ ብሎ ሙሉ ሥልጣን በመስጠት ኤጲስ ቆጶስ ብሎ በማለት አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ሾመው።

ኤጲስ ቆጶስ ሕዝበ ቀድስ ሥልጣነ ክህነትና ሙሉ መዓርገ ኤጲስ ቆጶስነት ካገኘ በኋላ ስብከተ ወንጌልን ጥምቀተ ክርስትናን ለማስፋፋት ቆርጦ በመነሳት በአክሱምና በአካባቢዋ ጀምሮ እስከ ኖባና ሳባ የሀገረ ናግራን፣ የትግራይ፣ የአንጎት፣ የአማራ፣ የሰሜን፣ የበጌምድር፣ የሲዋ፣ ሕዝቦችን አስተምሮ፣ አጥምቆ፣ ጠንካራ ክርስቲያኖችን አፈራ።

ሕዝበ ቀድስ የትውልድ ሐረጉ እንዴት እንደሆነ ገድለ ገብረ ክርስቶስ በዝርዝር ሲተነትነው ሕዝበ ቀድስ ሕዝበ ባርከን ወለደ፣ ሕዝበ ባርከ ከትግራይ ወጥቶ ወደ ዳውንት በመሄድ በዳውንት ተቀምጦ ጋሕረ ቃጋ ከተባለች ቀበሌ ተቀምጦ በዚህ አካባቢ ከሚኖሩ ባላባቶች ዘንድ ሚስት አግብቶ ተክለ ቈአትን ወለደ፣ ተክለ ቈአት ከአማራ መቅደላ ከተባለች ሀገር ባላባቶች ዘንድ ሚስት አግብቶ ሰባት ልጆችን ወለደ።

በዚች ሀገር የተወለዱት የተክለ ቈአት ልጆች አድገው ቤት ንብረት አበጅተው ርስትና ጉልት ይዘው እስከ ዛሬ ድረስ ሰባቱ ታላላቅ ካህናተ ደብተራ ዘሀገረ ጽዮን ተብለው የሚታወቁ ሲሆኑ ከነዚህም መካከል አንዱ አፅቀሌዊ የተባለው ሰው የወለቃና የአማራ የመርሃቤቴ፣ የመንዝ ሕዝቦችን ያስተማረና ያጠመቀ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን የተከለ ሰው ነው።

አፅቀሌዊ በአማራ ሀገር ቀበሮ ጕሽ ከተባለ ሀገር ከሚኖሩ ባላባቶች ሚስት አግብቶ አባ ይድላ ዘምድረ ዞሮሬና አራሞን ወለደ፣ አራሞም ከዋድላ ባላባቶች ሚስት አግብቶ ተስፋ ሕፃንን ወለደ፣ ተስፋ ሕፃንም በኮረ ጽዮንን ወለደ፣ በኮረ ጽዮን ይግናህ መስቀልን ወለደ፣ ይግናህ መስቀል ሴሩህን ወለደ፣ ሴሩህ እንበረምን ወለደ፣ እንበረምም ቦኤዝን ወለደ፣ ቦኤዝም ሕዝበ ቀድስ ዳግማዊን ወለደ፣ ሕዝበ ቀድስ ዳግማዊ ብርሃን መስቀልን ወለደ።

በዚህ ዘመን ሰሎሞናዊው የአክሱም ሥርወ መንግሥት ወደ ነገደ ሄጳጳ ወይም ነገደ ዛጕዬ ተዛወረና ብርሃነ መስቀል ከአክሱም ንቡረ እዶች ወገን የሆነች ሚስት አግብቶ በአማራ ሀገር እየተቀመጠ ተክለ አልፋን ወለደ፣ ተክለ አልፋም ከሰሜን መሳፍንት ዘር ሚስት አግብቶ ዘርዓ ሥናይን ወለደ፣ ዘርዓ ሥናይም መንግሥተ እስራኤልን ወይም ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥትን ከዛጕዬ ነገዶች መንግሥትን የመለሰ አፄ ይኩኖ አምላክን ወለደ፣ አፄ ይኩኖ አምላክም የዓለም ብርሃን የገዳም ኮከብ የሆነውን ብፁእና ቅዱስ አቡነ ገብረ ክርስቶስን የአክሱም ንቡረ እዶች ወገን ከሆነች ማርታ ከምትባል ሴት ወለደ፣ በማለት ገድለ ገብረ ክርስቶስ ዘዳግና ትውልደ ሐረጉ ይዘረዝራል።

አቡነ ገብረ ክርስቶስ ከአፄ ይኩኖ አምላክ ተወልዶ ወደ ትግራይ ገዳመ ዳግና እንዴት እንደገባ ብዙ ዝርዝር ባይገልጽም አቡነ ገብረ ክርስቶስ በልጅነቱ አባቱን እናቱን ወንድሞቹንና እህቶቹን ትቶ ወደ ምናኔ ዓለም በመሰማራት የአራዊትና የእንስሳት መነሀሪያ እጅግ በጣም አስፈሪና አስቸጋሪ ወደ ሆነው ገዳመ ዳግና ገብቶ የዱር አራዊት ጓደኛ በመሆን ለ፵ ዓመታት ያህል ከማንም ሰው ጋር ሳይገናኝ ብቻውን በገዳመ ዳግና በምናኔና በብህትውና ተቀምጧል።

አቡነ ገብረ ክርስቶስ በዚህ በረሃማው የዳግና ተራራና ሸለቆ እየተዘዋወረ ሲቀመጥ የወንድሙ የአፄ ሰይፈ አርዕድ ወታደሮች ዝሆን፣ አንበሳ፣ ነብር፣ አጋዘንና ወንደቢ፣ በወርኢ ሸለቆና በአካባቢዋ ለማደን ሲዞሩ በድንገት አንድ ቀን ዳግና ጫካ ውስጥ እየተሽሎከለኩ ሲያድኑ የአራዊት እንጂ የሰው ድምፅ በምንም ዓይነት መንገድ ከማይሰማበትና ከማይታይበት ጫካ ውስጥ አንድ ግርማ ሞገስ የተሞላበት አቡነ ገብረ ክርስቶስን ሲጸልይ አገኙትና ወደ እሱ ተጠግተው በእንክሮ እየተመለከቱ የእግዚአብሔር ሰላምታ በመስጠት ማነጋገር ጀመሩ።

አቡነ ገብረ ክርስቶስም ለ፵ ዓመታት ከሰው ተለይቶ በተቀመጠበት ፅሞና በረሀ ሰዎች በማየቱ ተደስቶ ሰላምታውን ካቀረበላቸው በኋላ ከየት መጣችሁ ትውልድ ሀገራችሁስ ወዴት ነው ብሎ ጠየቃቸው እነሱም እኛ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የአፄ ሰይፈ አርዕድ ወታደሮች ነን ሃይማኖታችንም ክርስቲያኖች ነን ወደዚህ አካባቢ የመጣነውም አራዊትን ለማደን ነው ብለው መለሱለትና እሱም መስቀሉን አውጥቶ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ፣ በረከት ይደርባችሁ ብሎ ባረካቸው ወታደሮቹም እርስ በእርሳቸው እየተጠቃቀሱ ይህ ሰው በዚህ በረሃ ላይ የተለያዩ አደገኛ የዱር አራዊቶች በነገሡበት ጫካ ብቻውን የሚኖረው እውነት ምድራዊ ሰው ነው ወይስ ሰማያዊ መልአክ እየተባባሉ ተነጋገሩ።

ቀጥለውም ለአደን እንደ መጡ ርቦአቸው ነበርና እስኪ የሚበላ እንደ አለው ብለው አባታችን ሆይ ለብዙ ጊዜያት በአደን ምክንያት በረሃ ለበረሃ እንደቆየን ነንና እባክህን የሚበላ ምግብ እንደ አለህ ካለአንተ በስተቀር በዚህ አካባቢ ሌላ ሰው አላገኘንምና ብለው ጠየቁት እርሱም ሥር እየማሰ ቅጠል እየበጠሰ የሚመገብ ባህታዊ እንጂ ሌላ ምግብ የማይመገብ ቢሆንም የእግዚአብሔር እንግዶች በገዳሙ መጥተውበት ምግብ የለኝም ብሎ መመለሱ የፈጣሪውን ትእዛዝ አለማክበር ስለሆነበት የተራቡትን አዳኝ ወታደሮች ለመመገብ ያስችለው ዘንድ ወደ ፈጣሪው እንዲህ ሲል ጸለየ።

«ሙሴ ደቂቀ እስራኤልን ከግብጽ ይዞ ሲወጣ በሲናይ በረሀ መና ከሰማይ አዝንመህ ነገደ እስራኤልን የመገብካቸው አንተ ነህ ለኢያሱ መስፍን ከአለት ውሃ አፍልቀህ እንዲጠጣ ያደረግህ አምላክ አንተ ነህ ሳሙሶንን ከባላቅ ጋር ጦርነት በገጠመ ጊዜ ከአህያ መንጋጋ አጥንት ውሃ እንዲፈልቅለትና እንዲጠጣ ያደረግህ አምላክ አንተ ነህ ለእኔ ለባርያህም እነዚህን እንግዶች የምመግብበት እንጀራና ውሃ ስጠኝ» እያለ ሲጸልይ መልአከ እግዚአብሔር አንድ እንጀራና ሁለት ቆቆችን ይዞ መጣና እንካ እነዚህን ቆቆችን ቀቅለህ እንግዶችህን መግባቸው ብሎ ሰጠው።

አቡነ ገብረ ክርስቶስም ፈጣሪውን የላከለትን ምግብ በምስጋና ተቀብሎ ቆቆቹን ቀቅሎ በአንድ እንጀራ አድርጎ ለወታደሮቹ ቢያቀርብላቸው እንግዲያውስ ይህ ሰው በቂ ምግብ አለው ደብቆን ነው እንጂ ብለው እኛ ብዙዎች ነን አንድ እንጀራና ሁለት ቆቅ ምን ይበቃናል ብለው ጨምረን እያሉ ቢያንገራግሩ ደግነትና የዋህነት ገንዘቡ የሆነው አቡነ ገብረ ክርስቶስ ይህንን በልታችሁ ጨርሱ እግዚአብሔር ያበረክተዋል ብሎ ቢላቸው ጨምረን እንጂ ይህንን ብቻ አንበላም ብለው ከአንዱ ሁለቱ ከሁለቱ ሦስቱ ቢለምናቸው የወታደር ነገር የባላገር ቤት መስሎአቸው አንበላም አሉ።

አቡነ ገብረ ክርስቶስም እንግዲያውስ ሌላ ምግብ እግዚአብሔር ይስጣችሁ ብሎ እነዚያን የተቀቀሉ ቆቆች በመስቀሉ ባርኮ እፍ እፍ አለባቸውና ከተቀቀሉበት ድስት እየበረሩ ወደየ መጡበት ዋሻና ዛፍ ተሰቀሉ። ወታደሮቹም ይህንን የአቡነ ገብረ ክርስቶስን ተአምር አይተው እየተደነቁ ምንም ነገር ሳይበሉ አደሩ። በበነጋታው ጥዋት ወደ አቡነ ገብረ ክርስቶስ ዘንድ መጥተው እጃቸውና እግራቸው እየተንቀጠቀጠ ተንበርክከው በመስገድ ይቅርታ በመጠየቅ ወደ ንጉሣቸው ተመልሰው የአቡነ ገብረ ክርስቶስን ተአምር ነገሩት።

የአቡነ ገብረ ክርስቶስ ተአምራዊ ሥራዎች በገድሉ ላይ በስፋት የተጻፉ በመሆናቸው በዚህ አጭር አምድ ላይ ማስፈር ባይቻልም ስለ ዳግና ገዳም አመሠራረትና በአሁኑ ወቅት ተመሳሳይና ተወዳዳሪ ስለሌላት የደብረ ዳግና ሕንፃ ቤተክርስቲያን አስተናነጽ ታሪክ በአጭሩ መጥቀሱ አስፈላጊ ይመስለናል።

አቡነ ገብረ ክርስቶስ ከአፄ ሰይፈ አርዕድ ሠራዊት ጋር ከተገናኘ በኋላ ንጉሡ የዚህ ጻድቅ ዜና ሰምቶ ወደ እርሱ እንዲመጣ እንደ ገና ሌሎች ወታደሮችን ልኮ እንዳስጠራውና እሱም ከትግራይ ወደ ሸዋ ተመልሶ ከአፄ ሰይፈ አርዕድ ጋር በ፲፪፻፺፩ ዓ.ም አካባቢ ከንጉሡ ጋር ተገናኘ። የአፄ ይኩኖ አምላክ ልጅና ወንድሙ መሆኑን ከገለጸለት በኋላም ብዙ ጉዳዮችን አንስተው ተነጋገሩ። ከዚያም ወደ ዳግና ተመልሶ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ሱባኤ ከገባ በኋላ እንደ ገና ከትግራይ ወደ ሸዋ ደብረ ሊባኖስ መጥቶ ከአቡነ ዮሐንስ ከማ ተባርኮና ሥርዓተ ምንኩስና ተቀብሎ በደብረ ሊባኖስ ገዳም አሥር ዓመት ከተቀመጠ በኋላ እንደ ገና ወደ ትግራይ ገዳመ ዳግና ገብቶ ገዳም መስርቶ ሲቀመጥ የሮማ ንጉሥ ልጅ የሆነ መልከ ጼዴቅ የተባለ ባህታዊ ታቦተ ሥላሴንና ቅዱሳት መጻሕፍትን ልዩ ልዩ ንዋየ ቅዱሳቶቹን ይዞ አቡነ ገብረ ክርስቶስ ወደ አለበት ገዳመ ዳግና ሄዶ ተቀመጠ።

ከዚያም ቀጥሎ ባህታዊ መልከ ጼዴቅ ከአቡነ ገብረ ክርስቶስ ጋር ሲኖር አባቴ ሆይ በዚች ቅድስት ገዳም ቤተ ክርስቲያን እንሥራ ሲል ጠየቀው፣ አቡነ ገብረ ክርስቶስም ልጄ ወዳጄ ሆይ እንደ ፈቃድህ ይሁን አለውና አዲስ ቤተ ክርስቲያን ማነጽ ጀመሩ የዚችም ቤተ ክርስቲያን ግብረ ሕንፃ አሠራር ሁሉ በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አምሳል ነው አስተናነጿ እጅግ በጣም ያማረ ሲያዩዋት የምታምርና የምታስደንቅ ቤተ ክርስቲያን ታነጸች ከዚህ በኋላ አቡነ ገብረ ክርስቶስ ባህታዊ መልከ ጼዴቅን ልብሰ ምንኩስና አልብሶ አመንኩሰው ከጊዜ በኋላም በእርሱ ምትክ የማህበረ መነኮሳቱ አለቃ አድርጎ ሾመው።

አቡነ ገብረ ክርስቶስና መልከ ጼዴቅ አዲስቱን ቤተ ክርስቲያን ካነጹ በኋላ ብዙ መናንያን ከአማራና ከትግራይ አካባቢዎች እየተሰባሰቡ በደብረ ዳግና ገዳም ገብተው በአቡነ ገብረ ክርስቶስ እጅ እየመነኮሱና እየተማሩ ከዚያም የየራሳቸው ገዳማትን እየመሠረቱ መኖር ስለ ጀመሩ የአቡነ ገብረ ክርስቶስ የቆብ ልጆች የሆኑ መነኮሳት የመሠረትዋቸው ገዳማት በአማራና በትግራይ በብዛት ተመስርተዋል።

በዚህ መሠረት በጣም እውቅ ከሆኑት መነኮሳት መካከል ስማቸውና ገዳማቸው፣

- አቡነ መልከ ጼዴቅ በደብረ ዳግና
- አቡነ ቴዎድሮስ በደብረ መቃራት
- አቡነ ነገደ ብርሃን በምድረ ለውሳ ጉባይ
- አቡነ ሴት በምድረ ዠማ
- አባ ተንስኢ ክርስቶስ በምድረ ኖቢ
- አቡነ ይምርሐ ክርስቶስ በምድረ አላል ደብረ አቡካዕ
- አባ ተወልደ ብርሃን በምድረ ሽሬ
- አባ ዘሚካኤል በምድረ መንዝ

ወዘተ. የመሳሰሉት ገዳማት የአቡነ ገብረ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መሆናቸው ሲታወቅ የእነዚህ ሁሉ ርእሰ ገዳማትና እናት ገዳም ግን በመልከ ጼዴቅ የበላይነትና አስተባባሪነት ገዳመ ዳግና እንዲሆን ብሎ አቡነ ገብረ ክርስቶስ የራሱ ሕግና ሥርዓት ደንግጎ አልፎአል።

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ገዳመ ገብረ ክርስቶስ ደብረ ዳግናን በአካል ሄዶ በማየትና በመጐብኘት ታሪኳንና ሥርዓትዋን በማጥናት ሥነ ጥበባዊ ቅርሶችዋን ፎቶ ግራፍ በማንሳት ያከናወናቸው ጥናታዊና ታሪካዊ ውጤቶች ለወደፊት በከለር ፎቶግራፍ ተቀነባብረው የሚታተሙ ቢሆኑም አቡነ ገብረ ክርስቶስና ባህታዊ መልከ ጼዴቅ ያነጽዋት ቤተ ክርስቲያን አምሳለ እስክንድርያ መሆንዋን ገድለ ገብረ ክርስቶስ ቢገልጽም በበኩሌ እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ካየሁዋቸው አቢያተ ክርስቲያናት ሁሉ ፍጹም የተለየችና የጣርያዋ ፲፱ ቀስተ ደመናዊ ቅርጽ ያላቸው ቤተ መቅደሶች የመንበር ታው ከአለት ተፈልፍሎ የተሠራው ሚካኤል አንባ ወይም የላሊበላው ቤተ መድኃኔ ዓለም በቅድስቱና በቅኔ ማህሌቱ ያሉትን ቀስተ ደመናዊ ቅርጽ ያላቸው አዕማድን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ✣

ከግርማ ኤልያስ




www.ethiopianorthodox.org